የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

16ኛ ቮልዩም ኅዳር፣ 1986	በዓመት አንድ የሚታተም **An Annual Journal**	Vol. XVI November, 1993

በዚህ እትም፤

የፍርድ ጉዳዮች

የምርምር ፅሁፎች

1. ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ፖሊሲ ተጠቃሚውን ለይቶ ስለማስታወቅ

   በዶ/ር ግርማ ወልደ ሥላሴ

2. ይርጋ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 /እንደተሻሻለ/ በሠንጠረዥ "ሐ" ካሉ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተከፋይ የሆነውን ግብር ከመሰብሰብ መብት ጋር በተያያዘ፣

   በአቶ በቀለ ኃይለ ሥላሴ

3. በኢትዮጵያ የሥራ ማቆም መብት አጠቃላይ አመለካከት።

   በአቶ ጥላሁን ተሾመ

In this issue:

CASE REPORTS

ARTICLES

1. Designation of the Beneficiary of a Life Insurance Policy in the Event of Death.

   Dr. Girma Wolde Sellassie

2. Limitation of Actions in Relation to the Recovery of Taxes on Income from Sources Chargeable under Schedule C of the Ethiopian Income Tax Proclamation.

   Ato Bekele Haile Sellasie

3. An Overview of the Right to Strike in Ethiopia.

   Ato Tilahun Teshome

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

16ኛ ቮልዩም
ኅዳር፣ 1986

Vol. XVI
November, 1993

በዚህ እትም፣

የፍርድ ተላዮች

የምርምር ፅሁፎች

1. ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ፖሊሲ ተጠቃሚውን ለይቶ ስለማስታወቅ

   በዶ/ር ግርማ ወልደ ሥላሴ

2. ይርጋ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 /እንደተሻሻለ/ በሠንጠረዥ "ሐ" ካሉ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተከፋይ የሆነውን ግብር ከመሰብሰብ መብት ጋር በተያያዘ፣

   በአቶ በቀለ ኃይለሥላሴ

3. በኢትዮጵያ የሥራ ማቆም መብት አጠቃላይ አመለካከት።

   በአቶ ጥላሁን ተሾመ

In this issue:

CASE REPORTS

. ARTICLES

1. Designation of the Beneficiary of a Life Insurance Policy in the Event of Death

   Dr. Girma Wolde Sellassie

2. Limitation of Actions in Relation to the Recovery of Taxes on Income from Sources Chargeable under Schedule C of the Ethiopian Income Tax Proclanation.

   Ato Bekele Haile Sellasie

3. An Overview of the Right to Strike in Ethiopia.

   Ato Tilahun Teshome

የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ቢያንስ በዓመት አንዴ እየተዘጋጀ የሚወጣ።
በ1957 ዓም ተመሠረተ።

(16ኛ የኢት. ሕግ. መ. ተብሎ ይጠቀስ)

የቦርድ አባሎች

አቶ ዮሐንስ ኅሩይ
በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
ማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የጥናት የምርምርና የዕቅድ መምርያ ኃላፊ
(ሊቀመንበር)

አቶ ሽፈራው ወልደ ሚካኤል
የሕግ አማካሪ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ትምህርት ቤት
የትርፍ ጊዜ ረዳት ፕሮፌሰር

አቶ መከብብ ይጋው
የሕግ አማካሪና ጠበቃ

አቶ ሐጎስ ደበሱ
በግዮን ሆቴሎች አስተዳደር
የሕግ አማካሪ።

ወ/ሮ አሪጂናል ወልደ ጊዮርጊስ
በፍትሕ ሚኒስቴር
የሕግ ባለሙያ።

አቶ ኢብራሂም ኢድሪስ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ትምህርት ቤት ዲንና
ረዳት ፕሮፌሰር

አቶ ጥላሁን ተሾመ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ትምህርት ቤት
ረዳት ፕሮፌሰር

አቶ ዘካርያስ ቀንዓ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሕግ ትምህርት ቤት
ሌክቸረር።

አዘጋጆች

አቶ ጥላሁን ተሾመ
ዋና አዘጋጅ

አቶ ዩሐንስ ሄኔ
የምርምር ጉዳዮች አዘጋጅ

አቶ ደታየው ዓለማየሁ
የፍርድ ጉዳዮች አዘጋጅ

አቶ አወል ሰይድ
ሥራ አስኪያጅ አዘጋጅ

ፀሐፊዎች

ወ/ሮ ምሕረት አደራየ
ወ/ት ዓይኔ ዑመር

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published at least once a year by the Faculty
of Law of Addis Ababa University

Founded in 1965

(to be cited as J. Eth. L., Vol. 16.)

EDITORIAL BOARD

Ato Yohannes Heroui
Head, Research and Publications Department of
The Central Supreme Court of
The Transitional Government of Ethiopia
[Chairman]

Ato Shiferaw Wolde Michael
Law Consultant and
Part-time Assistant Professor
Faculty of Law,
Addis Ababa University

Ato Ibrahim Idris
Assistant Professor and
Dean, Faculty of Law
Addis Ababa University

Ato Mekbib Tsegaw,
Attorney and Law Consultant

Ato Tilahun Teshome
Assistant Professor
Faculty of Law
Addis Ababa University

Ato Hagos Debessu,
Legal Advisor,
Ghion Hotels Administration

Ato Zekarias Keneaa
Lecturer
Faculty of Law
Addis Ababa University

Woiz. Original Wolde Ghiorgis
Legal expert, Ministry of Justice.

EDITORIAL STAFF

Ato Tilahun Teshome
Editor-in-Chief

Ato Yohannes Chanie
Articles Editor

Ato Yitayew Alemayehu
Cases Editor

Ato Awol Seid
Managing Editor

Secretaries

Woiz. Mehret Aderaye
Woizt. Ayni Umer

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት

በ1956 ዓ.ም የተቋቋመው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት የኤል.ኤል.ቢ. ዲግሪን ይሰጣል። እንደዚሁም ዲፕሎማ የሚያስገኝ ፕሮግራም አለው። ስለማንኛውም ጉዳይ መረዳት ቢያስፈልግዎ፣ ለሕግ ፋኩልቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 1176፣ አዲስ አበባ፣ ብለው ይጻፉ።

የሕግ መምህራን
1985 ዓ.ም

ኢብራሂም ኢድሪስ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ፕሮፌሰርና ዲን፣
አበራ ጀገቱ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ዲንና ረዳት ሌክቸረር፣
ዳንኤል ኃይሌ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣
ስዩም በቀለ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣
ጥላሁን ተሾመ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣
በቀለ ኃይለ ሥላሴ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ሌክቸረር፣
ዘካርያስ ቀነዓ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ሌክቸረር፣
ዮሐይ ጥዳ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ሌክቸረር፣
ዮሐንስ ሜኔ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ኤም ፊል፣ ሌክቸረር፣
አወል ሰዒድ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ሌክቸረር፣
ሰለሺ ዘዮሐንስ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ሌክቸረር፣
ጥዱ መንግሥቱ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ሌክቸረር፣
ይታየው ዓለማየሁ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ሌክቸረር፣
መዝገበ ኃይለ መስቀል፣ ኤል ኤል ቢ፣ ረዳት ሌክቸረር፣

የከፊል ጊዜ መምህራን

ፀፈሬው ወልደ ሚካኤል፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣
ጌታቸው አበራ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ሌክቸረር፣
ወንዲማገኘሁ ገብረ ሥላሴ፣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ ሌክቸረር፣
ማይክል ጃና ቴምባው፣ ቢሲ ኤል ድርፕ፣ ኤም ኤ፣ ፒ ኤች ዲ፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY
FACULTY OF LAW

The Faculty of Law of Addis Ababa University, established in 1964, offers courses in law leading to the LL.B. Degree and to a Diploma in law. For further information you may contact the Faculty of Law, Addis Ababa University, P.O.Box 1176, Addis Ababa.

Faculty

Ibrahim Idris, LL.B, Assistant Professor and Dean,
Aberra Degefa, LL.B, Assistant Lecturer and Assistant Dean
Daniel Haile, LL.B, LL.M, Associate Professor
Selamu Bekele, LL.B, Assistant Professor
Tilahun Teshome, LL.B, Assistant Professor
Bekele Haile selassie, LL.B, Lecturer
Zekarias Kenea, LL.B, LL.M, Lecturer
Tsehay Wada, LL.B, Lecturer
Yohannes Chanie, LL.B, LL.M, M.Phil., Lecturer
Awol Seid, LL.B, Assistant Lecturer
Seleshi Zeyohannes, LL.B, Lecturer
Mola Mengistu, LL.B, Lecturer
Yitayew Alemayehu, LL.B, Lecturer
Mezgebe Haile Meskel, LL.B, Assistant Lecturer.

Part-time Faculty

Shiferaw Wolde Michael, LL.B, LL.M, Assistant Professor
Getachew aberra, LL.B, LL.M, Lecturer
Wondimagegnehu Gebre Selassie, LL.B, LL.M, Lecturer
Getachew Mengistie, LL.B, LL.M, Lecturer
Michael Djiene Wembou, Lic. en Droit, M.A., Ph.D.,
Associate Professor

የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት

ቮልዩም 10 መሆን የነበረበት በስህተት ቮልዩም 11 ተብሎ በመውጣቱ ቮልዩም 10 በሚል የሚታወቅ መጽሔት የሌለ መሆኑን እንገልጻለን።

ሕግ ነክ የምርምር ጽሁፎች እንዲሁም በፍርዶችና በሕጎች ላይ የተጻፉ ትችቶችን ብትልኩልን በደስታ እንቀበላለን። ለሕትመት ብቁ መሆናቸው ሲታመንባቸውም በመጽሔታችን እናወጣቸዋለን።

አድራሻችን፣ ለዋና አዘጋጅ
የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሕግ ትምህርት ቤት
ፖ.ሣ.ቁ. 1176
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ነው።
የስልክ ቁጥር 11-17-33

የመጽሔታችን ደንበኞች መሆን የምትሹ፣ ለቡክ ሴንተር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፖ.ሣ.ቁ 1176፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ብላችሁ መጻፍ ትችላላችሁ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

We inform all subscribers and readers that Vol. 10 of the Journal had come out as Vol. 11 due to error as a result of which there is no Vol. 10.

The editors encourage all interested persons to submit to us any manuscript which would be suitable for publication in the Journal such as scholarly articles, comments on court decisions, and commentaries on ligislations.

Our address is: The Editor-in-Chief
Journal of Ethiopian Law,
Faculty of Law,
P.O.Box 1176
Addis Ababa, Ethiopia.

Tel. 11-17-33

The Journal is distributed by the Book Center of Addis Ababa University. If you wish to subscribe, please address correspondence to the Book Center, Addis Ababa University, P.O.Box 1176, Addis Ababa, Ethiopia.

<u>የአዘጋጆች መልክት</u>

የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ለሕግ ባለሙያዎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን ጥናታዊ ጽሁፎችና ጥናቶች እያተመ የሚያወጣ የምርምር እትም ነው።

አንድ የምርምር ጽሁፍ በዚህ መጽሔት በሚታተምበት ጊዜ በቦርዱ ወይም የአዘጋጆች ክፍሉ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የሠፈሩት ንድፈ ሀሳቦች ሁሉ ፍጹም ናቸው የሚል አመለካከት ኖሮት እንዳልሆነ ከወዲሁ ለመጠቆም እንወዳለን። ይሁንና የጽሁፉ ጥራትና ብቃት ለሕትመት ከሚያበቁት መለኪያዎች ውስጥ አንዱ አስፈላጊው እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል። በቦርዱ አባላት ወይም በአዘጋጆቹ እምነት አንድ ፍርድ አሳሳቢና ጠቃሚ የሕግ ጉዳዮችን የሚያነሳ መሆኑ ከታመነ፣ ፍርዱ በሙሉም ሆነ በከፊል አከራካሪ ነጥቦች ያሉት ከሆነ፣ ወይም ፍርድ ቤቱ በያዘው ጭብጥ ላይ የደረሰበት መደምደሚያ ጉዳዩን ለመፍታት ያለው ብቸኛ አማራጭ አይደለም የሚል ግምት ከተወሰደ፣ በዚህ መጽሔት ታትሞ ሊወጣ ይችላል።

<u>From The Editors</u>

The journal of Ethiopian Law is a scholarly publication addressing itself to all member of the legal profession. In publishing a particular article, the Board and editors do not wish to convey the impression that it is definitive on any proposition for which it may stand although the quality of the article is an important consideration in determining whether it should be included in the Journal. When, in the opinion of a Board member or an editor, a judgment is of interest and raises an important issue of law, or there is reason to believe that aspects of the decision are contestable, or the result reached by the court is not clearly the only supportable conclusion, it may be published in the Journal.

ማውጫ

ገጽ

የፍርድ ትችቶች

1. የፍ.ብ.ይ.መ.ቁ. 749/70 /ጠቅላይ ፍርድ ቤት/ 1
2. የፍ.ብ.መ.ቁ. 602/73 /ከፍተኛ ፍርድ ቤት/ 10
3. የፍ.ብ.ይ.መ.ቁ. 677/76 /ጠቅላይ ፍርድ ቤት/ 28

የምርምር ጽሁፎች

1. ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ፖሊሲ ተጠቃሚውን ለይቶ ስለማስታወቅ

   በዶ/ር ግርማ ወልደ ሥላሴ 48

2. ድርጋ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) በሠንጠረዥ "ሐ" ካሉ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተከፋይ የሆነውን ግብር ከመሰብሰብ መብት ጋር በተያያዘ፣

   በአቶ በቀለ ኃይለሥላሴ 81

3. በኢትዮጵያ የሥራ ማቆም መብት አጠቃላይ አመለካከት፣

   በአቶ ተፋውን ተሾመ 178

TABLE OF CONTENTS

Page

Case Reports

1. Civil Appeal Case No. 749/70 /Supreme Court/ 6

2. Civil Case No. 602/73 /High Court/ 20

3. Civil Appeal Case No. 677/76 /Supreme Court/ 40

Articles

1. Designation of the Beneficiary of a Life Insurance Policy in the Event of Death

   By Dr. Girma Wolde Selassie 67

2. Limitation of Actions in Relation to the Recovery of Taxes on Income From Sources Chargeable under Schedule 'C' of the Ethiopian Income Tax Proclamation No. 173/1961 (As Amended).

   By Ato Bekele Haile Selassie 141

3. An Overview of the Right to Strike in Ethiopia

   By Ato Tilahun Teshome 216

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 749/70

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም፥ ከመድን ተቀባይ ሕይወት በኋላ ወራሾቹና ተረው የትዳር ጓደኛ የሚኖራቸው መብት፥ የመድን ሰጭ ግዴታ፥ የመድን ውልን እሊፈጸም በተመለከተ ስለሚጠበቀው ቅን ልቦና፥ በሞቢንት ያልፋሉ ወይም ከተከሳሽ ጋር የክሱን ድርሻ ይጋራሉ የሚባሉ ሦስተኛ ወገኖች በክስ ውስጥ ስለሚጣመሩበት ሁኔታ፥ ስለጣልቃ ገብነት የንግድ ሕግ 691-701-705-706 - የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41-43፥

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽዋ በስም የተጠቀሰሁ ተጠቃሚ በመሆኔ ከመድን ውሉ የሚገኘው ገንዘብ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ ያቀረቡት ጥያቄ ገንዘቡ ቀደም ሲል በአውራጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ለሟቹ ወራሾች ስለተከፈለ መልስ ሰጭው አይጠየቅም ብሎ በሠጠው ፍርድ የቀረበ ይግባኝ ነው።

ውሳኔ:- ፍርዱ ተሽረዋል፥

1. በሕይወት መድን ውል የሚከፈለውን ገንዘብ በውሉ ተለይቶ ለተሰየመው ተጠቃሚ መክፈል የመድን ሰጭው ግዴታ ነው።

2. በዚህ ረገድ በመድን ውሉ ላይ ተሰይሞ ተጠቃሚ የሆነው ሰው የሚያቀርበውን ጥያቄ ለመጣለስ በታች ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ለወራሾች ከፍያለሁ በማለት መድን ሰጭው መከራከሪያ ሊያደርገው አይችልም።

ጥር 25 ቀን 1971 ዓ.ም

ዳኞች: አቶ ተሾመ ኃይለማርያም
አቶ አበበ ወርቄ
አቶ ጌታቸው አፍሬማ

ይግባኝ ባይ ወ/ሮ የሺመቤት ጀማነህ፥
መልስ ሰጭ: የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

የግራ ቀኙን ክርክር መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሣኔ

ለዚህ ይግባኝ መነሻ የሆነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 1133/69 በ26/5/70 የሰጠው ውሳኔ ነው።

የሰር ክስ በአሁኑ ይግባኝ ባይ የቀረበ ሲሆን ተያቄዎም ሟቹ ወንድሜ አቶ እንግዳ ጀማነህ ለብር 30,000 /ለሠላሳ ሺህ ብር/ የሕይወት ኢንሹራንስ ሲገባ ተጠቃሚ አድርጎኝ በነበረው መሠረት የተባለውን 30,000 ብር እንዲከፍለኝ ድርጅቱን ጠይቄው እህትነቴን አሳውቄ ስመጣ የሚከፍሉኝ መሆኑን አረጋግጦልኝ፣ እህትነቴን አሳውቄ ስመጣ ገንዘቡን ወራሾች ለሆኑት ለሟቹ ልጆች ከፍያለው በማለት ከልክሎኛል፣ ይህ የኢንሹራንስ ክፍያ በንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና 706 በተደነገገው መሠረት የውርስ ሀብት እንደሆነ ስለማይቆጠር፣ የመድን ድርጅት በኢንሹራንሱ ውል የተመለከተውን 30,000 ብር እንዲከፍለኝ በማለት የቀረበ ነው።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሰጠው የሰር መልስ ወ/ሮ የሺመቤት የኢንሹራንስ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ ወራሽነታቸውን እንዲያረጋግጡ ተነግሯቸው ነበር። ነገር ግን እሳቸው ወራሽነታቸውን ከማረጋገጣቸው በፊት የሟቹ ልጆችና ሚስት ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ስለመጡ በተጨማሪም የአውራጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/2450/67 ኅዳር 29/1968 እና የካቲት 4/1968 በሰጠው ትእዛዝ ገንዘቡ ለሟቹ ወራሾች እንዲከፈል ስለወሰነ፣ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ለወራሾች ከፍለናል። ገንዘቡንም ሲወስዱ ተቃዋሚ ቢመጣ እኛው እራሳችን ተከራክረን እንመልሳለን ብለው ፈርመዋል፣ ስለዚህ ክሱ መቅረብ ያለበት በወራሾቹ ላይ ስለሆነ፣ ወራሾች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት በክሱ ውስጥ ይግቡልን በማለት መልስ ሰጥቷል።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጣልቃ ይግቡ ተብለው የተጠየቁት የሟቹ ወራሾች በክርክሩ ውስጥ ገብተው መልስ እንዲሰጡ አዝዞ ተጠሪዎቹ በ20/4/70 በሰጡት መልስ ጣልቃ የሚያስገባን ምክንያት የለም ብለው ተቃውመዋል። የሰር ከሳሿም የመድን ድርጅት ሳይከሰስ ለማይገባቸው ሰዎች ገንዘቡን ከፍሎ ከተገኘ ራሱ ከሰሶ ከሚጠይቅ በስተቀር ከኃላፊነት የሚድንበት ምክንያት ስለሌለ፣ እንዲከፍለኝ ይፈረድበት በማለት ተከራክረዋል።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ የኢንሹራንሱ ውል ተጠቃሚ ወ/ሮ የሺመቤት መሆናቸውንና በሌላ በኩልም የንግድ ሕግ ቁ. 701 እንደሚያመለክተው ወራሾችም ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑን የተቀ ቢሆንም፣ የመድን ድርጅቱ አከራካሪ የሆነውን ገንዘብ ለሟቹ ወራሾች የከፈለው ገና በራሱ ፈቃድና ሀሳብ ሳይሆን የአዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/2450/67 በጥር 29/68 እና የካቲት 4/68 በሰጠው ትእዛዝ ስለሆነ፣ ድጋሚ እንዲከፍል ሊጠየቅ አይገባም ብሎ ፈርዷል።

ይግባኝ ባይ በ29/9/70 በተጻፈ ማመልከቻ በዚህ ፍርድ ላይ ያላትን ቅሬታ አቅርባለች። ቅሬታውም በአጠቃላይ ሟቹ የኢንሹራንሱ ገንዘብ ለይግባኝ ባይዋ እንዲሰጥ በግልጽ መቀቀላቸውንና፣ የኢንሹራንሱ ፖሊሲም በእኔ እጅ መኖሩን ያውቃል። ለእኔም ገንዘቡ እንዲከፈለኝ በጠየቅሁት ጊዜ ማንነቴን በፍርድ ቤት አረጋግጬ ስመለስ የሚከፍለኝ መሆኑን ገልጾልኛል። ይህን ሁሉ እያወቀ ተጠቃሚው ከውሉ ላይ ባልተገለጸ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነውን ሕግ ጠቅሶ የሚከራከረኝ ያላግባብ ከመሆኑም በላይ ያውራጃው ፍርድ ቤት አዝዞኝ ከፍያለሁ ስለሚለውም ቢሆን በውሉ የተጠቀሰውን ተጠቃሚ ስለሚያውቅ ከኃላፊነት ሊያመልጥ አይችልም።

የከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአውራጃው ፍርድ ቤት አሠራር ትክክል አለመሆኑን ከገለጸ በኋላ ኢንሹራንሱ ኩባንያ አይጠየቅም ብትፈልጊ የወሰዱትን ሰዎች ክሰሽ ብሎ የፈረደው ያላግባብ ነው በማለት የቀረበ ነው።

መልስ ሰጭው በበኩሉ በነገረ ፈጁ አማካይነት በ1/11/70 በጻፈው መልስ ወራሾቹ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ቢመጡ ዋስትና የተሰጠበትን ገንዘብ እንደሚከፍል ቃል የገባ መሆኑ አይካድም፣ ወ/ሮ የሺመቤት በንግዱ ሕግ መሠረት በተጠቃሚነት የተጠቀሱ ቢሆንም በዚሁ ሕግ ውስጥ ደግሞ የኢንሹራንሱን ውል የፈረመው ሰው ባለቤትና ልጆቹ ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ተገልጿል። ወ/ሮ የሺመቤት ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ከመምጣቸው በፊት የአቶ እንግዳ ሚስትና ልጆች ወራሽነታቸውን አሳውቀው መጥተዋል።

ወ/ሮ የሺመቤትም ቢሆኑ ታምራት እንግዳ ለተባለው ለሟቹ ልጅ ነገረ ፈጅ ናቸው። የአውራጃው ፍርድ ቤትም በመ/ቁ/4311/67 በ7/5/68 በሰጠው ውሳኔ የወ/ሮ የሺመቤትን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ከመሆኑም በላይ በመ/ቁ/2450/67 በ29/5/67 በሰጠው ትእዛዝ ደግሞ የኢንሹራንሱ ውል ፖሊሲ ዋናው ካልቀረበ ወይም ከጠፋ የሟቹ ወራሾች የውርስ መብታቸውን ሊያጡ ወይም ሊቀርባቸው አይገባም።

የኢንሹራንስ ፖሊሲውን ተከራካሪዎ እውን ባያቀርቡትም ሆነ በእጃቸው ባይኖት ከላይ ከቍ ቁጥሩ እንደተገለጸው የውርስ የሕግ ባለመብቶች የሟቹ ወራሾች ልጆች ናቸው በማለት አዝዞላቸዋል። ከዚያም ቀጥሎ በ4/6/68 በሰጠው ማብራሪያ "የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ድርጅት ተደም ሊል በደረሰው ውሳኔ መሠረት ይፈጽምላቸው ዘንድ የዚህ ትእዛዝ ግልባጭ" ተገልብጦ ይተላለፍለት በማለት ገንዘቡን ለወራሾቹ እንድንከፍል ሰላዘዘን ሌላ ተከራካሪ ቢመጣ ተከራክረው ሊመልሱ ግዴታ አለባቸውን ለወራሾቹ ከፍለናል።

ይግባኝ ባይዋ በውሉ መሠረት መጠቀም ትችላለች ቢባል እንኳን፥ ወራሾችን ከምትጠይቅ በስተቀር መልስ ሰጭን ልትጠይቅ አትችልም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናለት ጠይቋል።

በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር መርምረናል። ሟቹ በነበረው የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ይግባኝ ባይ በግልጽ መጠቀሷ አልተካደም። መልስ ሰጭ የሚከራከረው በንግድ ሕግ ቁ. 701 የተደነገገውንና ያውራጀው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ ምክንያት በማድረግ ነው። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ በኢንሹራንስ ገቢውና በኢንሹራንስ ሰጭው መካከል የሚደረግ ውል ነው። የኢንሹራንስ ሰጪውም በፖሊሲው መሠረት መፈጸም ግዴታው ነው። በፖሊሲው ውስጥ ተጠቃሚው ከተጠቀሰ ገንዘቡ መክፈል ያለበት ለዚሁ ለተጠቀሰው ሰው መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 691 ተደንግጓል። በተጨማሪም ተጠቃሚው ኢንሹራንስ ሰጭውን በቀጥታ የሚጠይቅ ስለመሆኑ በ ቁ. 706 ተገልጧል። ይግባኝ ባይም የጠየቀችው በዚሁ መሠረት ነው። መልስ ሰጭ በውሉ መሠረት መፈጸም ሲገባው ለማን ልክፈል ብሎ ፍርድ ቤቱን መጠየቁ የቅን ልቡና አሠራር ካለመሆኑም በላይ ተጠቃሚው ባልተጠቀሰው ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነውን አንቀጽ በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር የውርድ በጅ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ይግባኝ ባይ በፖሊሲው መሠረት መልስ ሰጭ እንዲከፍላት መጠየቋ ታውቋል። መልስ ሰጭው ይግባኝ ባይ አስፈላጊውን ሥርዓት ሁሉ ፈጽማ እንድትመጣ ጽፎላታል። በጻፈላትም መሠረት በፍርድ ቤት ፋይል ከፍታ የጂመቤት ጀግነህ መሆኑዋን አረጋግጣለች። መልስ ሰጭው የመድን ድርጅት ለወራሾች ከፍያለሁ ለሚለው የሰጠው ምክንያት ፍርድ ቤት አዝዞኛል የሚል ነው። ነገር ግን በሕይወት ኢንሹራንስ ውል መሠረት ገንዘቡ መከፈል የሚገባው ለተጠቃሚው በመሆኑ በዚህም ጉዳይ ተጠቃሚዋ ወ/ሮ የጂመቤት ጀግነህ ስለሆኑች መልስ ሰጭው በውሉ መሠረት ተጠቃሚ ለሆኑችው ለይግባኝ ባይዋ መክፈል ሲገባው ለፍርድ ቤት ጽፎ በማምታታት ባሰጠው ትእዛዝ ከኃላፊነት ሊድን አይችልም።

ስለዚህ የመድን ድርጅት ኃላፊነቱንና ተግባሩን ተገንዝቦ መሥራት ያለበት ቢሆን ይህን እሌፍ ውኔታውን እየወቀና እየተረዳ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ መከታ አደርጋለው በሚል አስተሳሰብ የመራው ሆኖ ስላገኘነው የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ውል ሳያመዛዝን የሰጠውን ፍርድ ሽረን በውሉ መሠረት ከስ የተረበበትን ገንዘቡ ይከፍላል በማለት ፈርደናል። ይጻፍ።

The Supreme Court of Ethiopia
Civil Appeal Case No. 749/70

Designation of a beneficiary in a life insurance policy - rights of the heirs and the surviving spouse in the event of death of an insured person - obligation of an insurer - good faith required in the performance of a life insurance contract - joining third parties as persons liable for contribution or indemnity to the defendant - intervention - Comm. C. Arts. 691, 701, 705, 706 Civ. Pro. C. Arts. 41, 43.

On appeal from a judgment of the High Court denying claim of the designated beneficiary to be entitled to the proceeds of a life insurance policy where such payment was earlier made to the heirs of the insured upon order of the Addis ababa Awraja Court.

Held: Judgment reversed

1. *Payment of the proceeds of a life insurance policy to the designated beneficiary is an obligation the insurer must assume.*

2. *Order of a lower court in this regard cannot be invoked for relief from subsequent payment to be made to the designated beneficiary.*

Tir 25, 1971*

Justices: Ato Teshome Haile Mariam
" Abebe Workie
" Getachew Afrassa

Appellant: Woiz. Yeshimembet Jemaneh

Respondent: The Ethiopian Insurance Corporation

After examining the arguments of both parties, we have rendered the decision as follows:

Decision

This is an appeal from the judgment of the High Court rendered on Tir 26, 1970 under file No. 1133/69.

The present appellant who initiated this proceeding alleged that:

1. her brother the late Ato Engidà Jemaneh had designated her as the beneficiary of his life insurance policy the proceeds of which is Birr 30,000;

2. upon the death of her brother she claimed payment of the said amount, but the respondent requested her to produce a dully probated court order in which her status is established;

3. when she fulfilled the request, the respondent once again failed to pay her the money on the ground that it had already effected the payment to the children of the deceased who are also his heirs;

4. pursuant to Art. 705 and 706 of the Commercial Code, money due from this policy does not form part of the estate of the insured person;

and pleaded that the Insurance Corporation pay her the proceeds of the policy, i.e. Birr 30,000.

The Ethiopian Insurance Corporation affirmed that when the appellant claimed the proceeds of the policy, she was told to have her status as an heiress established. Before she had complied with the request, the respondent contended, the spouse and children of the deceased produced a dully probated certificate of heirship from the Awraja Court on Tir 29, 1968 under file No. 2450/67. As it was further instructed to effect payment of the proceeds of the policy to these heirs by the said court, the Corporation stated, it had complied with the order and paid the sum to them. Respondent went on further and stated that the heirs have undertaken to intervene in any litigation that may ensue regarding this payment and prayed that these heirs be joined in the proceeding in accordance with Art. 41 of the Civil Procedure Code.

When the High Court ordered that the heirs of the deceased be joined in the proceeding, they submitted a reply dated 20/4/70 in which they stated the non existence of any ground justifying their intervention. The present appellant, on her part, argued that if the respondent had paid the proceeds of the policy to ineligible persons without there being any suit against it, it may claim restitution, but cannot in any way be relieved of its liability under the policy.

In its judgment, the High Court stated that Woiz. Yeshimebet is a designated beneficiary of the life insurance policy. On the other hand, the heirs are also entitled to the proceeds of the policy pursuant to Art. 701 of the Commercial Code. But as the Corporation paid the disputed sum not of its own will but in pursuance of the order made by the Addis Ababa Awraja Court dated Tir 29, 1968 and Yekatit 4, 1968 under file No. 2450/67, it should not be held liable for second payment.

The appellant brought an appeal from this judgment of the High Court on Ginbot 29, 1970 alleging that the Insurance Corporation was aware of the fact that the deceased had named her as a specified beneficiary of the policy and that she was in possession of the policy. She was furthermore informed by the Insurance Corporation that payment would be made to her when she established at court that she is the sister of the deceased. She argued that since the respondent is aware of all these, it is unlawfully litigating against her by invoking a legal provision that governs situations in which the beneficiary is not specified in the policy. As regards the contention that payment was made pursuant to the order of the Awraja Court, the appellant argued that since the respondent was aware of the beneficiary specified in the policy, it cannot avoid the obligation on this ground.

The appellant also objected to the judgment of the High Court which had reasoned that the decision of the Awraja Court ordering payment to the heirs was improper, but had nonetheless ruled that appellant should sue the heirs and not the Insurance Corporation.

Counsel for the respondent, in its reply dated Hamle 1, 1970 admitted that it had promised to pay the proceeds of the insurance policy when the heirs establish their right to the inheritance. It argued that although the appellant is a specified beneficiary of the policy, the law also provides that the subscriber's spouse and children are deemed to be specified beneficiaries. The spouse and children of the deceased had established their status as heirs before the appellant did so.

The respondent further argued that the appellant was also the representative of a child of the deceased named Tamirat Engida, but that the Awraja Court had rejected the claims of the appellant in its decision of Tir 5, 1965 (File No. 4311/67). The Awraja Court had also ordered on Tir 29/1967 (File No. 2450/67) that, since the right of the legal heirs of the deceased to the inheritance should not be prejudiced by reason of the loss or non-production of the policy, payment should be made to the legal heirs who are the children of the deceased. Furthermore in the explanation to this decision made on Yekatit 4, 1968 the Awraja Court had ruled that "the Ethiopian Insurance Corporation should effect the payment of the proceeds of the insurance policy in accordance with the earlier decision of the Court" and that this decision should be transmitted to the Corporation, thereby ordering the Corporation to pay the proceeds to the legal heirs. The Corporation therefore alleged that it had paid the proceeds of the policy to the heirs accordingly and that the legal heirs had undertaken to intervene in and litigate any dispute concerning the payment. The respondent therefore argued that even if the appellant were to be deemed as a beneficiary of the policy, she would have a claim only against the heirs, and the judgment of the High Court should be confirmed.

This Court has examined the arguments presented by both parties. That the appellant is a specified beneficiary of the deceased's life insurance policy is not contested. The respondent's argument is based on Art. 701 of the Commercial Code and the order given to it by the Awraja Court. A life insurance policy is a contract between the insurer and the subscriber. The insurer has the duty to perform its obligation in accordance with the policy the beneficiary a specified in the policy. Article 691 of the Commercial Code provides that the proceeds of the policy has to be paid to such specified person. Article 706 of the Commercial Code further rules that the beneficiary may claim directly from the insurer. The appellant's claim is based on these provisions.

The fact that the respondent had requested the Awraja Court to whom it should pay the proceeds of the insurance policy instead of discharging its obligation as set out in the contract shows its lack of good faith in performing the contract. It is established that the appellant has requested payment to be made to her in accordance with the policy. The respondent had also asked her to comply with necessary formalities. Accordingly, the appellant had duly established her status at court. The respondent contended that it had paid the proceeds to the legal heirs in conformity with the order of a court. However, the respondent cannot benefit from an order it had confusingly led the court to make and avoid its responsibility since in a life insurance policy payment is to be made to the beneficiary. The beneficiary in this case is the present appellant, W/o. Yeshimebet Jemaneh.

The Insurance Corporation had to discharge its duties conscientiously, but had failed to do so in this case, even though it was aware of all relevant facts, believing that a court order will relieve it of its obligation. We have therefore reversed the judgment of the High Court which was made without due cognizance to all these factors, and order that respondent should pay the proceeds of the life insurance policy to the appellant.

__Editor's Note__

**Unless stated otherwise, all dates are according to the Ethiopian Calendar.*

<u>የኢሶሰ ጊዐዓ ከፍተኛው ፍርድ ቤት</u>

<u>1ኛ የፍትሐ ብሔር ችሎት</u>

<u>የፍትሐ ብሔር መዝገብ ቁጥር 602/73</u>

ለሞት በሆነ የመድን ውል ተጠቃሚ የሆነ ሰውን ስለመሰየም – የወራሾችና የቀረው ወይም የተፋታ የትዳር ጓደኛ መብት – የመድን ውልን ጥቅም ለሌላ ለማስተላለፍ ወይም ስለማስያዝ – ከመድን ገቢው ሰው መብት የሚተላለፍላቸው ወገኖች – ቀደም ሲል የተሰጡ ፍርዶች በተመሳሳይ ጉዳዮች ስለሚኖራቸው ተፈጻሚነት – አካለ መጠን ያላደረሰን ልጅ መብት ለመጠየቅ ስለሚደረግ ጥረት – በክርክር የግድ ተካፋይ-መሆን ስለአለባቸው ወገኖች – ስለተከራካሪዎች መጣመር የሚሰጥ ትእዛዝ የዳኝነት ፋይከፈል ስለሚከፈት ፋይል የንግድ ሕግ ቁ. 692 (2)፣ 698፣ 701፣ 706፣ 707፣ የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ቁ. 40(2) 467፣

ክርክሩ የተጀመረው ከሳሽዋ የሟቹ የሕይወት መድን ገንዘብ እንዲከፈላቸው በውሉ ላይ የተሰየሙት ስለሆነ ይኸው ታውቆ በሙሉ ይሰጠኝ ብለው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው።

<u>ፍርድ፣ አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም</u>፡–

የመድን ገቢው የትዳር ጓደኛና ልጆች የሕይወት መድን ተጠቃሚዎች ናቸው ተብሎ በንግድ ሕጉ በግልጽ መመልከቱ እነዚህ ሰዎች በመድን ውሉ ከተሰየመው ተጠቃሚ ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ጥቅምት 25 ቀን 1976 ዓ.ም.

ዳኛ አቶ ጥላዬ ተገኝ

ከሳሽ: ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደ ሥላሴ

ተከሳሽ: የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ጣልቃ ገቦች:
1. ወ/ት ሣራ ተክለ ሃይማኖት
2. እነ ወ/ት ምህረት ተክለሃይማኖት

ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ፍርድ ሰጥቷል።

ፍርድ

ከሣሽ ታህሣሥ 27 ቀን 1973 ዓ.ም በተጻፈው ማመልከቻ የሚከተለውን ክስ አቅርበዋል።

የከሣሽ ባለቤት ሟች አቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል በፖሊሲ ቁጥር 30480 አ.ኢ.አ በየካቲት 21 ቀን 1973 ዓ.ም. በተጻፈው የኢንሹራንስ ማመልከቻ ውል እና በመጋቢት 14 ቀን 1973 ዓ.ም. በተጻፈ የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ከተከሣሽ ጋር ተፈራርመዋል።

አቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል ከዋ ብሎ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል የንግድ ቁጥር 660/1/ በሚፈቅደው መሠረት ለአንድ ለተለየ ሰው አድርገውታል። በዚሁ ውል ተራ ቁጥር 15 እንደሚታየው የተጠቃሚው ስም በሚለው ርዕስ ሥር የከሣሽ የወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ ስም በግልፅ ተመዝግቧል።

አቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል ይህን የኢንሹራንስ ውል ከፈረሙ በኋላ በየካቲት 10 ቀን 1971 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ከላይ የተጠቀሰውን ተጠቃሚ፣ ማለት ከሣሽ፣ በኢንሹራንሱ ውል የተደነገገውን ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ተከሣሽ እንዲያስረክባቸው በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ መሠረት ቢጠይቁ ፈቃደኛ ስለአልሆኑ በሕግ ተገዶ እንዲከፍል ይደረግልን የሚል ነው።

የክሱ ማመልከቻ ለተከሣሹ ደርሶት የካቲት 21 ቀን 1973 ዓ.ም በተጻፈው መልስ ላይ እንደሚከተለው ገልጸዋል። በመሠረቱ የከሳሽ ባለቤት ሟች አቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል በፖሊሲ ቁጥር 30480 አ.ኢ.አ. መጋቢት 14 ቀን 1973 ዓ.ም በተጻፈው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ከተከሣሽ ጋር መዋዋላቸው አይካድም። በዚህም መሠረት በፖሊሲው ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ለተጠቃሚዎቹ መክፈል እንዳለበት ድርጅቱ ያምናል።

ነገር ግን በአንድ በኩል ከሣሽ ፖሊሲውንና የንግድ ሕግ አንቀጽ 701/1/ን መሠረት በማድረግ የዋስትናው ገንዘብ በሙሉ እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሟች ወራሾች በዚሁ ሕግ አንቀጽ 701/2/ /ለ/ መሠረት ተለይተን ባንጠቀስም የፖሊሲው ተጠቃሚዎች ነን በማለት የሟች ወራሾች ስለመሆናቸው የአ.አ አውራጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ይዘው ቀርበዋል።

በዚህ ረገድ በተመሣሣይ ጉዳይ ላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ/1133/69 የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለሟች ወራሾች የሰጠውን ክፍያ ያጸደቀው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ/749/70 ከላይ የተሰጠውን የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የመድን ድርጅት ለተጠቀሱት ተጠያቂዎች መክፈል ሲገባው ለወራሾች የከፈለው ያላግባብ ስለሆነ እንደገና ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል። ከዚህም የተነሣ አሁን በተነሣው ጉዳይ ላይ ድርጅቱ ገንዘቡን ለማን መክፈል እንዳለበት ለማወቅ ተቸግሯል።

ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት የፍት/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/40/2/ በሚያዘው መሠረት በዚህ ጉዳይ ላይ የሟች ወራሾች አባሪ ሆነው በነገሩ መግባት ለውሣኔ አሰጣጥ አስፈላጊና አመቺ መሆኑን ተረድቶ በጉዳዩ ውስጥ ተካፋይ እንዲሆኑ እንዲያዝልን እያመለከትን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ባለመብቶቹ ተለይተው ከታወቁ በኋላ እንዲከፈል ገንዘቡን ለፍ/ቤቱ ለማስረከብ ድርጅቱ ፈቃደኛ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል።

ከሣሽ በበኩላቸው ለቀረበው መልስ የመልስ መልስ ከሰጡ በኋላ ፍ/ቤቱ ሰኔ 9 ቀን 1973 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሟች ወራሾች በክሱ ውስጥ እንዲገቡ ብይን ሰጥቷል። ለጣልቃ ገቦች መልስ አሰጣጥ እንዲያመች ተደርጎ ከሣሽ ታህሣሥ 27 ቀን 1973 ዓ.ም. የክስ ማመልከቻ አቅርበዋል። ከመጀመሪያው ክስ ተለይቶ ስለማይታይ ድጋሚ መግለፅ አላስፈለገም።

የክሱ ማመልከቻ ለጣልቃ ገቦች ደርሶ ምህረት ተክለሃይማኖት፣ አማኑኤል ተክለሃይማኖት፣ መዓዛ ተክለሃይማኖት፣ እና ነቢዩ ተክለሃይማኖት በጠበቃቸው አማካይነት ጥር 8 ቀን 1974 ዓ.ም. በጻፉት መልስ ላይ የኢንሹራንስ ገንዘብ እኛ የአባታችን ወራሾች ሆነን ከምንካፈለው የውርስ ሀብት ጋር ግንኙነት እንደሌለው ተረድተን ስለሆነ የፍትሐብሄር ክርክር ምክንያት ከሆነው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ መከፈል ይገባናል ብለን ያልጠየቅን መሆናችንን በትህትና እናመለክታለን ብለዋል።

ማራ ተክለሃይማኖት ግን በወኪል አማካይነት ጥቅምት 8 ቀን 1974 ዓ.ም. በተጻፈው ማመልከቻ የሚከተለውን ክርክር አቅርባለች።

የንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ ከሣሽን ብቻ ተጠቃሚ ስለማያደርጋትና በዚሁ ሕግ ቁጥር 701/2/ለ/ መሠረት የሟች ወራሾች አብረው ተጠቃሚ ስለሆኑ ከሣሽ እንዳቀረበችው ሁሉም የኢንሹራንስ ገንዘብ ሊሰጣት አይገባም በማለት ተከራክራለች።

ከሣሽ የኢንሹራንሱ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ሰፋ ያለ የሕግ ክርክር አቅርበዋል። በአጭሩ ለመጥቀስ ያህል፣

1ኛ. በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ከተጠቀሰው ተጠቃሚ ሌላ ፈራሚው እና ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል ባይፈርሙም መጨመር የተከለከለ በመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 698 ስለሚገልፅ።

2ኛ. የንግድ ሕግ ቁጥር 692 /2/ "ወይም" የሚለውን ቃል መጠቀሱ የተወሰኑ ተጠቃሚዎች ካሉ ከሞያው ለእነሱ ብቻ ይከፈላል ማለቱ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ "ወይም" የሚለው ቃል "እና" ተብሎ በተጻፈ ነበር።

3ኛ. የንግድ ሕግ ቁጥር 706/2/ ለተጠቃሚው የሚከፈለውን ገንዘብ ኢንሹራንስ ከገባ ሰው ውርስ ክፍል አይሆንም ማለቱና በ706 ደግሞ ለባል ወይም ለሚስት የተከፈለው ክፍያ በጋራ ሀብትነት ሳይሆን እንደግል ሀብት የሚቆጠር ነው ማለቱ የሚያስረዳን የሕይወት ዋስትና ኢንሹራንስ በንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ መሠረት ለሚስት ወይም ለባልና ለልጆች እንዲሰጥ የሚደረገው የንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ በደነገገው መሠረት የተለየ ተጠቃሚ የሌለ ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው በማለት ተከራክረዋል።

ግራ ተክለሃይማኖት በበኩሏ በጠበቃቸ አማካይነት ያቀረበችው የሕግ ክርክር እንደሚከተለው ነው።

1ኛ. የንግድ ሕግ ቁጥር 698 የሚገልፀው እንደገንዘብ የሚቆጠረውን የኢንሹራንስ ውል መያዣ ለማድረግ ወይም ለሌላ አሳልፎ ለመስጠት የሚችለው ኢንሹራንስ የገባው ሰው ወይም የእሱ ስምምነት ሲገኝ በሌላ ሰው ሊሆን እንደሚችል ነው።

2ኛ. ከሣሽ የንግድ ሕግ ቁጥር 692/2/ን በመጥቀስ በራሳቸው የሚያስወስን ክርክር አቅርበዋል። ምክንያቱም ኢንሹራንስ የገባ ሰው የሞተ እንደሆነ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ያላቸው ወይም በኢንሹራንስ ውል ውስጥ የተጠቀሰው ተጠቃሚ ጥቅሙን እንደሚያገኝ በመወሰን በአንደኛ ደረጃ ጥቅሙ የሚገባው ኢንሹራንስ ከገባ ሰው መብት ላለው ሲሆን ይህም

ካልተገኘ በሁለተኛ ደረጃ አማራጭ ሆኖ ተቀሙን ለመውሰድ የሚችል ተጠቃሚ ተብሎ ለተጠቀሰው እንደሚሆን የሚገልፅ የሕግ አንቀጽ ነው።

በዚህ በኩል ትክክለኛው የሕጉ መንፈስና ዓላማ ከሌሎች የሕግ ቁጥሮች አፈንግጦ ትርጓሜ ለመፍጠር ሳይሆን በውሉ ላይ እንደተመለከተው ዋናው ተጠቃሚ ተብሎ በውሉ ላይ የሚጠቀስ ሰው በንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ ስማቸው በውሉ ላይ ባይጠቀስም እንደተጠቀሰ ተቆጥሮ ተጠቃሚ ይሆናሉ የተባሉትን በመጨመር እኩል እንደሚካፈሉ ነው።

3ኛ. የንግድ ሕግ ቁጥር 666 እና 707 የሚወስኑት ተጠቃሚ ማነው የሚለውን ሳይሆን ተጠቃሚው ተቀሙን እንዴት እንደሚወስድ በመሆኑ እነዚህ አንቀጾች በተከሣሽ የተጠቀሱት አላግባብ ነው በማለት የሕግ ክርክሩን ካረመች በኋላ በአንቀጽ 701/2/ /ለ/ መሠረት ድርሻዋ እንዲከፈላት ጠይቃለች።

ከዚህም ሌላ የጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በይግባኝ መ/ቁ/749/70 በተመሣሣይ ጉዳይ ላይ የኢንሹራንስ ክፍያ የሚከፈለው በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ተጠቃሚ ተብሎ ለተገለፀው ሰው ብቻ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ኢንሹራንስ አትርፎ ለማስረጃነት አያይዛለች።

የግራ ቀኙ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር እንዲሁም ያቀረቡት ማስረጃ በአጭሩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም ጉዳዩን እንደሚከተለው ይመረምራል።

በመጀመሪያ ግራ ቀኙ ያቀረቧቸው የሕግ አንቀጾች ክርክሮች በመመልከት ፍ/ቤቱ ትርጉም ይሰጥባቸዋል።

1ኛ. የንግድ ሕግ አንቀጽ 698፥

በዚህ የሕግ አንቀጽ መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው በጽሁፍ ካልተስማማ በስተቀር የኢንሹራንስ ውል ለሌላ ለማዛወር፥ በውሉ ውስጥ ተገልጾ የተመለከተውን ተጠቃሚ መለወጥ እንደማይችል ተደንግጓል። አንቀጹ ራሱ በግልጽ እንደሚያስረዳው ውሉ ኢንሹራንስ የገባው ሰው በኢንሹራንስ ፖሊሲው ውል ላይ ተጠቃሚ አድርጎ

ያስመዘገበው ሰው ኢንሹራንስ አድራጊው ሳይፈቅድ ሊለወጥ ወይም ሊተካ እንደማይችል ነው።

አሁን የተያዘውን ጉዳይ ብንመለከተው የቀረበው ክርክር በኢንሹራንሱ ፖሊሲው ላይ ተጠቃሚ ሆኖ በሟች የተመዘገበችው ወ/ሮ ጽጌረዳ በሌላ ሰው ትለወጥ ወይም ትተካ የሚል ስለአልሆነና የሟሊቃ ገቦች ተያቱ ሕግ በፈቀደልን መሠረት እኛም ድርሻችንን እናገኛ የሚል በመሆኑ ይህ አንቀጽ 698 ለዚህ ክርክር ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

2ኛ. አንቀጽ 692 /2/

በዚህ አንቀጽ መሠረት ኢንሹራንስ ሰጭው የተዋዋለው ኢንሹራንስ ስለገባው ሰው ሞት የሆነ እንደሆነ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸው "ወይም" በኢንሹራንስ ውል ውስጥ ለተጠቀሰው ተጠቃሚ የተወሰነ ዋና ገንዘብ ይከፍላል ይላል።

"ወይም" የሚለው ቃል በአንቀጽ 701 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተገለጹትን ተጠቃሚዎች የኢንሹራንስ ገንዘቡን በአንድ ላይ እንደሚወስዱ የሚያደርግ ሳይሆን በአማራጭ እንዲከፈል የሚያደርግ ነው የሚለው የከሣሽ ክርክር ሕጉ በዚህ አገባብ ይተርጎም ቢባል እንኳን በዚህ ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ተጠቃሚ የሆኑት ወራሾች የተባሉት እንጂ ከሣሽ አትሆንም ማለት ነው። ስለዚህም ከሣሽ የንግድ ሕግ ቁጥር 692/2 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ለከሣሽ የቅድሚያ ብቻዋ መብት ያላት ስለሚያደርግ በዚህ ላይ የቀረበውን የከሣሽ ተቃውሞ አልተቀበልነውም።

3ኛ. ስለ አንቀጽ 706 እና 707፡

በአንቀጽ 706/2/ ላይ የተገለጸው ለተጠቃሚው የሚከፈለው ገንዘብ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው ውርስ ክፍል አይሆንም የሚል ነው። አሁን በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ክርክር ለሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚው ማነው? የሚለው እንጂ ለተጠቃሚው የተከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ የውርስ ክፍል ነው ወይስ አይደለም? የሚል ባለመሆኑ እንዲሁም አንቀጽ 707 የሚገልጸው ለተጠቃሚው የሚከፈለው ገንዘብ ለውርሱ ተመልሶ እንዲገባ ወይም ከድርሻው ላይ ተቀናሽ ሊሆን እንደማይችል ብቻ የሚገልጽ በመሆኑ ፍ/ቤቱ እንደመረመረው የንግድ ሕግ ቁጥር 706 እና 707 ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ

ግንኙነት ያላቸው ሆኖ ስላላገኘናቸው በዚህ ነጥብ ላይ ከግሽ ያቀረብናቸውን ጥያቄ አልተቀበልነውም።

4ኛ. የጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የኢንሹራንስ ገንዘብ በውሉ ላይ ለተጠቀሰው ብቻ ነው የሚከፈል በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬሰደንስ ሕግ በግድ ተፈጻሚ ስለአልሆነ ይህ ፍ/ቤት ለራሱ ሕጉ የደነገገውን በመመርመር የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።

በዚህም መሠረት ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለውን አንቀጽ 701/ እንመለከታለን። አንቀጽ 701 በርዕሱ ላይ ለሞት በሆነ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ይልና እነዚህ እነማን እንደሆኑ ከንዑስ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ይገልጻቸዋል።

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሆነ የንግድ ሕግ አንድ አንቀጽ ሥር የሚዘረዘሩ ንዑስ ቁጥሮች ወይም /or/ የሚል ቃል እየተጻፈባቸው በአማራጭ /alternatively/ ይቀርባሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እና /and/ የሚል ተጽፎ በድምሩ ማለት /cumulatively/ ይቀርባሉ። በአማራጭ የሚቀርቡ ከሆነ በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ የተጠቀሰው ባለመብት ወይም ባለእዳ የሚሆነው በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሰው ሳይኖር ሲሆን በድምሩ የሚቀርቡት ግን በንዑስ ቁጥሮች በሙሉ የተጠቀሱት በአንድ ላይ ባለመብት ወይም ባለእዳ መሆናቸውን ያሳያል።

በንግድ ሕግ ቁጥር 70ሐ ላይ በተገለጹት ንዑስ ቁጥሮች ላይ ግን ከላይ እንደገለጽነው በአማራጭ ወይም በድምሩ እንደሚጻፉት አንቀጾች ሆኖ በግልጽ የተደነገገ አይደለም። "ወይም" እንዲሁም "እና" የሚሉ ቃላት አልተጻፉበትም። ስለዚህም የተለያዩ ችሎቶች ይህን አንቀጽ በአማራጭ ወይም በድምሩ እያደረጉ እንዲተረጉሙ አድርጓቸዋል። በዚህ ፍ/ቤት አተረጓጎም ግን፥

1ኛ. አንቀጽ 701 በርዕሱ ላይ የሚገልጸው ለሞት በሆነ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በእንግሊዝኛው /beneficiary of Insurance Policy/ ስለሚልና እነዚህ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ ከታች በተዘረዘሩት 3 ንዑስ አንቀጾች ስለሚገልጽ፥

2ኛ. የአንቀጹ ንዑስ ቁጥር 1 ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ሊደረግ እንደሚቻል የሚገልጽ እንጂ የተለየ ተጠቃሚ የግድ መኖር አለበት ስለማይል፣ የተለየ ተጠቃሚው ሊገለጽም የኢንሹራንሱን ገንዘብ ለብቻው ይወስዳል የሚያሰኝ ግልጽ ድንጋጌ ባለመሆኑና፣

3ኛ. በንዑስ ቁጥር 2 ላይ ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም የሚለው ሐረግ ከንዑስ ቁጥር 1 ጋር አብሮ ሲነበብ ባል፣ ሚስትና በጊዜው የተወለዱት ልጆች በሕግ አማካይነት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ያሳያል።

በዚህ ፍ/ቤት እምነት የአንቀጽ 701/1/ አላማ ኢንሹራንስ የገባው ሰው ሕግ ተጠቃሚ ካደረጋቸው ሰዎች ሌላ የሚፈልገውን ማንኛውንም ሰው በውል ተጠቃሚ ሊያደርገው እንደሚችል መብት ለመስጠት እንጂ በንዑስ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ተጠቃሚዎች ከጥቅሙ ተካፋይ እንዳይሆኑ ለማድረግ አይደለም። ይህንንም የሚያጠናክረው "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም" የሚለው ሐረግ ይሆናል።

በሌላ በኩል በንዑስ ቁጥር 2 ላይ የሕግ ተጠቃሚ ናቸው የተባሉት ባል፣ ሚስት፣ እና ልጆች መሆናቸው ምንም እንኳን የኢንሹራንስ ገንዘብ የውርስ አካል ባይሆንም በተለይ ለሟች ቅርብ የሆኑ ዘመዶችና በሱ የቅርብ ጥገኝነት የሚኖሩት ግን በሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለመግለጽ የተደረገ ሆኖ እናገኘዋለን። በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ወራሽ ወደታችና ወደላይ የሚቆጠሩ ሌሎች ግለሰቦችንም ሊያቅፍ የሚችልበት ሁኔታ አለ። በኢንሹራንስ የሕይወት ዋስ ተጠቃሚ የተደረጉት ግን ተለይተው ከላይ የገለጽናቸው ባል፣ ሚስትና ልጆች መሆናቸው እነዚህ ግለሰቦች በውል ተጠቃሚ ተብሎ ከተመዘገበው ጋር አብረው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን ያሳያል።

ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ የሟች የአቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል የሕይወት ኢንሹራንስ በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ለተጠቀሰችው ግለሰብ /በአንቀጽ 701/1/ እና በአንቀጽ 701/2/ የተገለፁት ግለሰቦች በአንድ ላይ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ፈርደናል።

በዚህ መዝገብ ላይ እነ ወ/ት ምህረት ተክለሃይማኖት በሰጡት መልስ ላይ ይህን የሕይወት ኢንሹራንስ እንደማይፈልጉት ገልፀው ጽፈዋል። ከተደረገው የቃል ክርክርና

ከመዝገቡ አጠቃላይ ይዘት እንደተረዳነው እነ ወ/ት ምህረት ይህንን መሰል የዳቶት በውል ተጠቃሚ የሆኑቸው ከግኝ እናታቸው በመሆንም እሷን ለመጥቀም ከሌላ የተወለደችውን ግራ ተከላካዮማናትን ለመጉዳት ያሰቡት እንጂ በእርግጥ መብታቸውን ለመተው ያሰቡ ሆኖ አላገኘነውም። ምንም እንኳን እነርሱ ሕግና በመሆናቸው መልሱን ያዘጋጀው ሌላ ቢሆንም፡-

1. እንደዚሁ ዓይነት ክርክር ቀን ለበና የነደለው በለሆኑ፤
2. በዚሁ መነሻነት እነዚህ ሕፃናት መብታቸውን እንዲያጡ ሊያደርግ የሚችል "እኔ ትርጓሜ ዘንድ አልሆ" እንደተባለው ችግር የሚያስከትልም በመሆኑ ይህንን መሰል ዓቀረቡት አወደዶት ትምህርት እንዲሆናቸው ፍ/ቤት በዚሁ አጋጣሚ ተገቢ ይሰጣል።

ሌላው ይህን መዝገብ የተለየ የሚያደርገው ደግሞ በንዑስ ቁጥር 1 ተጠቃሚ ተብላ የተመዘገበችው በንዑስ ቁጥር 2 ላይም በሕግ ተጠቃሚ ነች የተባለችው የሟች ሚስት ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ በመሆኑ በክፍፍሉ የሚደርሳት ምን ያህል ነው? የሚለው የሆናል።

በመሠረቱ ከላይ እንደገለፅነው ሁሉ በንዑስ ቁጥር 1 ላይ ኢንሹራንስ የገባው ሰው በራሱ ፈቃድ የመረጠውን ሰው ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችልበት መብት በመሆኑ ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴን ስለመረጠ ወ/ሮ ጽጌረዳ በንዑስ ቁጥር አንድ እንዲሁም በሕግ ደግሞ በንዑስ ቁጥር ሁለት ተጠቃሚ ነች ማለት ነው።

ከሟች ልጆች መካከል ወጣት ነቢዩ ተከላካዮማናት የኢንሹራንሱ ውል በተፈጸመበት ጊዜ ያልተወለደ ስለነበር በሕንቀጽ 701/2/ለ/ መሠረት ተጠቃሚ አይደለም ማለት ነው።

ስለዚህም በውሉ መሠረት መከፈል ያለበት ሃያ ሺ ብር ለሶስቱ ተጠቃሚዎች እኩል ተከፍሎ፤

1ኛ. ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ በሕንቀጽ 701/1/ መሠረት፤ ብር 3,333.03
2ኛ. ለወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ እንደገና በሕንቀጽ 701/2/ሀ/ መሠረት፤ ብር 3,333.03

3. ለወ/ት ማሬ ተክለሃይማኖት ብር 3,333.03
4. ለወ/ት ምፀረት ተክለሃይማኖት ብር 3,333.03
5. ለወጣት አማኑኤል ተክለሃይማኖት ብር 3,333.03
6. ለወጣት መአዛ ተክለሃይማኖት ብር 3,333.03

እንዲከፈል በማለት ፈርደናል።

ከተራ ቁጥር 3-6 ያሉት ተጠቃሚዎች ግን የዳኝነት ስለአልከፈሉ ትዕዛዝ ወጪ ከመሆኑ በፊት የዳኝነት ሂሣብ ያስገቡ። ይህ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሬጂስትራር ይገለፅላቸው።

ማንኛውንም ወጪና ኪሣራ ሁሉም ለእየራሳቸው ይቻቻሉ። መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

በአዳሬ ሲሰራ ቆይቶ የከሣሽ ጠበቃ በተገኘበት ዛሬ ኅዳር 5 ቀን 1976 ዓ.ም. በችሎት ተነቦአል።

<u>The High Court of Addis Ababa</u>
<u>First Civil Division</u>

<u>Civil Case No. 602/73</u>

Designation of beneficiaries in a life insurance policy for the event of death - Rights of heirs and the surviving spouse - Assignment or pledge of proceeds of a life insurance policy - Persons having rights from the insured - Application of the rule "stare decisis" - Consideration of the best interests of minors - indispensable parties - mandatary joinder of parties - Suits by paupers. Comm. C. Arts. (692(2), 698, 701, 706, 707 Civ. Prov. C. Arts. 40(2), 467.

Action by a designated beneficiary to be entitled to the whole proceeds of a life insurance policy.

Held: Action dismissed.

The fact that the spouse and children of an insured person have been expressly included in the Commercial Code of Ethiopia as beneficiaries of a life insurance policy shows that they are equally entitled to the proceeds together with the designated beneficiary.

Tikemt 25, 1976*

Judge:	Ato Tilaye Tegegn
Plaintiff:	Wro. Tisgereda Wolde Selassie
Defendant:	The Ethiopian Insurance Corporation
Intervenors:	1. Wrt. Sara Tekle Haimanot
	2. Wrt. Mehret Tekle Haimant et. al.

The court renders the following judgment after examining the case at hand.

<u>Judgment</u>

In her statement of claim dated Tahssas 27, 1973, plaintiff pleaded that:

On the basis of the request contained in a letter dated Yekatit 21, 1973, a life insurance policy No. 30480 was signed between her late husband Ato Tekle Haimanot Wolde Gabriel and the Defendant on Megabit 14, 1973;

The insured designated her as the beneficiary of the policy under item 15 in accordance with Art. 660(1) of the Commercial Code of Ethiopia;

The defendant refused to pay the agreed sum in the policy, i.e., Birr 20,000 (twenty thousand) when she claimed it after the deceased passed away on Yekatit 10, 1974; and prayed that the defendant be ordered to effect payment of the sum in the policy as per Art. 706(1) of the Commercial Code.

When summon was served on the defendant, it presented a statement of defence dated Yekatit 21, 1973 and admitted its liability on the policy under consideration.

The defendant, however, argued:
While plaintiff claims the whole sum on the basis of the policy and Art. 701(1) of the Commercial Code, the heirs of the deceased, who have produced a duly probated certificate of heirship from the Addis Ababa Awraja Court, contend that they should benefit from the proceeds of the policy according to Art. 701(2) (b) of the Code;

In a similar case the High Court affirmed the payment the Corporation made to the heirs of another insured under Civil Case No.1133/69 while the Supreme Court quashed the judgment under Civil Appeal Case No., 749/70 and ordered it to pay the sum stated in that policy for the second time to the designated beneficiaries.

Accordingly, defendant pleaded that the heirs of the deceased be joined in this proceeding as indispensable parties under Art. 40(2) of the Civil Procedure Code, as it is confused as to whom it should pay. It further expressed its willingness to deposit the sum in the policy with this court so that payment be effected when the beneficiaries are ascertained.

After the plaintiff gave her reply to this argument, this court ruled, on Sene 9, 1973, that the heirs of the deceased be parties to the proceeding. The amended statement of claim, which was no different in substance from the initial one, was served on the intervenors.

Four of them namely Mehret Tekle Haimanot, Amanuel Tekle Haimanot, Meaza Tekle Haimanot and Nebiyu Tekle Haimanot submitted a reply on Tir 9, 1974. In this reply written by their attorney they disclosed that they do not claim the sum under litigation because they have now learned the proceeds of the insurance policy does not constitute part of the estate of their father.

The other heiress, Sarra Tekle Haimanot, however, brought a different argument in a statement written by her pleader on Tikemt 8, 1974. She stated that Art. 701(1) of the Commercial Code does not entitle the plaintiff to be the sole beneficiary because the subscriber's heirs are equally entitled under sub article 3.

The plaintiff, who claims full payment, presented extensive legal arguments, including:

1. It is not possible to specify any beneficiary in addition to the ones designated in the policy without the consent of the subscriber, Ato Tekle Haimanot Wolde Garbriel, and this is stated under Art. 698 of the Commercial Code.

2. The word "or" in Art. 692(2) of the Commercial Code implies that if there are designated beneficiaries, payment should only be effected to them - otherwise, the word "or" should have been "and".

3. The statement that says the sum to be paid to a specified beneficiary shall not form part of the insured person's estate under Art. 706(2) of the Commercial Code and further the other statement that reads the sum to be paid to the subscriber's spouse is to be regarded as the personal property of the spouse in Art. 706(3), show that the benefit from a life insurance policy must be given to the spouse or children in accordance with Art. 701(2), provided no beneficiary is designated in the policy as per Art. 701(2).

Through her lawyer, Sarra Tekle Haimanot, on her part, responded to this argument in the following manner.

1. What Art. 698 of the Commercial Code provides is that only the insured himself or one who obtains his consent may assign or pledge the insurance policy which is treated as money. Also, with the exception of Nebiyu, as no other beneficiary was added than those stated under item 15 of the policy in line with Art. 701 of the Code, the plaintiff is wrong in citing Art. 698.

2. The plaintiff has presented an argument that would defeat her claim by citing Art. 692(2) of the Commercial Code. This is because the provision provides that when the insured dies the insurer should pay a specified capital or life interest to those having rights from the insured or in the event of their non-appearance to the beneficiary named in the policy.

> The true spirit and purpose of the law, in this respect, is not to derogate from, and contradict the other provisions of the law, but rather, to enable the person designated as the main beneficiary to share the precedes of the policy equally with those envisaged by Art. 701(2), notwithstanding that they are not mentioned in the policy.

The Insurance Corporation also produced copy of a decision rendered by the First Division of the Supreme Court in which it was held that the Corporation pay proceeds of an insurance policy to a designated beneficiary under Civil Appeal Case No. 749/70.

In light of these facts, legal arguments and the evidence presented, this Court shall now examine the case as follows:

It will first provide interpretation on the legal provisions cited by the parties.

Art. 698 of the Commercial Code

In this provision, it is stated that an assignment, or endorsement of an insurance policy or changing the beneficiary named in the policy is of no effect unless the insured person agrees in writing. The provision makes clear that it is not possible to replace or change the person specified as the beneficiary without the consent of the insured.

In the case at hand, since the claimant does not demand that Wro. Tsigereda, the specified beneficiary of the insurance policy, be changed or replaced by another person, and since the request of the intervenors is to get their share in accordance with the law, we have not found this provision to have a direct relevance to the case.

Art. 692(2)

This provision states that if the insurer has entered into a contract for the event of death of the insured, the insurer shall pay the specified money to those that have rights from the insured person or to the beneficiary named in the insurance policy.

The plaintiff argued that the term "or" does not imply that the persons mentioned in Art. 701(1) and (2) would jointly receive the money but it rather gives the option to make payment to one of them. If it is decided to interpret the law based on such argument, it would be the heirs that would be the primary beneficiaries and not the plaintiff. Therefore,this argument presented by the plaintiff by invoking

Art. 692(2) of the Commercial Code is not tenable and is thus rejected, because it would not make the plaintiff the sole beneficiary.

Articles 706 and 707

Art 706(2) states that the money to be paid to the beneficiary shall not form part of the insured person's estate. Since the issue in this case is who the beneficiary of the life insurance policy is and not whether the insurance money constitutes part of the estate, and, furthermore, since Art. 707 provides that the money to be paid to the beneficiary cannot be refunded to the estate and cannot be deducted from his share, the court, holds that these provisions have no relevance to the case and on this point we have thus rejected the plaintiff's claim.

Even if the Supreme Court has held that the insurance money should only be paid to the designated beneficiary, this court cannot be bound by such decision as the Ethiopian legal system does not follow the system of precedence. Accordingly, it renders its own decision by interpre'ng the law.

The provision that is directly relevant to the case at hand is Art. 701 of the Commercial Code. The Article, captioned as "beneficiary of insurance policy", enumerates who such beneficiaries are in sub-articles 1 and 2.

In the Civil and Commercial Code of Ethiopia some sub-articles are alternatively listed under an article by using the word "or". Others are cumulatively listed using the word "and". If the provisions are listed alternatively, it is only in default of the creditor or debtor in sub-article 1 that the person mentioned in sub-article 2 will take the place of a creditor or debtor; while in provisions that are listed cumulatively, persons mentioned in both sub-articles shall jointly be creditors or debtors.

But the sub-articles of Art. 701 of the Commercial Code have not been listed in the alternative or cumulative as mentioned above. The words "and" or "or" have not been used. Therefore, various courts have interpreted this provision either in the alternative or in the cumulative.

This court would interpret it in the following manner:

1. The heading of Art. 701 is "beneficiary of insurance" and it describes the beneficiaries in its three subsequent sub-articles;

2. The fact that sub-article 1 of this article provides that the insurance policy in the event of death may be made for the benefit of a specified beneficiary does not make it a mandatory requirement that there should always be a specified beneficiary, and even when there is a specified beneficiary, the provision does not clearly state that such person shall be the sole beneficiary of the insurance policy; and

3. The phrase "notwithstanding that they are not mentioned by name" in sub-art. 2 cum sub-article 1, shows that the spouse and children are made beneficiaries by law.

In the opinion of this court, the purpose of Art. 701(1) is to give a right to the insured person to add other beneficiaries he wants, in addition to those who are beneficiaries by law; it does not exclude those beneficiaries mentioned in sub-article 2 from sharing the proceeds. This interpretation is further strengthened by the phrase, "notwithstanding that they are not mentioned by name."

On the other hand, even if proceeds of an insurance policy does not form part of the inheritance claim, the fact that the spouse and children are made beneficiaries by virtue of sub-article 2 helps us to determine that the law wants close relatives of a deceased person and those who are mentioned by him in the policy to be beneficiaries of such a policy. According to the Civil Code, other descendants and ascendants could be heirs. But the fact that the spouse and children have been expressly included as beneficiaries of the life insurance shows that these persons shall be deemed to be beneficiaries together with the person that is specified in the policy.

Therefore, in this case, we hold that the life insurance of the deceased, Ato Teklehaymanot Wolde Gebriel, shall be paid to the person whose name is specified in the policy in accordance with Art. 701(1) and to those persons specified in Art. 701(2).

The file shows that Wrt. Mihret Tekle Haymanot et.al. do not want to share proceeds of this insurance policy. From the oral litigation and the contents of the file of this case, we have come to realize that they have given such response in order to support their mother who, as a beneficiary specified in the policy, was litigating against Sara T/Haymanot who is born from a different mother. However, we do not think that they intend to renounce their right. Since the reply was prepared for them by some one else for they are minors:

1. It is evident that such argument lacks good faith; and

2. Because of this argument an unwanted consequence could have resulted whereby the children might have lost the benefit of the insurance; therefore the court wishes to caution those who prepared the reply to refrain from such conduct in the future.

Another point that makes this case unique is the issue of how much the deceased's wife, Woizero Tsigered a Woldeselassie, will get considering that she is the specified beneficiary in accordance with sub-article 1 of Art. 701 of the Commercial Code, and she is also a beneficiary under sub-article 2 of same Article.

As stated above, since sub-article 1 allows the insured person to specify any person he wishes, and Woizero Tsigereda W/Selassie has been specified under this provision, this makes her a beneficiary; furthermore, by virtue of sub-article 2, she is also made a beneficiary.

One of the children of the deceased, Nebiyou T/Haimant, was not born at the time the insurance policy was signed. Thus in pursuance of Art. 701(2) (b) of the Commercial Code, he is not deemed to be a beneficiary.

Therefore, we hold that the 20,000 Birr that is payable under the insurance policy shall be divided among the six beneficiaries as follows:

1.	Woizero Tsigereda W/Selassie, pursuant to Art. 701(1)	Birr 3,333.03
2.	Again W/O Tsigered W/Selassie, pursuant to Art. 701(2) (a)	Birr 3,333.03
3.	Woizerit Sara T/Haymanot	Birr 3,333.03
4.	Woizerit Mihret T/Haymanot	Birr 3,333.03
5.	Amanuel T/Haymanot	Birr 3,333.03
6.	Meaza T/Haymanot	Birr 3,333.03

As the beneficiaries listed from number 3-6 have not paid court fees, they should pay it before an execution order is given. Let this be communicated to the High Court's Registrar.

All costs of the proceedings shall be paid by each party. Let this file be returned to the archives.

Editor's Note

**Unless stated otherwise, all dates are according to the Ethiopian Calendar.*

***The Amharic and English versions of art. 701(2) (b) of the Commercial Code are not the same. The English version makes all children beneficiaries whether or not born at the time the insurance policy was signed; on the other hand, the Amharic version provides that only those who were born at the time of the signing of the policy shall be beneficiaries.*

ጠቅላይ ፍርድ ቤት
1ኛ የፍትሐ ብሔር ችሎት

የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 677/76

ለሞት በሆነ የመድን ውል ተጠቃሚ የሆነ ሰውን ስለመሰየም፣ የቀረው ወይም የቀረች የትዳር ጓደኛና የወራሾች መብት፣ የሕይወት መድን ውል ዓላማ፣ ቀደም ሲል የተሰጠ ፍርዶች በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በመጠኑም ቢሆን የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፣ እስከ መጠን ባላደረሰ ልጅና በሞግዚቱ መሀል የሚፈጠር የጥቅም ግጭት፣ ሞግዚትና አሳዳሪ ስለምትነሳበት ሁኔታ የአቤቱታ ጽሁፍን ስለማሻሻል በይግባኝ ስለሚነሱ አዲስ የክርክር ጭብጦች፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 827(2) የንግድ ሕግ ቁጥር 691፣ 692፣ 695፣ 701፣ 705 – 708፣ የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 91፣ 329፣

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይ በሟች የመድን ውል ላይ በስም የተጠቀሰ ተጠቃሚ ብትሆንም የመድን ገንዘቡን ብቻዋን መውሰድ አይገባትም ብሎ በመፍረዱ የቀረበ ይግባኝ ነው።

ውሳኔ፣ ፍርዱ ተሻሽሏል።

የሕይወት መድን ውል ሁለት ዓላማዎች ያሉት ነው።

1. መድን ሰጭው ለመድን ተቀባዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብን ለመክፈል ግዴታ የገባበት ነው።

2. መድን ተቀባዩ በሕይወት ከሌለ ደግሞ ገንዘቡ የሚከፈለው ከዚህ ሰው መብት ለሚተላለፍላቸው ወገኖች ወይም በመድን ውሉ ተለይቶ ለተሰየመው ሰው ነው።

መድን ገቢው ለፈለገው ስጦታ ማድረግ እንደሚችል ሁሉ በመድን ውሉም የፈቀደውን ሰው ተጠቃሚ አድርጎ ለመሰየም ይችላል። አንድ ጊዜ ይህን ካደረገ የመድኑ ገንዘብ ሊከፈል የሚገባው በስም ተለይቶ ለተጠቀሰው ተጠቃሚ ነው። በሕይወት ያለው ወይም ያለችው የትዳር ጓደኛና የሟች ልጆች ይህን ገንዘብ መጠየቅ የሚችሉት የተለየ ሰው በመድን ውሉ ተጠቃሚ ነው ተብሎ ባልተመለከተበት ጊዜ ብቻ ነው።

ሰኔ 28 ቀን 1976 ዓ.ም

ዳኞች: አቶ ጌታቸው አጥራሉ
አቶ ደምሴ ያደቴ
ወ/ት ራሄል ዓለማሁ

ይግባኝ ባይ ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደ ሥላሴ

መልስ ሰጭዎች: 1. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
2. ሣራ ተክለ ሃይማኖት
3. ምሕረት ተክለ ሃይማኖት
4. አማኑኤል ተክለ ሃይማኖት
5. መዓዛ ተክለ ሃይማኖት
6. ነቢዩ ተክለ ሃይማኖት

መዝገቡ ያደረው መርምሮ ባስፈላጊው ለመሥራት ነው። መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

ለዚህ ይግባኝ መቅረብ ምክንያት የሆነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 602/73 ኅዳር 5 ቀን 1976 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ባይ ታኅሣሥ 25 ቀን 1976 ዓ.ም. የተጻፈ የይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው።

መልስ ሰጪ ባለበት ለማጣራት እንዲቀርብ ታዞ ቀርቦ 1ኛው መልስ ሰጪ መጋቢት 17 ቀን 1978 ዓ.ም. የተጻፈ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ መልስ ሰጪዎች ነገረ ፈጅ መጋቢት 17 ቀን 1976 ዓ.ም እና መጋቢት 24 ቀን 1976 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ ሰጥተዋል።

ይግባኝ ባይም ሚያዝያ 4 ቀን 1976 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የክርክሩ ሁኔታ የሟቹ የአቶ ተክለሐይማኖት ወልደገብርኤል የኢንሹራንስ ገንዘብ ለኔ ይገባል ለኔ ይገባል በመባባል ነው።

የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዳየነው ሟች ተጠቃሚውን ለይቶ በግል የሰጠውን ኢንሹራንስ በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ መሠረት በግል ተጠቃሚ ነኝ በማለት ያቀረቡትን ክርክር ሰፋ ያለ ትችት ሰጥቶ በዚው አንቀጽ በንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ተጠቃሚ ናቸው የሚባሉት ባል፣ ሚስት፣ እና ልጆች መሆናቸውን ገልጾ ምንም እንኳ የኢንሹራንስ ገንዘብ የውርስ አካል ባይሆንም በተለይ ለሟቹ ቅርብ የሆኑ ዘመዶችና በሱ የቅርብ ግንኙነት የሚኖሩት ግን በሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለመግለጽ የተደረገ ሆኖ እናገኘዋለን። በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ወራሽ ወደታችና ወደላይ ሌሎች ግለሰቦችንም ሊያቅፍ የሚችልበት ሁኔታ አለ። በኢንሹራንስ የሕይወት ካሣ ተጠቃሚ የተደረጉት ግን ተለይተው ከላይ የገለጽናቸው ባል፣ ሚስትና ልጆች በመሆናቸው እነዚህ ግለሰቦች በውል ተጠቃሚ ተብሎ ከተመዘገበው ጋር አብረው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን ያሳያል ሲል ዘርዘር ባለሁኔታ ትርጉም ሰጥቶ በንግዱ ሕግ ቁጥር 701/1/ እና /2/ መሠረት ያቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል የሕይወት ኢንሹራንስ በውሉ ላይ ለተጠቀሱት በአንድ ላይ ሊከፈላቸው ይገባል ሲል ፈርዷል።

ከዚህም አያይዞ እነ ወይዘሪት ምህረት ተክለሃይማኖት ከሰጡት መልስ ላይ የሕይወት ኢንሹራንሱን እንደማይፈልጉ ገልጸዋል ተብሎ የቀረበው ክርክር ይህን መልስ የጻፉት በውሉ ተጠቃሚ የሆኑቸው ከሣሽ እናታቸው በመሆኑዋን እሷን ለመጥቀም ከሌላ የተወለደቻቸውን ሣራ ተክለሃይማኖትን ለመጉዳት ያሰቡት እንጂ በእርግጥ መብታቸውን ለመተው ያሰቡ ሆኖ አላገኘነውም። ምንም እንኳ እነርሱ ሕፃናት በመሆናቸውና መልሱን ያዘጋጀው ሌላ ቢሆንም 1. እንዲህ ዓይነት ክርክር ቅን ልቦና የጎደለው ስለሆነ፣ 2. በዚህ መነሻነት እነዚህ ሕፃናት መብታቸውን ሊያጡ አይችሉም የሚል አስተያየት አክሎ ሚስት ወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ ከኢንሹራንሱ ብር 20,000 ውስጥ እንደ አንድ ልጅ ተቆጥራ ከሌሎች አምስት ልጆች ጋር ለእያንዳንዳቸው ብር 3,333.33 እንዲከፋፈሉ ፈርዷል። ይግባኝ ተብሎ የቀረበው ይህንን ፍርድ ለማሻር ነው። የይግባኝ ባይ ነገረ ፈጅ ባቀረቡት ቅሬታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ሥር የተጻፉትን 1ኛ ንዑስ ቁጥር እና 2ኛ ንዑስ ቁጥር እንደ አንድ ንዑስ ቁጥር አድርጎ በመውሰድ የተሳሳተ ትርጉም ሰጥቷል።

በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ሥር የተጻፉት ሁለት ንዑስ ቁጥሮች እያንዳንዳቸው የተለዩ አላማ ያላቸውና ስለሁለት የማይገናኙ የኢንሹራንስ ገንዘብ ክፍያዎች መምሪያና መሠረት የሆኑ ንዑስ ቁጥሮች መሆናቸውን ዘርዘር ባለ ሁኔታ ገልጸው የንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/2/ን ከንግድ ሕግ ቁጥር 706 - 705 የተመለከተውን ጠቅሰው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከህጉ ዓላማ ውጭ ተርጉሞ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ 20,000 ብር በንግድ ቁጥር 706 መሠረት በኢንሹራንስ ውል ዋና ተጠቃሚ ሆነው ለተመዘገቡት ለወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ ብቻ ይከፈላል ተብሎ እንዲፈረድ ጠይቀዋል።

መልስ ሰጭዎችም ማለት 1ኛው መልስ ሰጭ የኢንሹራንሱ ነገረ ፈጅ ባቀረበው መከላከያ በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንዑስ ቁጥር 1እና 2 መካከል ልዩነት ስላለና ብዙውን ጊዜ በፍርድ ቤቶች ውዝግብ የፈጠረብን ከመሆኑም በላይ በተለይም ለዚህ ጉዳይ ተመሳሳይ በሆነ ክርክር የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈረደው በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽሮ ሁለት ጊዜ በመክፈል ብር 60,000 ኪሣራ ደርሷል። ፍርድ ቤቱ ለህጉ ትርጉም በመስጠት ለሟች ባለቤት ወይም ለልጆችቻው ለማን እንደምንከፍል ተገምግሞ ይወሰን የሚል ሲሆን ከዚህም አያይዞ ኢንሹራንስ ገቢው በተስማሙበት ፕሪሚየም ክፍያቸው መሠረት ሊከፈል የሚገባው ብር 15,625 ሲሆን ኢንሹራንስ ገቢው የተስማሙበት ተዘንግቶ በብር 20,000 የተቀበልነው በስህተት ነው በማለት በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 345 ማስረጃ ለማቅረብ ጠይቀዋል።

የ5ቱ መልስ ሰጭዎች ነገረ ፈጅ ባቀረቡት ይግባኝ መከላከያ መልስ ደግሞ ቀደም ብሎ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር የተለየ የሚያቀርቡት ክርክር ያለመኖሩን ጠቅሰው በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 827/2/ መሠረት በኢንሹራንስ ውል ውስጥ የገንዘብ ተጠቃሚ ሆኖ ስሙ ተለይቶ የተመዘገበ ካለ በንግድ ሕግ ቁጥር 706 ስለተጠቃሚው መብት በንዑስ ቁጥር 2 ሥር ለተጠቃሚው የሚከፈለው ገንዘብ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው ውርስ ክፍል አይሆንም ካለ ሟች አባታችን የውርስ ሀብት ክፍል አለመሆኑ በዝርዝር ተብራርቶ ስለተገለጸ እኛ ሕግ ያልሰጠንን ገንዘብ ይገባናል ብለን አልጠየቅንም የሚል መልስ ሰጥቷል።

የ2ኛ መልስ ሰጭ ነገረ ፈጅ ባቀረቡት መልስ የገለጹት ፍሬ ቃል ወ/ት ሣራ ተክለሃይማኖት የሟች የመጀመሪያ ልጅ መሆኑዋን ከሟችና ካሁን ይግባኝ ባይ እንደማትወለድ ገልጸ በመጀመሪያ ገጽ የጻፈው የሬጂስትራሩ ጽ/ቤት ለዚህ ችሎት ጉዳዩን የመራው በይግባኝ ባይ ሃሳብ በመመራት መሆኑንና ካሁን ቀደም ተመሳሳይ ክርክር ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 749/70 ውሳኔ መስጠቱን ጠቅሞ ጉዳዩ በዳኞች ሰብሰባ

ወይም በፓናል እንዲታይና ለአንድና ለመጨረሻ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ሲባልና ትክክለኛ ፍትህ ላይ ለመድረስ ይረዳ ዘንድ ጉዳዩ በፍርድ ቤቱ በኩል ለፓናል እንዲቀርብ የሚል ማሳሰቢያ ሲሆን፣ ይህም ተቀባይነት ካጣ በማለት ለፍሬ ጉዳዩ ያቀረቡት መልስ ይግባኝ ባይ እቅመ አዳም ያልደረሱ 4 ልጆች ሞግዚት ንብረት አስተዳዳሪና ወኪል ሲሆኑ አሁን የሚከራከሩት የጥቅም ግጭት ፈጥረው መሆኑን በመግለጽና ስለጠበቆቻቸውም ወጭ በመጠኑ አውስተው 4ቱን ልጆች የሚያስተምርላቸውና የሚያሳድጓቸው ይግባኝ ባይ ሲሆኑ የሞግዚትነትና የአስተዳዳሪነት ሥልጣናቸው ሳይሻር ተወካይ ከወኪሉ ጋር የጥቅም ግጭት ፈጥረው ሁለቱን ወገን ወክሎ መከራከር እንደማይገባቸው ጠቀመው መልስ ከሰጡ በኋላ፣

ሀ. ይግባኝ ባይ ለራሳቸውና ለእራሱ መልስ ሰጭዎች ወኪልና ተወካይ በመሆን ተቃራኒ ሃሳቦች በአንድ መድረክ ላይ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ክርክር ተነስቶ ብይን ያልተሰጠበት ስለሆነ የ4ቱ መልስ ሰጭዎች የጥብቅና ውክልና በአግባቡ የተሞላ ባለመሆኑ እንዲሰረዝና ውድቅ እንዲሆን በመጠየቅ፣

ለ. ክርክር መቅረብ ያለበት በቅን ልቦናና በአግባቡ እንጂ ሁለቱ ወገን ተመሳጥረው ሌላውን ለማጥቃት የፍርድ መድረክን በተገኘው ላይ እንዲጠቀሙበት በሳልሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ የፀና እንዲሆንና መዝገቡም እንዲዘጋ፣

ሐ. በቅን ልቦና ላይ ያልተመሠረቱና ያልተገዱ ወገን የመሠረተውን ክስ የምንቀጥል ቢሆን የአቶ ተክለሃይማኖት ሕጋዊ ሚስትና የልጅ እናት ወ/ሮ አሰቁር ተከስተ ሲሆኑ ልጃቸው ወ/ት ሣራ ተክለሃይማኖት ናት።

ወ/ት ሣራ ተክለሃይማኖት ከተወለደች በኋላ በባልና ሚስት መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ተለያዩ። የመጀመሪያ ሚስት የ2ኛ ዋን ሚስት በጥቅም እንዳይፃረሩ ያውንዋ ይግባኝ ባይ መድሀን ፖሊሲ ላይ በማቸው ተጻፈ። ሣራ ተክለሃይማኖትን ኗች ወስደው አብረዋት አስቀምጠው ያሳድጓት ነበር።

ይግባኝ ባይ አቶ ተክለሃይማኖት ሀመም ሲጀምራቸው ወ/ት ሣራን አባረሩ። አቶ ተክለሃይማኖት ከሞቱም በኋላ ይግባኝ ባይ አቶ ተክለሃይማኖት ሌላ ልጅ እንዳላቸው እያወቁ ከሳቸው የተወለዱትን ብቻ ለውርስ አቀረቡ።

ያውራጃው ፍርድ ቤት በጋዜጣ ባደረገው ጥሪ መሠረት ወ/ት ማሩ ቀርባ ወራሽነቷ ተረጋግጦ ይግባኝ ባይ የሟች ውርስ ለወ/ት ማሩ እንዳያደርስ በመደረጉ ያውራጃው ፍርድ ቤት ከኢንሹራንስ ገንዘብ በቀር የውርሱን ንብረት በሚመለከተው የማሩ ተከለሃይማኖት መብት በሀግና በፍርድ ቤት እርዳታ ሊከበርላት ችሏል።

ይግባኝ ባይ የወለዷቸውን ልጆችና ማሩ ተከለሃይማኖት በማስወገድ የራሳቸውንና የልጆቻቸውን ድርሻ በማሰባሰብ ለመጠቀም በመሆኑ የማሩ ተከለሃይማኖት ሕጋዊ መብት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የጠበቀላት በአግባቡ ስለሆነ ፍርዱ እንዲፀና ውዝግቡ እንዲወገድ ጠይቀዋል።

በመሠረቱ ክርክሩ ለተነሳው ጭብጥም በሰጡት መልስ የኢንሹራንስ ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል ነው አይደለም? የንግድ ሕግ ቁጥር 701 እና 706 ግንኙነት ወይስ ቅራኔ አዘል ትርጉም መያዝ አለባቸው? ቀጥታ የህግ ትርጉም ምን መሆን ይገባዋል? ከሚል ተነስተው ያብራሩት ቢኖር መብት ከህግ ወይም ከውል በሰሚመነጭ ከውል የሚመነጭ መብት ከህግ የሚመነጨውን መብት ይበልጣል ለማለት ምን ይከለከላል? ከሕግና ከውል የሚመነጩ መብቶች በአፈጻጸም ፍትህን ተከትሎ ሊደላደል ይገባዋል ተብሎ ሚዛንን መጠበቁ ሃቁ የተሻለ ይሆናል? በማለትና ስለሕግ ትንታኔ አስተያየትና መከራከሪያ ጭብጥ አውስተው "የተለዩ ተጠቃሚና" "የታወቀ ተጠቃሚ" የሚሉት ቃላት በሀጉ ውስጥ ያላቸው ኃይልና አስተጋብእ በተለይ በሀጉ ውስጥ "የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመ በኋላም ቢሆን" የሚለውን ሐረግ ለጠቃላይ ሀሳብ ወይም ጀኔራል ፕሪንስፐልና ግድፈት (ኤክሴፕሽን) ያላቸውን የህግ አተረጓጎም ዘይቤ በማስታወስ በአንድ ድንጋጌ አንቀጾች መካከል ቅራኔ ከመፍጠር ውህደትና መግባባትን መፍጠር የበለጠ የህግ አተረጓጎም የተከተለ አይሆንም? የኢንሹራንስ ገንዘብ የውርስ ገንዘብ ስላልሆነ ሁለተኛው መልስ የውርስ ገንዘብ ነው በማለት አልተከራከረችም፣ ይህ ከጭብጡ ውጭ በመሆኑ መወገድ አለበት።

አንድ የውርስ ሕግ ወራሽ የሆነ ሰው በንግድ ሕግ የታወቀ ተጠቃሚ መሆን የሚችል አለ። እንዲሁም ቢሆን ተጠቃሚው ሊሆን የሚችልም አለ። ሁለት የተለያዩ መብቶች የተለያዩ ንብረቶች ላይ ነው በማለት በሰፊው ዘርዝረው ስለንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና 706 አንስተው ከጉዳዩ ግንኙነት የሌላቸው መሆናቸውን እንደዚሁም በመዝገብ ቁጥር 749/70 በተጠቀሰው ምክንያት ጭብጥና መከራከሪያ ሃሳቡ አግባብነት የሌላቸውና የማይዛመዱ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህም ቀጥሎ ያነሱት ክርክር መድን ድርጅት ለሁለቱም ተጠቃሚዎች ማለትም ከህጉም ሆነ ከውል ለመነጩላቸው

ባለመብቶች ከማከፋፈል በስተቀር ለአንዱ ሰጥቶ ሌላውን እንዲከለክል የተሰጠ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ አለመኖሩን ቢሆን ተደም ብሎ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 749/70 በወይዘር የሺመቤት ጃማነህና በመድን ድርጅት መካከል ተነስቶ የተከራከሩበትና የወሰነውን በመጥቀስ በዚያ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ የተጠቃሚዎችን መብት ሳይነካ የተገኘ ብቻ የሚካሰበት ውሳኔ በመስጠት በህግም ሆነ በውል ከመነጨላቸው መብት የታወቁ ተጠቃሚዎች ከፍያቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን ያረጋግጣል። የተጠቀሰው ውሳኔ ይግባኝ ባይ እንዳሉት ሳይሆን አጠቃላይ የሕግ ትርጉም በመመሪያ መልክ ያልተሰጠበት በመሆኑ አሁን ሊሰጥበት ይገባል በማለት በረጅሙ አብራርተው የቀረበው ይግባኝ ከህግ ውጭ መሆኑን፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ በሚገባ ነው ተብሎ ከበቂ ኪሣራ ጋር ይግባኙ እንዲሰናበት ጠይቀዋል።

ይግባኝ ባይም ባቀረቡት የመልስ መልስ የቀድሞ ክርክራቸውን የሚያጠናክር ጠቅለል ባለ ሁኔ አቅርበዋል።

በኛ በኩል መዝገቡን መርምረናል የቀረበውን የሕግ ክርክር ከማየታችን በፊት 1ኛ/ መልስ ሰጭ በቅድሚያ ያቀረበው ክርክር የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ግን መሆኑ ተለይቶ በሚገባ እንዲታወቅ፣ 2ኛ/ የኢንሹራንስ ፖሊሲው ብር 15,000 ሆኖ ብር 20,000 የተባለው በስህተት ነው፣ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ያለውን ተመልክተናል።

በመሠረቱ ክሱ የአሁኑ ይግባኝ ባዮች መሆኑ ታውቋል፤ 1ኛው መልስ ሰጭ የሟች ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ተለይቶ በውሳኔ ይገለጽ ማለቱ የሚደገፍ አይደለም።

በ2ኛ ደረጃ ያነሳው ቢኖር የሟች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ብር 15,000 ብቻ እንጂ 20,000 አይደለም የተባለው ነው። በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 መሠረት አሥር ላይ መልሱን በማሻሻል ወይም የከፍያውን መጠን ተቃውሞ መልስ በመስጠት አላቀረበም። በዚህም ላይ ክርክር አቅርቦ የተሰጠ ውሳኔ ሳይኖር 1ኛ መልስ ሰጭ አሁን ለዚህ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበው ወይም ያነሳው ክርክር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው ጥያቄው ውድቅ ነው።

ሌላው የ3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ መልስ ሰጭዎች ጥማቢትና ወኪል ነገረ ፈጅ ያቀረበውንም መልስ ተመልክተናል። ነገረ ፈጁ ባቀረበው መልስ የይግባኝ ባይ ጥያቄ በመደገፍ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ ተጠቃሚው የተገለጸ በመሆኑ አከራካሪ ስላልሆነ

በፖሊሲው መሠረት እንዲፈጸም የሚጠይቅ ስለሆነ በነሱም በኩል ክርክሩን እንስቶ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘነው በዚሁ አልፈነዋል።

2ኛዋ መልስ ሰጭ ጉዳዩ አከራካሪ ነው፥ በላዮች ወይም በፓነል እንዲታይና የህግ ትርጓሜ በሚገባ እንዲሰጥና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ የሚጠይቅ ነው። ይህም ቢሆን ለዚህ ችሎት የቀረበው ተመሳሳይ ክርክር ቀደም ሲል አልቀረበም ማለት አይቻልም። የ2ኛ መልስ ሰጭ ነገረ ፈጅ አዲስ ክርክር የቀረበ መስሎአቸው ካልሆነ በዚህ ችሎት በተደጋጋሚ ቀርቦ በተለያዩ ጊዜ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ አከራካሪ የህግ ነጥብ ያለበት ጉዳይ ሆኖ ወደ ፓናል እንዲመራ ለማድረግ ባለመቻሉ በዚህ ነጥብ ላይ የቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልንም።

ይህ ተቀባይነት ካጣ ደግሞ በ3ኛ ደረጃ በ2ኛ መልስ ሰጭ ያነሳቸው ክርክር የይግባኝ ባይ የልጆቿ ሞግዚት ሆና ጥቅማቸውን በመፃረር መብታቸውን ለመግፈፍ ክርክር ስላቀረበች በዚህ ውሳኔ ተሰጥቶ ሞግዚትነቷ መሻር አለበት የሚል ነው። ይህን ክርክር እንዳየነው የተባሉትን ልጆች ጥቅም ለመጠበቅ ሞግዚትነቷ ሊሻር ይገባል የሚል ተከራካሪ በቅድሚያ ለቤተዘመድ ሽምግልና አመልክቶ በማስወሰን ለፍርድ ቤት አቅርቦ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንጂ አሁን ይግባኝ ባይ በከፈተችው የይግባኝ መዝገብ ላይ የሷን ጥያቄ ለማምከን የቀረበ ክርክር ሆኖ በመታየቱ ተቀባይነት የለውም።

ስለፍሬ ጉዳይ የቀረበውን ክርክር መርምረናል። እንደመረመርነውም ያሁን ይግባኝ ባይ ክርክር በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ መሠረት የሟች ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ነኝ፥ ገንዘቡን በሙሉ ማግኘት አለብኝ ነው።

2ኛዋ መልስ ሰጭ ደግሞ በንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ /ለ/ መሠረት ሕጉ የሟቹ ልጅ በመሆኔ ተጠቃሚ ስለሚያደርገኝ በክፍያ የሚደርሰኝን ድርሻ ማግኘት አለብኝ ነው።

በዚህ ችሎት ከዚህ ቀደም በተለያዩ መዝገቦች ተመሳሳይ ክርክር ቀርቦ ትርጉም ሰጥቶበታል። ከእያሌ መዝገቦች ውስጥ በመዝገብ ቁጥር 156/72 እና 740/70 ይገኙበታል።

በቁጥር 1561/72 መዝገብ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም ብንጠቅሰው

"በሕጉ ረገድ የቀረበውን ክርክር እንደተመለከትነው ክርክራቸው የተመሠረተው በቁጥር 701/1/ እና /2/ በተጻፈው ላይ ነው። በቁጥር 701 የተጻፈው ድንጋጌ አላማና መንፈስ ለመረዳት ዲህን ድንጋጌ ስለሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ በንግድ ሕግ የተጻፉት ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር እና እንዲሁም የሕይወት ኢንሹራንስ የውርስ አካል ሊሆን ስለሚችልበትና የማይችልበት ሁኔታ በፍትሐ ብሄር ሕግ በቁጥር 827 ከተጻፈው ጋር አብሮ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

በመሠረቱ የሕይወት ኢንሹራንስ በኢንሹራንስ ገቢውና በኢንሹራንስ ሰጭው መካከል የሚደረግ ውል ሲሆን፣ የውሉም አላማ ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል። 1ኛው ኢንሹራንስ የገባው ተዋዋይ በውሉ ውስጥ በተወሰነው ጊዜ በሕይወት ያለ እንደሆነ የተወሰነውን ገንዘብ በአንድ ጊዜ ወይም በሕይወት እስካለ ድረስ የተወሰነ ገንዘብ በየጊዜው እንዲከፈለው ለማድረግ ሲሆን 2ኛው ደግሞ ኢንሹራንስ ገቢው በሞቱ ጊዜ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው ሀብት ላላቸው ሰዎች ወይም በኢንሹራንሱ ውል ውስጥ ተጠቃሚ ሆኖ ለተጠቀሰው ሰው የተወሰነ ዋና ገንዘብ ወይም እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ በየጊዜው የሚከፈል ገንዘብ እንዲከፈል የሚያደርግ ነው።

በኢንሹራንስ ፖሊሲ ውል ውስጥ ሁለቱም ዓይነት ሁኔታዎች አጣምሮ መዋዋል ይቻላል።

አሁን የቀረበልን የፖሊሲ ውል ሁለቱንም የያዘ ነው። ይኸውም ሟች አቶ ዮሐንስ ነጋ የኢንሹራንሱን ውል የተዋዋለው በውሉ "በተወሰነው ጊዜ ውስጥ 1993 ዓ.ም. ከ33 ዓመት በኋላ በሕይወት ያለ እንደሆነ ለፖሊሲው የተመለከተው ብር 30,000 /ሠላሳ ሺህ/ ለራሱ እንደሚከፈለው ወይም ይህ የተወሰነው ጊዜ ከመድረሱ በፊት የሞተ እንደሆነ፣ የተጠቀሰው ገንዘብ ለባለቤቱ ላሁኑዋ ይግባኝ ባይ እንዲከፈላት" በማለት ነው። ይግባኝ ባይም ክፍያውን የጠየቀችውና የምትከራከረውም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው።

ከኢንሹራንሱ ፖሊሲ ውስጥ ተጠቃሚው ከተጠቀሰው ገንዘቡ መከፈል ያለበት ለዚሁ ለተጠቀሰው ሰው መሆኑ በንግድ ሕግ በቁጥር 691 እና 692 በተጻፈው ውስጥ ተደንግጓል።

ለሞት የሚደረግ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ሰው ጥቅም ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ በቁጥር 701/1/ ላይ የተገለጸ ሲሆን በቁጥር 701/2/ ደግሞ በውሉ ውስጥ በስም ባይጠቀሱም የኢንሹራንስ ገቢው ባለቤትና ልጆቹ ተለይተው እንደተጠቀሱ ተጠቃሚዎች የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው ተገልጿል። በቁጥር 701 የተጻፈው ድንጋጌ በቁጥር 695 ከተጻፈው ጋር መታየት ይኖርበታል። በቁጥር 695 በተጻፈው ድንጋጌ መሠረት የሚታወቅ የሆነ እንደሆነ በኢንሹራንሱ ተጠቃሚ የሆነው ሰው በኢንሹራንሱ ውል ውስጥ መገለጥ አለበት። ይኸውም ኢንሹራንሱ ውል ገቢው ተጠቃሚውን ለይቶ ለመጥቀስ የፈለገ እንደሆነ የተጠቃሚውን ስም ይገልጻል፤ ያልፈለገ እንደሆነ ግን አይገልጥም።

እንግዲህ በቁጥር 695 የተጻፈው 701 ከተጻፈው ጋር በማዛመድ ስንመለከተው ኢንሹራንስ ገቢው ተጠቃሚውን ለይቶ የጠቀሰው እንደሆነ በቁጥር 701/1/ መሠረት ፖሊሲውን ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ሰው ጥቅም እንዳደረገው ይቆጠራል። "ተጠቃሚውን ለይቶ ያልጠቀሰው የሆነ እንደሆነ ግን በቁጥር 701/2/ በተጻፈው መሠረት ባለቤትና ልጆቹ እንደተጠቃሚ ይቆጠራሉ ማለት ነው። ይህም ከሌሎች "በንግድ ሕግ ቁጥር 705፣ 706፣ 707 እና 708 ከተጻፉት ድንጋጌዎችና እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ሟቹ ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ ወይም ኢንሹራንሱ ሌላ ነገር ቢያመለክት ለሟቹ ወራሾች ጥቅም የተደረገ እንደሆነ ሟቹ በፈረመው በሕይወት ኢንሹራንሱ ውል መሠረት የሚከፈሉ ገንዘቦች የውርሱ ንብረት አካል ይሆናሉ፤ ተቃራኒ ሁኔታ ቢኖር የውርሱ ንብረት አካል አይሆኑም ከሚለው ጋር የሚስማማ ነው።

የኢንሹራንስ ገቢው ባለቤትና ልጆቹ ተጠቃሚ ተለይቶ በተጠቀሰው ጊዜ በግልጥ እንደተጠቀሰው ተጠቃሚዎች የሚቆጠሩ ቢሆን ኖሮ በአንድ ሕግ ውስጥ በቁጥር 705፣ 706፣ 707 እና 708 የተመለከተውን መጻፍ ባላስፈለገም ነበር።

እንግዲህ ነገሩን ስናጠቃልለው በንግድ ሕግ መሠረት አንድ ሰው በሚፈጽመው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል የፈለገውን ሌላ ሰው ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል። ይኸውም ሚስቱን ከልጆቹ አንዱን ወይም ሁለቱን ልጆቹ ለይቶ ወይም ሌላ ሰው ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል ማለት ነው። ለፈለገው ሰው ስጦታ ሊያደርግ እንደሚችለው ሁሉ የፈለገውን ሰው ተጠቃሚ ማድረግ ይችላል። ተጠቃሚ ካደረገ እንደስጦታ የሚቆጠር ነውና የኢንሹራንሱ ገንዘብ መከፈል የሚገባው በኢንሹራንሱ ውል ለተጠቀሰው ተጠቃሚ ነው።

ባለቤትና ልጆች ከኢንሹራንሱ ገንዘብ ተካፋይ ሲሆኑ የሚችሉት የኢንሹራንሱ ውል ውስጥ ሌላ ተጠቃሚ ተለይቶ ያልተጠቀሰ እንደሆነ ብቻ ነው። ይኸውም መሆኑ ይታወቅ ዘንድ "በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 827 ሟቹ ተጠቃሚውን ለይቶ ያልጠቀሰ እንደሆነ .... እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 705 ተጠቃሚ ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ወይም ተነግሮ እንደሆነ፣ ወይም በሕይወት የሌለ በመሆኑ ውድቅ እንደሆነ፣ ... በሕይወት ኢንሹራንሱ ውል መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ የውርስ አካል ይሆናል" በማለት የተደነገገውን መመልከቱ ይበቃል የሚል ነው።

ሁለተኛዋ መልስ ሰጭም ብትሆን በጻፈችውም ሆነ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክርክር ሟቹ በኢንሹራንስ ውሉ ሚስቱን ማለት ያሁን ይግባኝ ባይዋን የኢንሹራንስ ገንዘብ ተጠቃሚ አላደረጋትም በማለት ሳይሆን የሟቹን ኢንሹራንስ ብቻዋን ተጠቃሚ መሆን አይገባትም፣ ከውል ባሻገር ከህግና ከውል የሚመነጩ መብቶች በአፈጻጸም ፍትሀን ተከትሎ ሊደላደል ይገባል ተብሎ ሚዛን ለመጠበቅ የቀ የተሻለ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ ተነስታ ተጠቃሚና የታወቀ ተጠቃሚ የሚሉት ቃላት በህጉ ውስጥ ያላቸውን ኃይልና አስተጋብኦ እንዲሁም በተለይ በህጉ ውስጥ የኢንሹራንሱ ውል ከተፈረመ በኋላም ቢሆን የሚሰውን ሐረግ አጠቃላይ ሃሳብ ወይም ጀኔራል ፕሪንስፐል እና ግድፈት (ኢክሴፕሽን) ያላቸውን የህግ አተረጓጎም ዘይቤ በማስታወስ በአንድ ድንጋጌ እንቀጾችም መካከል ቅራኔ ከመፍጠር ውህደትን መገንባት የበለጠ የህግ አተረጓጎም የተከተለ አይሆንም? የሚል ነው።

በይግባኝ ባይ በወይዘሮ የሺመቤት ፍሥሐና በመልስ ሰጭዎች 1ኛ/ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና 2ኛ/ የአቶ ዮሐንስ ነጋ ወራሾች መካከል ቀርቦ የነበረው ክርክር የንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ እና 701/2/ እንዲሁም በቁጥር 705፣ 706፣ 707 እና 708 ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ጋር ያላቸው ግንኙነት በሚገባ ተብራርቶ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ በዚህም መዝገብ በይግባኝ ባይና በመልስ ሰጭዎች ለቀረበው ክርክር ተመሳሳይና ተስሚነትም ያለው ሆኖ አግኝተነዋል።

በዚህም መሠረት የ2ኛ መልስ ሰጭ ክርክር ተቀባይነት አይኖረውም። በንግድ ሕግ ቁጥር 701 እና 706 መሠረት በኢንሹራንስ ፖሊሲ ውል ውስጥ የኢንሹራንሱ ገንዘብ ተጠቃሚ ይግባኝ ባይዋ መሆኑዋ በግልጽ ተጠቅሶ ስለምትገኝ የሟች የአቶ ተክለሃይማኖት ወልደገብርኤል የሕይወት ኢንሹራንስ በሙሉ ለወ/ሮ ጽጌረዳ ወልደሥላሴ ሊከፈላት ይገባል ብለን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 መሠረት ሽረን ወስነናል።

ኪሣራ ወጭ ለይግባኝ ባይዋ መብቷ ተጠብቆላታል፤ ዝርዝሩ በፍትሐብ
ሥርዓት ሕግ ቁጥር 463 እና 464 መሠረት ቢቀርብ እንዳስፈላጊነቱ ታይቶ
ይጻፍ።

The Supreme Court of Ethiopia First Civil Division
Civil Appeal Case No. 677/76

Designation of beneficiaries in a life insurance policy - Right of the surviving spouse and heirs - purposes of a life insurance policy - the limited scope of precedence in Ethiopia - Conflict of interest of minors and guardians - Removal of a guardian tutrix - Amendment of pleading - New facts and arguments on appeal. Civil. C. Art. 827(2), Comm. C. Arts. 691, 692, 695, 701 705-708, Civ. Pro. C. Arts. 91, 329.

On appeal from a judgment of the High Court denying the designated beneficiary her request to be entitled to the whole proceeds of a life insurance policy.

Held: Judgment Reversed

A life Insurance Policy may have two purposes.

1. *The insurer undertakes to pay a specified capital or life interest to the insured if he is alive.*

2. *Upon the death of the insured, the money is to be paid to those having rights from him or to the beneficiary named in the policy.*

As the subscriber is free to make donations to anyone, so can he make anyone he likes a specified beneficiary. Once he has done this, the money should be paid to the specified beneficiary. The surviving spouse and children are paid only when a specified beneficiary is not named in the policy.

Sene 28, 1976*

Justices:	Ato Getachew Afrassa Ato Demissie Yadetie Woizt Rahel Alemayehu	
Appellant:	Woiz. Tsigereda Wolde Sellassie	
Respondents:	1.	The Ethiopian Insurance Corporation
	2.	Sara Tekle Haimanot
	3.	Mehret Tekele Haimanot
	4.	Amanuel Tekle Haimanot
	5.	Meaza Tekle Haimanot
	6.	Nebiyou Tekle Haimanot

We have examined the file and given the decision as follows:

Decision

This is an appeal against the decision of the High Court rendered on Hedar 5, 1976 under Civil Case No. 602/73.

The Appellant field her memorandum of appeal dated Tahssas 25, 1976. It was served on the respondents. The first Respondent filed a reply written on Megabit 17, 1976, and the 2nd, 4th, 5th and 6th Respondents filed their replies on Megabit 17 and Megabit 24, 1976. Later on, the Appellant filed a counter reply on Miazia 4, 1976.

This case arose from a disagreement between the parties because each claimed to be the beneficiary of a life insurance policy to which the deceased, Ato Teklehaimanot W/Gebriel, was a subscriber.

The High Court considered the Appellant's claim in light of Art. 701 of the Commercial Code, and it also referred to sub-art (2) and held that the spouse and the children of the subscriber are specified beneficiaries. It further noted that, although money due from a contract of a life insurance policy does not form part of the inheritance, the Code provision intends to make the nearest relatives of the deceased and his dependents beneficiaries of the policy. Under the Civil Code, the Court went on, ascendants and descendants could become heirs, but the law considers only the spouse and children as beneficiaries of a life insurance policy. Accordingly, the High Court interpreted the law to mean that the policy subscriber's spouse and children are specified beneficiaries even when the subscriber has clearly designated the beneficiary. Finally, the High Court decided that in accordance with Art. 701(1) and (2) of the Commercial Code, the insurance money should be paid to both the spouse (present Appellant) and the children of the deceased.

Moreover, the court rejected the contention that the children of the present Appellant had refused to share in the insurance proceeds on the ground that the policy specified the Appellant as the sole beneficiary. It further termed this contention as an act of bad-faith intended to prejudice the second Respondent (Appellant's step daughter). The Court finally ruled that the life insurance money should be partitioned among the spouse (present Appellant) and the five children on an equal basis so that each would receive Birr 3333.03.

The Appellant objected to this judgment on the ground that the High Court erred when it considered sub-arts (1) and (2) of Art. 701 of the Commercial Code as one and the same. The Appellant argued that sub-arts (1) and (2) of Art. 701 deal with two different forms of insurance payments and prayed that the judgment of the High Court be reversed, and the whole sum (Birr 20,000) paid to her as a specified beneficiary in the policy.

Counsel for the first Respondent stated that sub-arts (1) and (2) of Art. 701 of the Commercial Code have always been controversial in the Courts. To this effect, he cited a similar case wherein the Insurance Corporation was obliged to make a second payment and lost Birr 60,000 as a consequence of the Supreme Court's reversal of the High Court's decision. Counsel then requested the court to decide who should be paid; the Appellant or the children?

Furthermore, counsel stated that the actual amount due, based on the premium, should have been Birr 15,625; but it was wrongly set at Birr 20,000. To prove this point, he asked leave to introduce evidence under Art. 345 of the Civil Procedure Code.

In his reply, counsel for five of the respondents stated that, as there is a specified beneficiary pursuant to Art. 827(1) of the Civil Code, and since the sum to be paid to such beneficiary does not form part of the insured's estate (Art. 706/2/Commercial Code), we did not claim what we are not entitled to under the law.

The salient points of the reply by counsel for the second Respondent were the following:

- that the second Respondent is the eldest daughter of the deceased but not by the present Appellant;
- that the office of the Registrar referred the case to this court based entirely on the Appellant's motion; and
- that this same issue was formerly decided in file No. 749/70.

Counsel finally requested that the case be reviewed by a panel of judges so that a lasting and just decision could be given. Should this be rejected, counsel alternatively argued that the Appellants interests are in direct conflict with that of the four minor children. Based on this, the counsel prayed to the court that:

a. since the Appellant has a conflict of interest with the four children to whom she is a guardian tutrix, the representation of these children by the counsel for Appellant is unfair and should be revoked;

b. the contention of the Appellant and her four children is contrary to good-faith and, since the case was instituted deliberately to injure the second Respondent, the judgment of the High Court should be upheld with damages and the file should be closed;

c. if he is expected to resume this appeal initiated by a person who has not sustained any harm he would like to clarify this fact.

The deceased first married Wro. Aster Tekeste but the marriage was terminated by divorce after Sara Tekle Haimanot (the 2nd Respondent) was born. Later on the deceased married the present Appellant and made her a specified beneficiary of his life insurance policy. Ever since the dissolution of the first marriage, the second Respondent lived with the deceased. When deceased fell sick, the Appellant forced Wt. Sara Tekle Haymanot to leave her father's house.

Upon the death of Ato Tekle Haymanot, Appellant presented her four children as sole heirs of deceased, although she knew that he also had another daughter. That Wrt. Sara is an heir of the deceased was later determined by the Awraja Court when she appeared before it after reading the notice in the newspaper. The Awraja Court decided that, except for the deceased's life insurance, Wrt. Sara is entitled to share the inheritance of her deceased father. Counsel for the 2nd Respondent asked that the decision of the High Court which legitimately entitled the Respondent also to share in the proceeds of the insurance policy be confirmed.

In his attempt to show what the relationship between Arts. 701 and 706 of the Commercial Code should be, counsel for the second Respondent stated that rights emanating from the law prevail over contractual rights. He stressed "specified beneficiary" and especially the phrase, "... even after the policy was entered into" in Art. 701 (2) (a) of the Commercial Code as crucial to the interpretation of the law.

Having considered these facts in light of the rules of interpretation concerning general principles and exceptions, counsel concluded that the two provisions should be interpreted positively so as to reconcile them, rather than to give them conflicting meanings. Counsel reiterated the fact that money due from a contract of life insurance does not form part of the inheritance, and denied that the Respondent argued to this effect.

He also stated that those who are heirs under the Civil Code are not necessarily specified beneficiaries under the Commercial Code. The two rights relate to different properties. Therefore, Arts. 705 and 706 of the Commercial Code are not relevant to the case under consideration. In addition, as stated in file No. 749/70, the points of argument raised are not relevant to the issue.

Counsel also contends that there was no order or decision to the effect that the Insurance Corporation should pay one beneficiary and not the other. The Insurance Corporation should have paid both beneficiaries without any distinction between those whose rights derive from the law and those whose rights derive from the insurance policy.

In relation to this, counsel cited a case decided by the Supreme Court (Yeshimebet Jemaneh v. the Ethiopian Insurance Corporation). He explained that the decision in that case had established that payment should be made to the specified beneficiaries, both in accordance with the law and the contract of insurance. Finally, he challenged the appeal as unfounded and asked the Court to confirm the decision of the High Court. In her counter-reply, the Appellant made arguments substantiating her initial contentions.

This court, on its part, has examined the file thoroughly. Before dealing with the legal arguments we have considered: (1) first Respondent's contention for the determination of the actual beneficiary and (2) his request to introduce evidence to show that the value of the insurance policy is Birr, 15,000 and not Birr 20,000.

It is clear that the suit was initially instituted by the present Appellant who is a specified beneficiary in the policy. Therefore, the contention of the first Respondent that the actual beneficiary be determined is not appropriate. As regards the second point raised by the first Respondent, it neither amended its reply nor did it object to the amount before the lower court pursuant to Art. 91 of the Civil Procedure Code. Therefore, we have rejected the request, for it is not in accordance with Art. 329(1) of the Civil Procedure Code. We have also considered the replies made by counsel for the 3rd, 4th, 5th and 6th Respondents. In his reply, counsel supports the Appellant's claim and suggests that payment be made to the specified beneficiary named in the insurance policy. This court believes that this point is not controversial. Hence, there is no point in dwelling on it.

Concerning the request of the 2nd Respondent that the case be tried by a panel of judges, in the opinion of this court, the case does not involve any unusual and difficult question of law. Besides, this court has repeatedly rendered decisions on similar cases. For these reasons, we reject Respondent's claim.

The second Respondent has also argued alternatively that the Appellant has conflicting interests with the children to whom she is a guardian-tutrix, and therefore she must be removed. We reject his argument on the ground that one who deems the removal of a guardian necessary for the benefit of the minor should first obtain the decision of the family council in his favour. Without doing this, the second Respondent cannot demand the removal of the Appellant by the Court.

We have duly examined all the arguments made by all parties. The Appellant claims the whole of the insurance money, for she is a specified beneficiary of the deceased's life insurance policy pursuant to Art. 701 (1) of the Commercial Code. The second Respondent on the other hand, invoking Art. 701 (2) (1) of the Commercial Code has claimed her share as an heiress of the deceased. The court had previously interpreted the law while deciding many similar cases. Among them were files No. 1561/72 and 749/70. In file No. 1561/72, the court interpreted the law in the following way:

The argument of both parties is based on the provisions of Art. 701 (1) and (2) of the Commercial Code. In order to understand the purpose and spirit of the provision, Art. 701 should be seen in light of other relevant provisions of the Commercial Code. It should also be read together with Art. 827 of the Civil Code, which regulates the circumstances under which life insurance money may or may not form part of the inheritance.

A life insurance policy is basically a contract between the subscriber and the insurer and it may have two purposes. The first is where the insurer undertakes to pay a specified capital or life interest provided the insured person is alive; the second is where the insurer undertakes to pay, upon the death of the insured person, a specified capital or life interest to those having rights from the insured person or to the beneficiary named in the policy. A combined policy may be made where the insurer undertakes to pay under both circumstances. The policy under consideration is of such a nature.

The insurance policy was concluded on such terms that the insurer will pay to the insured Birr 30,000 provided the insured, Ato Yohannes Nega, is alive in 1983, i.e., after 33 years. Should the insured die before this period, the agreed amount will be paid to the decreased's wife. The Appellant's claim is based on this provision of the policy.

It is provided under Art. 691 and 692 of the Commercial Code that the insurer undertakes to pay to the beneficiary who is specified in the policy. Art. 701 (1) of the Commercial Code provides that an insurance policy for the event of death may be made to the benefit of a specified beneficiary. Sub-art (2) of the same article provides that the spouse and the children of the subscriber shall be deemed to be specified beneficiaries notwithstanding that they are not mentioned by name.

In order to understand it clearly, Art. 701 should be read together with Art. 695 of the Commercial Code. According to the latter article, if the beneficiary is known, his name should be indicated in the policy. This shows that the insured may or may not choose a specified beneficiary. Thus the cumulative reading of Arts. 695

and 701 of the Commercial Code leads to the conclusion that, if the insured has specified the beneficiary, then the insurance policy will be deemed to have been made to the benefit of the specified beneficiary pursuant to Art. 701 (1) of the Commercial Code. If, however, the insured has not specified the beneficiary in the policy, his spouse and children, pursuant to art. 701(2), will be deemed to be specified beneficiaries.

This conclusion is in conformity with other relevant provisions of the Commercial Code, (Arts. 705-708). It is also in conformity with Art. 827 of the Civil Code which provides. "money due in performance of a contract of life insurance shall form part of the inheritance where the deceased has not determined the beneficiary or the insurance is made to the benefit of the heirs of the deceased without any other indication; in all other cases, they shall not form part of the inheritance."

If the spouse and the children of the deceased were deemed to be beneficiaries even when the beneficiary is specified in the policy, Art. 705-708 of the Commercial Code would be rendered redundant.

To sum up, the subscriber can make any person the beneficiary of his life insurance in accordance with the provisions of the Commercial Code. By the same token, he can make his spouse, or one or more of his children specified beneficiaries. As the subscriber is free to make donations to anyone, so can he make anyone he likes a specified beneficiary. Once he has done this, it will be considered as if he had made a donation and the money should be paid to the specified beneficiary named in the policy.

This line of argument is also supported by the provisions of Art. 827 of the Civil Code, which reads. "... where the deceased has not determined the beneficiary ...", and also by the provision of Art. 705 of the Commercial Code, which reads, "where the deceased has not determined the beneficiary ...", and also by the provision of Art. 705 of the Commercial Code, which reads, "where no beneficiary has been specified or has been revoked or is not alive, the capital to be paid by the insurer shall be paid into the subscriber's estate."

In her arguments presented to the High Court the 2nd Respondent did not deny that the deceased had made his wife (present Appellant) a specified beneficiary to the life insurance. The Respondent contended that the Appellant should not be the sole and exclusive beneficiary. To substantiate her contentions, the Respondent stressed that all rights emanating both from the law and contracts should be realized on the basis of justice. The Respondent also emphasized the impact the words "beneficiary" and "specified beneficiary" may have on the interpretation of the law. Finally, the Respondent analyzed the phrase "... even after the policy is entered, into"

contained Art. 701(2) (a) of the Commercial Code, in light of the rules of interpretation concerning general principles and exceptions, and concluded that it is not proper to create contradiction between provisions of the same article.

The case considered above between Yeshimebet Fissaha and the Ethiopian Insurance Corporation, et. al, is the one wherein the relationship between Commercial Code Arts. 701(2), 705-708 and Civil Code Art. 827 is extensively elaborated. Hence, we have ruled that the decision given in that case is relevant and applicable to the case under consideration.

Accordingly, we have rejected the contentions of the second Respondent. Hence, because pursuant to art. 701(1) and 706 of the Commercial Code, the Appellant has been named in the policy as beneficiary, we have ruled that the whole amount of the insurance money should be paid to the Appellant, Tsigereda Wolde Selassie.

The decision of the High Court is hereby reversed in accordance with Art. 348 of the Civil Procedure Code. Costs and damages shall be paid to the Appellant in accordance with Arts. 463 and 464 of the Civil Procedure Code.

<u>Editor's Note</u>

**Unless stated otherwise, all dates are according to the Ethiopian Calendar.*

<u>ለሞት በተዳረገ የሕይወት መድን ፖሊሲ ተጠቃሚውን ለይቶ ስለማስታወቅ</u>

በግርማ ወ/ሥላሴ*

ማንኛውም ሰው ለሕይወቱ የኢንሹራንስ ውል ሲዋዋል እንዲሆንለት የሚፈልገው እሱ በሚሞትበት ጊዜ እንድሌላ ሰው ከኢንሹራንስ በሚገኘው ገቢ እንዲጠቀም መሆኑ ግልፅ ነው፤ የሕግ ሊቃውንትን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እያጨቃጨቀ ያለው ጥያቄ ግን "የማሕበረሰቡ ፍላጎት ኢንሹራንስ በተዋዋለው ሰው ላይ ተፅዕኖ በማድረግ በሕግ አካማይነት ቢያገባ ቢያገባ የእሱ ባለቤትና ልጆች የኢንሹራንሱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት ወይስ ተዋዋዩ ሙሉ ነፃነት ተሰጥቶት በራሱ ነፃ ምርጫ ተጠቃሚውን መወሰን አለበት?" የሚለው ነው።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች በዚህ ጥያቄ ላይ በአቋም ተለያይተው ይገኛሉ።** ለፍርድ ቤቶች በቀረቡ ብዙ ጉዳዮች ላይ ተዋዋዮች በሞት ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ሰዎች ከቅርብ ቤተሰባቸው ውጪ አድርገዋል። ኢንሹራንስ የገባው ሰው በሚሞትበት ጊዜም ክፍያ የሚጠይቁት በፖሊሲው ላይ የተመለከቱት ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ን መሠረት በማድረግ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆችም ጭምር ናቸው። በፍርድ ቤቶች ዘንድ የተነሳው አከራካሪ ነጥብም የተጠቀሰው ሕግ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች በፖሊሲው ላይ ባይጠቀሱና ሌላ ሦስተኛ ሰው በብቸኛ ተጠቃሚነት በግልፅ ቢጠቀስ ከሚገኘው ገንዘብ ማግኘት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ነበር።

በተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁ. 701/1/ ላይ በመመሥረትም የከፍተኛው ፍ/ቤት አንድ ችሎት ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከባል ወይም ሚስቱና ልጆቹ ውጪ የሆነ ሰውን ጨምር የራሱን ተጠቃሚዎች ሊጠቅስ እንደሚችል ይፈቅዳል።

* ፀሐፊው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት ረዳት ፕሮፌሰር ነበሩ።

** በዚህ የሕግ መጽሔት ላይ የወጡትን የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይመለከቷል። (አዘጋጁ)

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ቁጥር 701/1/ን ከንዑስ ቁ. /2/ ጋር አጣምሮ በማንበብ ግን ፍ/ቤቱ ምንም እንኳን በተዋዋዩ በተጠቃሚነት ባይጠቀሱም ባል ወይም ሚስትና ልጆች በማንኛውም ለሞት ጊዜ የሚደረግ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ይገመታል ከሚል ማጠቃለያ ላይ ደርሰአል። ስለዚህ፥ በዚህ ፍ/ቤት መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው እናቱን እንደብቸኛ ተጠቃሚ አድርጎ ቢጠቀስም ሴትዮዋ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገንዘብ ከሟቹ ባል ወይም ሚስትና ልጆች /እንዲሁም ከሌሎች "ወራሾች" እንደ ፈረንሳይኛው ሕግ አባባል/ ጋር መካፈል ይኖርባታል ማለት ነው።

በግልፅ እንደሚታየው ይህ ትርጓሜ የሚከተለው ተጠቃሚው ማን መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ለተዋዋዩ ገደብየለሽ ሥልጣን መስጠትን የሚቃወመውን የአስተሳሰብ መሥመር ነው። ይህንንም አቋም የሚደግፉ ብዙ መከራከሪያ ሃሣቦች አሉ።

መጀመሪያ ነገር፤ ተዋዋዩ አብዛኛውን ጊዜ ብቸኛው የገቢ ምንጭ ነው። በመሆኑም እሱ ቢሞት ቤተሰቡ ሊኖር የሚችልበትን ነገር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት። የሚወረስ ንብረት ቢኖርም እንኳን የማጣራቱ ሂደት በአብዛኛው በጣም ረዢም ጉዳይ መሆኑ የቤተሰብ እንገብጋቢ ችግሮችን ወዲያውኑ ለማስወገድ አያስችልም። በሌላ በኩል ደግሞ የኢንሹራንስ ክፍያዎችን በተነፃፃሪ መልኩ በጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ቀላል እንደሚል ይታሰባል።

ሌላው የመከራከሪያ ሃሳብ የጋራ ሀብትን ለመጠበቅ ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም ከሕይወት ኢንሹራንስ የሚገኝ ገቢ ሟቹ ትቶት ከሚያልፈው ጠቅላላ ሀብት ሆኖ ስለማይቆጠርና በውርስ ሕጎችም የሚታይ ባለመሆኑ ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆች ውጪ የሆነውን ሰው ለመጥቀም የሚደረግ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሊወረስ ከሚችለው ሀብት /estate/ ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ ለማግለል በመሣሪያነት ሊያገለግል ስለሚችል ነው።

ሦስተኛ፤ ተጠቃሚ ሰው መጥቀሱ በተለይም የጠቅላላ ሀብቱ ክፍል ቢሆን ኖሮ ግማሹን ሊያገኝ ይችል የነበረውን በሕይወት ያለውን የሟች ባል ወይም ሚስት በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ ይችላል። መስተዋል ያለበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተዋዋዩ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያደርጋቸው ክፍያዎች /premiums/ የባልና የሚስቱ የጋራ ንብረት ከሆነው ከገቢው ላይ መሆኑ ነው።

ስለዚህ ባልና ወይም ሚስትንና ልጆችን፣ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች ተብለው ባይጠቀሱም እንኳን፣ ሕግ ተጠቃሚዎች አድርጎ ይህን መሠረታዊ ጥቅማቸውን መጠበቅ ስሜት የሚሰጥ አሠራር ይሆናል። በተጠቀሰው የከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎት አስተያየትም የኢትዮጵያ የሕይወት ኢንሹራንስ ሕግ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው።

አንድ የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት ግን በነዚህ የመከራከሪያ ሃሣቦች አላመነም። ይህ ፍርድ ቤት ያለው ኢንሹራንስ የገባው ሰው በንግድ ሕግ ቁ. 701/1/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የጠቀሰው ተጠቃሚ በሚኖርበት ጊዜ ይህ ተጠቃሚ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገቢ በሙሉ መውሰድ አለበት ነው።

ወደ ቁ. 701/2/ ትርጓሜ በመመለስም ባል ወይም ሚስትና ልጆች የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረው ተዋዋዩ ማንንም ሰው በተጠቃሚነት ባይጠቅስ ኖሮ ብቻ ነበር በማለት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ወስኖአል።

በአጠቃላይም ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃርነዋል። እንደ መጀመሪያው ውሣኔ ንዑስ ቁ./1/ እና /2/ ተደጋጋፊ ናቸው። በርግጥ አንድ ሌላ ሦስተኛ ሰው በተጠቃሚነት ሊጠቀስ ይችላል፤ ግን ምንም እንኳን በተጠቃሚነት ባይጠቀሱም የሚያገኘውን ጥቅም ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆቹ ጋር መካፈል አለበት።

እንደ ሁለተኛው ውሣኔ አባባል ግን የተዋዋዩ ፍላጎት ገዥ ነው። በመሆኑም ማንኛውም በእሱ እንደተጠቃሚ የተጠቀሰ ሁሉ ከፖሊሲው የሚገኘውን ጥቅም በሙሉ ያገኛል። ባል ወይም ሚስትና ልጆች ሊያገኙ የሚችሉት ተዋዋዩ ተጠቃሚን ሳይጠቅስ የሞተ እንደሆነ ብቻ ነው።

እነዚህ የተለያዩ የሁለት ፍ/ቤቶች ውሣኔዎችም ኢንሹራንስ ገቢዎችንም ሆነ ኢንሹራንስ ሰጪዎችን ፍፁም ውጥንቅጥ የወጣ ሁኔታ ውስጥ ጥለዋቸዋል። ይህም <u>የስታሬ ዲሲስ</u> /በአንድ ጉዳይ ላይ አንድ የበላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሌሎች የበታች ፍ/ቤቶች እንዲከተሉት የሚገደዱበት/ ሥርዓት በእኛ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት ተባብሷል።

ይህ ሁኔታም እላይ የተጠቀሰው ጉዳይ በጠቅላይ ፍ/ቤት የተሻረ አንድ ተራ የሆነ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ላለመሆኑ አንድ ምክንያት ነው። ያ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ በጣም ቀላል ይሆን ነበር። ይህ ግን አንድ የበታች ፍ/ቤት በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ የበላይ ፍ/ቤት የተወሰነን ሁኔታ በግልፅ ውድቅ ያደረገበት ሁኔታ ነው። ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀደም ሲል የጠቅላይ ፍ/ቤት በተመሳሳይ ጭብጦች ላይ በተመሠረተ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ፍርድ የተመለከተው መሆኑን ገልጿል። የበታች ፍ/ቤቱ ግን የጠቅላይ ፍ/ቤት ለንግድ ሕግ ቁ. 701 የሰጠውን ትርጓሜ እንደማይቀበልና ይህ የበላይ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ጋር ለመስማማትም በምንም ዓይነት ደረጃ እንደማይገደድ ገልጿል። ስለዚህ ተቃራኒ ማጠቃለያ ላይ የደረሰው እያወቀ ነበር ማለት ነው። በግልፅ እንደሚታየው እነዚህ ጉዳዮች የእኛ የሕግ ሥርዓት ለቀደምት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች /precedents/ ምን ዓይነት ቦታ መስጠት አለበት የሚል ወቅታዊ ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል። ሆኖም ግን ይህ ጥያቄ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ አይደለም።

እዚህ ላይ የምናተኩረው የተጠቀሱት ሁለት ውሣኔዎች የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አወሳሰንን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆነ አቋም የያዙ የተለያዩ የአስተሳሰብ መሥመሮች የሚከተሉ በመሆናቸው ላይ ነው። ሁለቱ አመለካከቶችም በተራቸው የሚያንፀባርቁት የተለያዩ ማሕበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዕድገት ደረጃዎችን ነው። ስለዚህ በሥርዓተ ሕጋችን ዕድገት ውስጥ አሁን መታየት ያለበት ጥያቄ ከነዚህ አመለካከቶች መካከል የዛሬይቱ ኢትዮጵያን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የሚያገለግለው የትኛው ነው የሚለው ነው።

የአንድን ሕግ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አንዱና በጣም ጠቃሚው መንገድ የሕጉን ታሪካዊ ዕድገት ማጥናት ነው። ለዚህም የመጀመሪያ ረቂቆች፣ ቀጣይ ለውጦች፣ የአርቃቂ ኮሚሽን ቃለ ጉባኤዎች፣ እንዲሁም የፓርላማ ክርክሮች በጣም ጠቃሚ መግለጫዎች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ላይ በቀላሉ የምናገኘውና በመጠኑም ሊረዳ የሚችለው የዚህን ሕግ ረቂቅ ብቻ ነው።

ያም ሆኖ በንግድ ሕግ ቁ. 701 ላይ ፕሮፌሰር ዦዋሬ[1] የፃፉት ነገር እራሱ በሚያፀፅት ሁኔታ በጣም ጥቂት ነው። ነገር ግን በአንድ ጠቃሚ ዐረፍተ ነገር አማካኝነት ይህ ሕግ ምን እንዲል እንደተፈለገ ሊያሳይ የሚችል ፍንጭ ሰጥተውናል። አርቃቂው ም ሲፅፉ "የሕይወት መድን ተጠቃሚ አወሳሰንን በተመለከተ በጣም ልቅ /the most liberal/ የሆነ መፍትሄ አስገብቻለሁ" ብለዋል። እንደመጥር አጋጣሚ ሆኖ ግን "በጣም ልቅ በሚሉበት ጊዜ ምን ማለታቸው እንደሆነ ምንም አልተናገሩም። በመሆኑም አንድ ሰው ለሞት ጊዜ ለሚደረግ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማን መሆን አለበት የሚለውን ለመወሰን "ፖሊሲ" ሲባል ምን እንደሆነ ለማወቅ ከዚህ ፊት አድርጎ መመልከት አለበት።

በዚህ ረቂቅ ውስጥ ዦዋሬ "ልቅ" የሚለውን ቃል በሌሎች ብዙ አጋጣሚዎች ሁሉ ተጠቅመውበታል። ለምሳሌ የሌሎች ጥቂት አገሮችን ሕጎች በመጥቀስ የአንድ የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተዋዋይ ሕይወቱን በራሱ በማጥፋቱ ምክንያት ትክክለኛነቱን አያጣም በማለት ተናግረዋል። ይህ ዓይነቱን አቋምም ከሚገባው በላይ "ልቅ" ይሉትና በኢትዮጵያው ረቂቅ ሕግ ላይ ተቃራኒ መሥመር ተከትለዋል። እነዚያ አገሮች ሰውየው ሕይወቱን በራሱ ቢያጠፋም እንኳን የእሱን ፍላጎት ውጤት በመስጠት መቀበል መምረጣቸውንና ዦዋሬ ይህን አቋም "ልቅ" የሚል ቃል በመጠቀም ከገለፁት በመነሣት ስለ ቁ. 701 ሲናገሩም ቃሉን መጠቀማቸው ተመሳሳይ ሀሣብ፥ ማለትም የተዋዋዩን ፍላጎት ማስቀደምን፥ ለማስተላለፍ መሆን አለበት ወደሚል ማጠቃለያ ያመራል።

[1] የመጀመሪያው የንግድ ሕጉ አርቃቂ የነበሩት ፕሮፌሰር አስካሬሊ የጻፉት ገና ሥራው ከማለቁ በፊት ነው። በመሆኑም ፕሮፌሰር ዦዋሬ ወደ መጨረሻ አካባቢ የአርቃቂነት ሥራውን ስለተረከቡ በኢንሹራንስ ላይ ላለው የማርቀቅ ሥራ ኃላፊው እርሳቸው ነበሩ።

ይህ የክርክር መሥመር በተለይም ሌሎች አገሮች "ልቅ" የሚለውን ቃል በምን መልክ እንደሚጠቀሙበት በመጥቀስ የበለጠ ሊጠናከር ይችላል። በኢትዮጵያ ተመሳሳዩ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያሳደረው የፈረንሣይ የሕይወት ኢንሹራንስ ሕግ የተለየ ተዛምዶ አለው።[2]

ለልቅነት ትርጉም የፈረንሣይን ሕግ የምንፈልግበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን፣ በሞት ጊዜ፣ ስለመወሰን ጉዳይ በጣም "ልቅ" በመባል የሚታወቀው ይህ የፈረንሣይ ሕግ በመሆኑ ነው። እንደ አንድ ፀሐፊ አባባል "የተጠቃሚውን ማንነት መግለፅን በሚመለከት የፈረንሣይ ሕግ ደንቦች /የ1930 ሕግ ቁጥር 63/ ከመጠን በላይ ለፊና ልቅ ናቸው። ይህም መድን የገባው ሰው ያቀደውን ዓላማ በላቀ ሁኔታ ለመወጣት እንዲችል ለማድረግ ሲባል ነው።"[3]

ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ በፈረንሣይ የሕግ ሊቃውንት አመለካከት በአብዛኛው የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን በተመለከተ "ልቅ" አቋም በመባል የሚታወቀው ፖሊሲውን ለፈረመው ሰው በጣም ዝቅተኛ ገደብ ያለበትን ነፃነት የሚሰጠውን አቋም ነው። በዚህ መሠረት አንድ ሰው የፈረንሣይ የሕግ ሊቅ የሆኑት ዡ ፍሬ "በጣም ልቅ የሆነውን መፍትሄ" መርጫለሁ ካሉት በመነሣት፣ ማለት የፈለጉት ተዋዋዩ የፖሊሲው ተጠቃሚ ማን መሆን እንዳለበት ለመምረጥ ከፍተኛ ነፃነት ሊኖረው ይገባል ነው፣ ወደ ሚል ምክንያታዊ የሆነ ማጠቃለያ ሊደርስ ይችላል። ይህም ግብ የተገኘው በንዑስ ቁ/1/

2 ዡ ፍሬ ራሳቸው "ብዙ ዘመናዊ ሕጎችን በተለይም የጁላይ 13፣ 1930ውን የፈረንሣይ ሕግ ... ተመልክቻለሁ" ብለዋል፣ ፒተር ዊንሽፕ <u>ባክግራውንድ ዶክመንትስ ኦቭ ዘ ኢትዮጵያ ኮመርሻል ኮድ ኦፍ 1960</u> (አዲስ አበባ፣ ሕግ ፋኩልቲ አ.አ.ዩ እ.ኤ.አ 1972) ገጽ 83።

3 ጆልነር እና ጄ ናርድ /አዘጋጆች/ <u>ላይፍ ኢንሹራንስ ሎ ኢን ኢንተርናሽናል ፐርስፔክቲቭ፣</u> ሪፖርትስ ፍሮም አን ኢንተርናሽናል ኮሎኪየም /ስቶክሆልም፣ 1969/ ገጽ 29።

በሚያምታታ ሁኔታ በተገለፀውና "ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተሰየ ተጠቃሚ ጥቅም ሊደረግ ይችላል" በሚለው ነው።

በአርቃቂው ረቂቅ አውሮፓውያን ተጠቃሚን በመወሰን ረገድ በሚከተሉት "ለቀቅ"፣ "ለበብ" ያለ ፖሊሲ ላይ በመመርኮዝ ቁ. 701 የተመሠረተበትን ፖሊሲ በዚሀ ሁኔታ ካስቀመጡ በኋላ የሚቀረን ንዑስ ቁ /2/ ከንዑስ ቁ. /1/ ጋር የማስታረቁ ሥራ ነው።

ለመነሻም ያህል፣ ንዑስ ቁ. /1/ አርቃቂው ከገለፁት ግባቸው ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣም ነው የሚል አንድ ክርክር አለ። ይሀ ሕግ የሕጉ አርቃቂ የተጠቃሚ አወሳሰን በተመለከተ የሚነሳውን ነቀፋ "በጣም ልቅ" በሆነ መንገድ ለማቃለል የነበራቸውን ፍላጎት የገለፁበት ሕግ ነው። "በጣም ልቅ" የሚለው አባባል በተራው፣ ተዋዋዩ ተጠቃሚውን ለመምረጥ ያለው ነፃነት በጣም ከፍተኛ /በጣም ትንሽ ገደብ ብቻ ያለበት/ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ወደ ሁለተኛው ንዑስ ቁጥር ስንመለስ ደግሞ አርቃቂው ሁለት ተቃራኒ ሐሳቦችን በአንድ ቁጥር ውስጥ አጠቃለዋል ብሎ መውሰድ ከሕግ ማርቀቅ መሠረታዊ መርሆች ጋር መቃረን ይሆናል። በሌላ አባባል፣ በንዑስ ቁ. /2/ የተገለፀው በንዑስ ቁ. /1/ የተገኘውን የአርቃቂውን ግብ በሚያጠፋ መንገድ መተርጎም የለበትም ማለት ነው።

ሆኖም ግን ይሀ ዓይነቱ አለመጣጣም በማንኛውም ሕግ፣ በተለይም በመጀመሪያው ረቂቅ ሕግ ላይ ከአርቃቂው ውጪ በሆኑ ሰዎች ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ሊፈጠር የሚችል እንደሆነ መታመን አለበት። እንዲሀ ዓይነት ለውጦች ሲደረጉ በሌሎች ሐሳቦችና ግፋ ቢልም ጠቅላላው ሕግ በተዋቀረበት ፖሊሲ ላይ ምን ዓይነት ችግር ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በቂ ትኩረት አይሰጥም። ይሀ ሊሆን ከመቻሉ አንፃር ሲታይ፣ ለጊዜውም ቢሆን ንዑስ ቁ. /2/ ንዑስ ቁ. /1/ን ይቃረናል ብንል፣ እንዲሁም ንዑስ ቁ. /2/ በአርቃቂ ከሚኸኑ ወይም በፓርላማው በኋላ የተጨመረ ወይም የተለወጠ ሆኖ ቢገኝ አስገራሚ ይሆናል።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ነገር ግን ሁኔታው እንዲህ እንዳልነበር የሚያሳይ ከምሳ ኅዳል አስተማማኝ የሆነ መረጃ አለ። ምፍሬ በንግድ ሕጉ የኢንሹራንስ ክፍል ላይ ያቀረቡት ረቂቅ በአርቃቂ ኮሚሽን ያለምንም ለውጥ ተቀባይነትን አግኝቷል። በአንድ የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል እንደተገለፀ የሚታመንበትና በረቂቁ የመጀመሪያ ገፅ ላይ ለምፍሬ የተገለፀው የእጅ ፅሁፍ የሚገልፀው ረቂቁ "ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት እንዳገኘ" ነው።[4]

የመጀመሪያ ረቂቁና የአሁኑ የቁ. 701 ይዘት ሙሉ በሙሉ አንድ መሆናቸው አርቃቂ ኮሚሽኑም ሆነ ፓርላማው በምፍሬ ረቂቅ ላይ ምንም ለውጥ ያላደረጉ ለመሆናቸው ሌላው ማስረጃ ነው።[5]

የቁ. 701/2/ ትርጉም

የኢትዮጵያ ሕግ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አወሳሰን እስመልክቶ ሕግ አውጪው የተመሠረተበትን ፖሊሲ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። ከላይ የተገለፀውን ግብ ለማንፀባረቅ ተብሎ የቀረበው የመጀመሪያ ረቂቅም በየትኛውም ወደ ሕግነት ለመሸጋገር ባለፈባቸው ሂደቶች ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳልተደረገበት አይተናል። በመሠረቱም፣ የቁጥር 701 የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር የኢንሹራንስ ጥቅም ለማን

4 ፒተር ዊንሽፕ ከተመሳሳይ ግጠቃለያ ላይ ደርሰዋል። ሲፅፉም "አርቃቂ ኮሚሽኑ የፕሮፌሰር ምፍሬን ረቂቅ ያለ ምንም ማሻሻያ የተቀበለው ይመስላል። በሕግ ፋክልቲ /አ.አ ዩኒቨርሲቲ/ መፃሕፍት ቤት /አርካይቭስ/ ውስጥ የሚገኘው የረቂቁ ቅጅ ከመጀመሪያው ገፅ የላይኛው ጠርዝ ላይ የተገለፀ እንደሆነ /ማትር ፖርላካስ በተባሉ የንዑስ ኮሚሽኑ አባል በሆኑ ሰው የእጅ ጽሁፍ የተገለፀ እንደሆነ የሚታሰብ/ ረቂቁ ያለምንም ማሻሻያ ተቀባይነት እንዳገኘ የሚገልጽ ጽሁፍ ይገኛል" ብለዋል። ፒተር ዊንሽፕ፣ በማስታወሻ ቁ. 2 የተጠቀሰው መጽሀፍ ገጽ 6.

5 ብዙዎች አለመጣጣም የሚያያዘው እንግዳና አስተያየት በሆነው በመጀመሪያው ረቂቅ የሚገኘውና "ወራሾች" የሚለው ቃል ከአማርኛውና ከእንግሊዝኛው አለመካተቱ ነው። እዚህ ላይ እንዲህ ያለ ልዩነት በረቂቁ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ምክንያት ነው ሊባል አይችልም። ምክንያቱም የንግድ ሕጉ የፈረንሣይኛ ቅጅ እስከአሁን ድረስ ይህን ቃል እንደያዘ በስሚገኝ ነው።

መስጠት እንዳለበት የመወሰን ሙሉ ነፃነት ለተዋዋዩ ስለሚሰጠው ከተገለፀው የሕግ አውጪ ፖሊሲ ጋር በሙሉ እንደሚስማማ ግልፅ ነው።

ስለዚህ 701 /2/ን፣ ልክ እንደኛው ፍ/ቤት እንዳደረገው ሁሉ ተዋዋዩ ለሞት ጊዜ በገባው የሕይወት ኢንሹራንስ ላይ ሌላ ሦስተኛ ሰው በብቸኛ ተጠቃሚነት በግልፅ ቢጠቅስም እንኳን የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች በማንኛውም ጊዜ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ብሎ መተርጎሙ ሕጉ የተመሠረተበትን መሠረታዊ ፖሊሲ ከመቃወሙም ባሻገር በቀዳሚው ንዑስ ቁጥር የተደረሰበትን ግብ የሚያጠፋ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ብቻ የተጠቀሰው ትርጓሜ ውድቅ መደረግ አለበት።

ያም ሆኖ ግን ይህን ማጠቃለያ በመደገፍ ሌሎች ክርክሮችም ሊነሱ ይችላሉ። ከተገለፀው "ልቅነት" ጋር በሚጣጣም መልኩ ሕጉ ለኢንሹራንስ ውል ተዋዋዩ በውሉ ውስጥ ተሰይቶ የተጠቀሰው ተጠቃሚ ጥቅሙን እቀበላለሁ እስካላለ ድረስ ተጠቃሚውን መለወጥ የሚያስችል ሥልጣን ሰጥቶታል /ቁ. 703/2/። በሌላ ጎኑ ግን ባል ወይም ሚስትና ልጆች ከተዋዋዩ ፍላጎት ውጪ በሆነ ሁኔታና በሕጉ ትዕዛዝ ብቻ ተጠቃሚዎች ተብለው የሚቆጠሩ ከሆኑ ተዋዋዩ ተጠቃሚውን መቀየር እንደሚችል ሥልጣን መስጠቱ ትርጉም የለሽ በሆነ ነበር። በድጋሚ ለመግለፅም ቁጥር 701/2/ን ወደ እንደዚህ ዓይነት ተቃርኖ በሚያመራ መልኩ መተርጎም ተቀባይነት አይኖረውም።

ከዚህ በላይ የተገለፀው ትርጓሜ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ በዘመናዊ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወተውን ዘመናዊ የመሣሪያነት ጠቀሜታ ዋጋ የሚያሳጣው ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በአደጉ አገሮች ውስጥ አንድ ሰው ለአበዳሪው ጥቅም የኢንሹራንስ ውል መግባትና ውሉንም ለዚህ ተጠቃሚ አንድ ሌላ ግዴታን ለመፈፀም እንደዋስትና መውሰድ የተለመደ ነገር ሆኗል።

ይህ ተግባርም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ መጠነኛ ጊዜያትን አስቆጥሯል። ለምሳሌ ያህልም ቤት ለመሥራት ከቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ /Morgage Bank/ ገንዘብ የተበደሩ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን መውሰድ ይቻላል። ብድሩን ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት ባንኩን ተጠቃሚ ያደረገ የኢንሹራንስ ውል ውስጥ እያንዳንዳቸው መግባት ነበረባቸው።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ፣ እንደ አንድ ዘመናዊ የሕግ ክፍልነቱ፣ ይህን የሕይወት ኢንሹራንስ ጥቅም ያውቃል። ለምሳሌ ቁ. 692/1/ ኢንሹራንስ ሰጪው ኢንሹራንስ የገባው ሰው በሚሞትበት ጊዜ" ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸው ሰዎች ..." የተወሰነ ገንዘብ /ካፒታል/ ለመስጠት ግዴታ ውስጥ ሊገባ የሚችልበትን ሁኔታ ያሳያል።

ቁጥር 697 ደግሞ የኢንሹራንስን ውል መያዣ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በግልፅ በመጥቀስ ይህን ጉዳይ የበለጠ ያብራራዋል።

ቁ701(2)ን የተዋዋዩን ነፃ ፍላጎት በሚገድብ ሁኔታ መተርጎም ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት የሕግ ቁጥሮች መንፈስ ጋር ከመፃረሩም በተጨማሪ አስገራሚ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ የብድር ባንኩ ብቸኛው የኢንሹራንሱ ተጠቃሚ ሆኖ በሚጠቀስበት ጊዜ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገቢ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች ተካፋይ ሊሆኑ ነው፤ ይህም የውሉን ዓላማ በማፋለስ ይህን የሕይወት ኢንሹራንስን መያዣ በማድረግ የተገባውን የብድር ውል ዋጋ ያሳጣዋል ማለት ነው።

በላይኛው የመከራከሪያ ሃሣቦች ላይ በመመሥረትም፣ ቁ. 701/2/ን የኢንሹራንስ ውል የገባው ሰው አንድ ሌላ ሰውን ብቸኛ ተጠቃሚነት ጠቅሶ በሚሞትበት ጊዜም ቢሆን እንኳን የሟች ባል ወይም ሚስትና ልጆች ከሚገኘው ገቢ የተወሰነውን ክፍል ማግኘት አለባቸው ብሎ መተርጎም ሕጉ የተመሠረተበትን ፖሊሲና ብዙ ሌሎች መሠረታዊ ሕጎችን ስለሚፃረር ውድቅ መሆን ያለበት ነው ለማለት ያስገድዳል።

ይህ ከተባለ በኋላ መታየት ያለበት ለዚሁ ሕግ ሁለተኛው ፍ/ቤት የሰጠው አማራጭ ትርጉም ነው። እዚህ ላይ ፍ/ቤቱ በቁ. 701/2/ መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆች ውጪ የሆነ ተጠቃሚ ሊጠቀስ እንደሚችል ዕውቅና ይሰጣና፣ ይህንንም ሊያደርግ የተጠቀሰው ተጠቃሚ ከፖሊሲው የሚገኘውን ገንዘብ በሙሉ ሊወስድ እንደሚችል ይናገራል።

ሁለተኛውን ንዑስ ቁጥር በተመለከተ ፍ/ቤቱ የወሰደው አቋም ኢንሹራንስ የገባው ሰው በተጠቃሚነት ሳይጠቅሳቸው በሚሞትበት ጊዜም እንኳን በሕጉ ብቻ ባል ወይም ሚስትና ልጆች የፖሊሲው ተጠቃሚዎች ይሆናሉ የሚለው ነው።

ከዚያም ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ አቋሞች ማስታረቅ ነበረበት። ይህንንም ሥራ ያከናወነው በተጠቃሚነት ያልተጠቀሱ የተጋቢዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች የኢንሹራንሱን ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉት በመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር የተመለከተው ሁኔታ ሳይኖር፣ ማለትም ተጋቢዩ የተወሰነ ተጠቃሚ ሳይጠቅስ በሚቀርበት ሁኔታ ብቻ ነው ብሎ በማጠቃለል ነበር። በዚህ አኳኋንም ፍ/ቤቱ ከላይ ከተጠቀሰው የሕግ አወጣጥ ፖሊሲ ጋር በሚጣጣም መንገድ ኢንሹራንስ የገባውን ሰው ፍላጎት የበላይነት ጠብቋል። እስከዚህ ወሰን ድረስም ውሳኔው ትክክል ነው።

ይህ ፀሐፊ ግን ፍርድ ቤቱ ለሕጉ ሁለተኛ ንዑስ ቁጥር ከሰጠው ትርጓሜ አንድ ነጥብ ማንሣት ይፈልጋል። በዚህ ፍ/ቤት አባባል የዚህ ንዑስ ቁጥር ጠቀሜታ ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከፖሊሲው የሚገኘው ገንዘብ ወደማን መሄድ እንዳለበት ምንም ሳይናገር በሚሞትበት ጊዜ የተጋቢዩን ባል ወይም ሚስትና ልጆች ተጠቃሚዎች ለማድረግ ነው።

ሆኖም ግን ኢንሹራንስ የገባው ሰው ተጠቃሚውን ሳይወስን የሞተ እንደሆነ ከኢንሹራንሱ የሚገኘው ገንዘብ ወደየት መሄድ እንዳለበት የሚለውን በተመለከተ ሕጉ ፍፁም ግልፅ ነው። የፍትሐብሔር ሕግ /ቁ. 827/ም ሆነ የንግድ ሕግ /ቁ. 705/ ገንዘቡ "የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ወራሽ ነው" በማለት የውርሱ ሀብት ክፍል ያደርጉታል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሁለቱ ሕጎች አንድነትና የሚጠቀሙት ቋንቋም የሚያምታታ አለመሆኑ ለትርጉም ቦታ እንደሌለ ያሳያል። በመሆኑም ለንግድ ሕግ ቁ. 701/2/፣ ልክ ከላይ እንደተጠቀሰው ፍ/ቤት ዓይነት እነዚህን ሁለት ሕጎች የሚቃረን ትርጉም መስጠቱ ተቀባይነት የሚያገኝ አይሆንም።

የቁ. 701/2/ ትርጉም ምን መሆን አለበት፣ ዓላማውስ ምን ነበር? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የንዑስ ቁ./1/ እና /2/ን የቃላት አጠቃቀም በጣም ቀረብ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

በመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር ተዋዋዩ የኢንሹራንስ ፖሊሲውን "ተለይቶ ለታወቀ" ተጠቃሚ ጥቅም ሊያደርገው እንደሚችል ሥልጣን ተሰጥቶታል። "ተለይቶ ለታወቀ" ማለት ምን ማለት ነው? በሌላ አባባል ተዋዋዩ ምን ያህል "ውስን" መሆን አለበት? በጣም ብዙ ተዋዋዮች ከተጠቃሚዎቻቸው ጋር ወደፊት ስለሚኖራቸው ግንኙነት ለመተንበይ ካለው አስቸጋሪነት አንፃር ሊለወጥ በማይችል መልኩ መዋዋል ስለማይፈልጉ የዚህ ጥያቄ አስፈላጊነት በጣም ከፍተኛ ይሆናል። እንደ ዕውነቱ ከሆነ በአንዳንድ አገሮች "የተወሰነ" ሰው በስም ተጠቃሚ ሆኖ የሚጠቀሰው በጣም በጥቂቱ ነው።

በዴንማርክ ሕግ ለምሳሌ፥ "ተዋዋዩ ባሏ ወይም ሚስቱ የኢንሹራንሱን ገቢ በሙሉ እንዲወስድ ከፈለገ ተጠቃሚ" ባል ወይም ሚስት" ብሎ በመጥቀስ ማግኘት ይችላል። ስለዚህ ባል ወይም ሚስትን በስም መጥቀስ አያስፈልገውም ማለት ነው። ተዋዋዩ ልጆቹ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ከፈለገ "ልጆች" በሚል የተጠቃሚ አጠቃቀስ /የእያንዳንዳቸውን ስም ሳይጠቅስ/ ሊገልፅ ይችላል።

ሁኔታው እንዲህ ሳለ፥ ተጠቃሚዎችን በመጥቀስ ላይ የጠቅላላ ቃላትን /general terms/ አጠቃቀም የሚቆጣጠር ሕግ የሌለው ማንኛውም የኢንሹራንስ ሕግ የተሟላ ሊሆን አይችልም። ቁ. 701/2/ም በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ ውስጥ የተካተተው ይህን ዓላማ ለማሳካት መሆኑ ታምኖበታል።

ይህን ሀሳብ ለማብራራት ተዋዋዩ ፖሊሲው "የተወሰኑ" ተጠቃሚዎችን እንዲጠቅም ለመጥቀስ የሚያስችለውን የቁ. 701/1/ን ይዘት በበለጠ እንመርምር። ምን ያህል የተወሰነ ወይም የተለየ መሆን አለበት የሚል ጥያቄ ተነስቷል። በተዘዋዋሪ ሊሆን ቢችልም ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ ከሁለተኛው ንዑስ ቁጥር ማግኘት ይቻላል። በዚያ ሕግ ሥር የተወሰኑ ሰዎች "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" /አፅንኦት የታከለበት/። ስለዚህ በዚህ ንዑስ ቁጥር ውስጥ "ተለይቶ የታወቀ" የሚለው ቃል መተርጎም ያለበት ተጠቃሚውን በስም እንደመጥቀስ ማለትና ይህንንም አለማድረግ የህጉን ተፈላጊ ነጥቦች እንዳለማሟላት ተደርጎ ነው።

ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ግልፅ ነው። ጥቅሙ ለማን መሰጠት እንዳለበት በፍፁም ርግጠኛነት የወሰኑ ተዋዋዮችን ፍላጎት ይጠብቃል። ሁለተኛ ደግሞ ስሞች ከተጠቀሱ የተዋዋዩ ፍላጎት የማያጠራጥር ስለሚሆን ተጠቃሚው ማን መሆን እለበት የሚሉ ጭቅጭቆችን እጅግ በጣም ይቀንሳቸዋል፥ ወይም ያጠፋቸዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ተዋዋዮች ሁሉ እስከዚህ ደረጃ ድረስ ወስነው እንዲያሳውቁ መምከር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሃሳብ አይሆንም። ከፍ ብሎ እንደተገለፀው በብዙ አገሮች ለሞት ጊዜ የሚሆን ኢንሹራንስ ከሚገቡ ሰዎች ውስጥ ተጠቃሚዎቻቸውን በስም የሚገልፁ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

ነገ ለእነርሱ ምን እዘጋጅቶ እንደምትጠብቃቸው በርግጠኝነት ስለማያውቁ ብዙ ተዋዋዮች ሊኖር የማይችል ውል መፈፀምን አይቀበሉትም። በኢትዮጵያ ሕግ ለምሳሌ "ለአንድ ተለይቶ ለታወቀ ተጠቃሚ የተሰጠ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚው እንደሚቀበል መፍቀዱን ካስታወቀ በኋላ ሊኖር አይችልም" /የንግድ ሕግ ቁ. 703/1/፥ የፍትሐብሄር ሕግ ቁ. 1961/1/ንም ተመልከት/፥ ለቤተሰቡ የገንዘብ ዋስትና መስጠት የተመኘና ለዚህም ሲል ለሞት ጊዜ የሚሆን የሕይወት መድን የገባ አንድ ሰውን ወስዶ መመልከት የዚህ መሰሉ ውል ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ሙሉ ለሙሉ ሊያስረዳ ይችላል። ሰውየው ሚስቱ የሆነችውን "ታሚማ"ን ተጠቃሚ አድርጎ እንበል። ታሚማም ፖሊሲውን ወዲያውኑ ተቀበለች። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ተፋቱና በየበኩላቸው ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መሠረቱ። በተጨማሪም ተዋዋዩ ከአዲሷ ሚስቱ ብዙ ልጆችን ሊወልድ ከታሚማ ግን ምንም አልወለደም እንበል። የኢንሹራንሱ ገንዘብ ያለምንም እንከን ለታሚማ ይሰጣል፤ የፖሊሲው ዓላማም ከንቱ ይቀራል ማለት ነው፤

ከእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ለመከላከል ነው ብዙ ተዋዋዮች ተጠቃሚውን ሲጠቅሱ "ባለቤቴ" ወይም "ሚስቴ" የሚሉትንና መሰል የአጠቃላይነት ባሕርይ ያላቸውን ቃላት መጠቀምን የሚመርጡት።

---

6 ሄልነር አላይ በማስታወሻ 3 የተጠቀሰው ገጽ 18፤

7 ይህንኑ መጽሐፍ ገጽ 17 ይመልከቱ፤

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ልጆቹ ከፖሊሲው እንዲጠቀሙ የፈለገን ተዋዋይ ደግሞ እንመልከት። ውሉን በፈረመበት ጊዜ የተወለዱትን ልጆች ስም ቢፅፍ እነርሱ ብቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ ነው፤ ይህም ውሉን ከተዋዋሉ በኋላ የተወለዱትን ጨምር ሁሉንም ልጆቹን ለመጥቀም ከፈለገ ከተዋዋይ ፍላጎት ውጪ ይሆናል። ይህ አመለካከትም ብዙ ሰዎች ግለሰቦችን በስም ከመጥቀስ ይልቅ "ልጆች" ወይም "ተወላጆች" እና የመሳሰሉ አጠቃላይነት ያላቸውን ቃላት ለምን እንደሚመርጡ ያሳያል።

ሌላው ተዋዋዮቹ አዘውትረው የሚጠቀሙበት ቃል "ወራሾች" የሚለው ነው። /ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ይህ ቃል በንግድ ሕጉ ቁ. 701/2/ በፈረንሳይኛው መጽሐፍ ቢገኝ በአማርኛውና በእንግሊዝኛው ግን አይገኝም/። ተዋዋዩ ወራሾቹን በተጠቃሚነት በስም ከጠቀሱ በልጆች ጉዳይ የተነሳው ጥያቄ እዚህም ተመልሶ ይመጣል።

ስለዚህ ቁ. 701/2/ የሚያገለግለው አጠቃላይ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ተጠቃሚዎች ስለሚጠቀሱበት ሁኔታ እውቅናና ግብታ ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል ተዋዋዩ "ሚስቴ"፣ "ልጆቼ"፣ "ወራሾቼ" እና የመሳሰሉ ቃላትን መጠቀም ሲመርጥ እንዚህን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ሰዎች "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም" ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ይህ አቋም ከፈረንሳይ ሕግ አቋም ጋር አብሮ ይሄዳል። በ ኤ ቢሰን አባባል።

> "በርግጥ ተጠቃሚውን በስም ከመጥቀስ /በትክክል/ የሚያግድ ምንም ነገር የለም። በዚህም መንገድ ተጠቃሚው በግልፅ ይታወቃል። ሆኖም መድን የገባው ሰው ገንዘቡ በሚከፈልበት ጊዜ ተጠቃሚ እንዲሆን ያሰበውን ሰው ያለጥርጥር የሚያሳይ ከሆነ የተጠቃሚውን መለያ /በቤተሰብነት፣ በሙያው፣ በማሕበራዊ ግንኙነት/ መጥቀስ በቂ ነው። ተጠቃሚው ሰው ተለይቶ ሊታወቅ መቻሉ ብቻ ይበቃል። ስለዚህ መድን ለገባው ሰው ሚስት ጥቅም፣ እንዲያውም ከዚያም አልፎ ለባለ መድኑ ባለቤት ጥቅም፣ ሲባል የተደረገ ውል ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አለው"።[8]

ቁ. 701/2/ ተጠቃሚውን አጠቃላይ በሆኑ ቃላት ከመወሰን ጋር የሚያያዙ ሌሎች ጥያቄዎችንም ይመለከታል። ለምሳሌ "ሚስት" ወይም "ባለቤት" የሚሉ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚነሣው ጥያቄ የትኛዋ? ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ የነበረችው ሕጋዊ ሚስቱ ወይስ በሚሞትበት ጊዜ አብራው የነበረችው ሕጋዊ ሚስት? የሚለው ነው። ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ ያላገባ ከነበረና በኋላ ካገባ ቁ. 701/2/ ግልፅ ይሆናል። ይህቺ ዓይነቷ ሚስትም ትክክለኛዋ ተጠቃሚ ትሆናለች።

ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ "ተ"ን አግብቶ ከነበረና በኋላ እሷን ፈትቶ "ዋ"ን አግብቶ እያለ በሚሞትበት ዓይነት ሁኔታ ግን የሕጉ ቋንቋ በሚፈለገው መጠን ግልፅ አይሆንም። ያም እንኳን ቢሆን ዕውቅና መስጠት የተፈለገው "ፖሊሲው ከተፈረመ በኋላ" የተደረገውን ጋብቻ ይመስላል። ይህ አቋም ለፖሊሲው መሠረት የሆነውን ምክንያት በመጥቀስ ሊደገፍ ይችላል። ይህም ምክንያት በአብዛኛው አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ለቅርብ ቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማቅረብ የሚለው ነው።

የግብር ክሶችን የይርጋ ደንቦች እንዳይመለከታቸው ማድረግ ብልህነት እንዳልሆነ ለማሳየት በመሞከር ከዚህ በላይ ብዙ ተነግሯል። አሁን ደግሞ በተግባር በሚታየው ይህን አመለካከት የተሟላ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

የብዙ ሀገሮች የግብር ሕጎች ግብር የመወሰንና እንዲከፈል የመጠየቅ መብቶችን የሚመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች አሏቸው። የነዚህ ድንጋጌዎች መኖር ለመንግሥት የፊስካል ጥቅም ከማድላት ይልቅ የጊዜ ገደብ ማበጀት ለሚያስገኘው ጥቅም ማድላት የተመረጠ መሆኑን ያሳያል። ቀጥሎ የተመለከቱት ፓራግራፎች ባጭሩ ጥቂቶቹን ያብራራሉ።

የብራዚል የግብር ሥርዓት የገቢ ግብር አወሳሰንንና አሰባሰብን የሚመለከት የይርጋ ውሳኔ የሚደረገው ግብር ከፋዩ ያቀረበውን የገቢ መግለጫ መሠረት በማድረግ ወይም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በራሱ የሥራ ኃላፊነት በሚወስደው እርምጃ ነው። ይህ መከናወን ያለበት ግብሩ ከሚከፈልበት ዓመት መጨረሻ አንስቶ ባሉት የ5 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው።

የብራዚል ሕግ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የግብር ውሣኔ ሊደረግ እንደሚችልም ይገልጻል። ይህ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የሆነው የግብር ውሣኔ መደረግ ያለበት ግን ለግብር ከፋዩ የመጀመሪያው የግብር ውሣኔ ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባለው የ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ ማለት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመጀመሪያውን የግብር ውሳኔ በተደነገገለት ጊዜ ውስጥ ባልሰጠበት ሁኔታ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የሆነውን የግብር ውሣኔ ማድረግ አይችልም ማለት ነው።[17]

"አሁን ሕጉ ባለበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱት የ5 ዓመት የጊዜ ገደቦች ግብር የመወሰን መብትን ቀሪ የማድረግ ውጤት ያላቸው ወሳኝ የጊዜ ገደቦች ናቸው። መንግሥት በሚፈጽማቸው ተግባሮች መቆጠራቸው የሚቋረጥ ወይም ለጊዜው የሚታገድ አይደሉም"።[18]

መንግሥት ግብር ለመሰብሰብ ያለው መብት እንዲሁ በ5 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንዲሆን ተወስኗል። ይርጋው መቆጠር የሚጀመረውም በግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ላይ ግብር እንዲከፈል ከተገለጸበት የመጨረሻ ቀን አንስቶ ነው። የዚህ ይርጋ መቆጠር ሊቋረጥ ይችላል። ለምሳሌ፣ ለግብር ከፋዩ ግብሩን እንዲከፍል በሚቀርበው ጥያቄ ወይም ለግብር አከፋፈሉ በሚሰጥ ተጨማሪ የመክፈያ ጊዜ ፈቃድ፣ ግብሩ እንዲከፈል የቀረበ ክስም ካለ ክሱ እስከቀጠለ ድረስ የይርጋውም መቆጠር ለጊዜው የሚያግድ ይሆናል።[19]

በኢጣሊያ የግብር ሕጎች ውስጥ መንግሥት ያለውን ግብር የመጠየቅ መብት የሚመለከቱ በርካታ የይርጋ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። ሥራ ላይ ያለው የሕግ አወጣጥ ዘይቤ ሁኔታዎችን ለይቶ በማመልከት በነዚሁ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑትን የተለያዩ የጊዜ ገደቦች መደንገግ ነው። ይህ እንግዲህ ድንጋጌዎቹ ለምን ሊበረከቱ እንደቻሉ ያስረዳል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ሳይነኩ የግብር አስተዳደር መ/ቤቱ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውንና የወጪውን መግለጫ ካቀረበበት ቀን አንስቶ 3 ዓመት ካለፈ በኋላ ግብር እንዲከፈል ከመጠየቅ የተከለከለ ነው። የገቢና የወጪ መግለጫ ባልቀረበበት ሁኔታ ግን የይርጋ ጊዜ 20 ዓመት ይደርሳል። መቆጠር የሚጀምረውም መግለጫው መቅረብ ከነበረበት ቀን አንስቶ ነው።

ለግብር ከፋዩ የማኅጸ ትዕዛዝ እንዲደርሰው ማድረግ ወይም በግብር ከፋዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ሥነሥርዓት (ክስ) መመሠረት የይርጋውን መቆጠር ያቋርጣል። የይርጋው መቆጠር በአግባቡ ከተቋረጠ አዲስ ይርጋ እንደገና መቆጠር ይጀምራል። የዚህም የይርጋ ጊዜ ለቀድሞ (ለተቋረጠው) ይርጋ በሕግ ከተደነገገው ጋር እኩል ነው።[20]

የሰዊድን የግብር ሥርዓት መንግሥት ያለው ግብር የመሰብሰብ መብት በይርጋ ቀሪ ሊሆን ስለመቻሉ የሚጠቀስ ሌላ አስደናቂ ምሳሌ ነው። በሰዊድን ያለው አጠቃላይ የሆነው ደንብ የግብር መሰብሰቢያ ከሆነው ዓመት መጨረሻ አንስቶ የ5 ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ በግብር ከፋይ ላይ ምንም ዓይነት የክፍያ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም የሚል ነው። ግብሩ ሳይከፈል የቀረው በግብር ከፋይ የወንጀል አድራጎት ቢሆን እንኳ ደንቡ ተፈጻሚ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በሰዊድን ያለው አፈጻጸም ከብዙ አገሮች የግብር ሥርዓት ሥር ነቀል (መሠረታዊ) በሆነ መንገድ ልዩነት ያሳያል።

አግባብ ያለው የግብር ባለሥልጣን መ/ቤት የተወሰነው ግብር ገቢ እንዲሆን በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማናቸውም ግዴታውን በማይፈጽም ግብር ከፋይ ላይ በሰዊድን የፍትሐብሄር ፍ/ቤቶች ክስ ማቅረብ ይችላል። ንብረቱንም ለማስከበር ወይም የኪሣራ ሥነ ሥርዓት እንዲካሄድበት ለማድረግ ማመልከት ይችላል። የዚህ ዓይነቱ እርምጃ መወሰድ መጀመሩ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የ5 ዓመቱ ይርጋ ካለፈ በኋላ እንኳ ግብሩን ለመሰብሰብ መብት እንዲኖረው ያደርጋል።[21]

የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ የፊስካል ኮድ የግብር ክሶች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለባቸው የሚደነግጉ ዝርዝር ደንቦችን የያዘ ነው። እነዚህ ደንቦች የአወሳሰን ይርጋና የአሰባሰብ ይርጋ በማለት ልዩነት አያደርጉም። ለሁለቱም የተደነገገው ይርጋ በአጠቃላይ ሲታይ አምስት ዓመት ነው። መቆጠር የሚጀምረው ግብሩ በሚመለከተው ዓመት መጨረሻ ማለትም የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች ሁሉ ከተደረሰባቸው ጊዜ አንስቶ ነው።[22] ግብር ከፋዩ ግብር በመሸወድ (በማጭበርበር) ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ይርጋው የሚቆይበት ጊዜ 10 ዓመት ይሆናል።

የታክስ ይርጋ

እንዚህ ደንቦች የይርጋው መቆጠር በተለያዩ ምክንያቶችና ሁኔታዎች ሊቋረጥ ወይም ሊታገድ ስለመቻሉ ይደነግጋሉ። መቆጠሩ ታግዶ ይርጋው የሚራዘምበት ሁኔታ በይርጋው መጨረሻ ባሉት በድስት ወራት ውስጥ የሕዝብ ጠላት ወይም የተፈጥሮ መቅሰፍት ባደረሰው ችግር የተነሳ መንግሥት ግብር እንዲከፈለው ያለውን ተያቄ ለማቅረብ (ለመክሰስ) ያልቻለበት አጋጣሚ ነው።

አግባብ ያለው ያካባቢ የፋናንስ ኃላፊ የግብር ከፋዩን ማንነት ወይም ያለበትን የግብር ግዴታ ለማወቅ የሚወስደው ማናቸውም ግልጽ የሆነ እርምጃ የይርጋውን መቆጠር ያቋርጣል። የተለመደ አሠራር የሆነው የገቢና የወጪ መግለጫ እንዲቀርብ መጠየቅ እንኳ የዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ግብር ከፋዩ ግዴታ ያለበት መሆኑን ማመኑ፣ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለክፍያ የተወሰነውን ጊዜ ለማራዘም መፍቀድ የመሳሰሉ ተግባሮች ይርጋው ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚመደቡ ናቸው። ይህ ዓይነቱ መቋረጥ ካጋጠመበት ዓመት መጨረሻ አንስቶ አዲስ ይርጋ መቆጠር ይጀምራል።

በምዕራብ ጀርመን የይርጋ ደንቦች የሚታየው አስገራሚ ገጽታ ራሱ ግብር ከፋዩ ይህንን መከላከያ እንዲያነሳው የማይጠይቁ መሆናቸው ነው። በዚህ ፈንታ ለማናቸውም የግብር ክስ ምሥረታ የጊዜ ገደቡ አለማለፍ ሥነ ሥርዓታዊ ቅድመ ሁኔታ እንዲሆን ደንግገዋል። በመሆኑም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት በሥራው አካሄድ ሁሉ ለዚህ ነጥብ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የምዕራብ ጀርመን ደንቦች በሌሎች የፍትሐብሔር መስኮች ካሉ የጊዜ ገደብ ደንቦች ሥር ነቀል በሆነ መንገድ (ፍጹም) ይለያሉ።

ይርጋው ከማለቁ ጋር መንግሥት ያለው የግብር ክስ የማቅረብ መብት ቀሪ ይሆናል። ከዚሁ ጋር የተገናኙትንም ወጪዎች፣ መቀጫዎችና በግብሩ ላይ ተደማሪ የሚሆኑ ሌሎች ክፍያዎች ሁሉ የማስከፈል መብቱ እንዲሁ ቀሪ ይሆናል። በመሆኑም የጊዜው ገደብ ካለፈ በኋላ ግብር ቢወሰን ውሣኔው እንዳች ውጤት አይኖረውም።[23]

በመጨረሻ የኢትዮጵያ የግብር ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት የፋናንስ ጥቅም ባለበት ሁኔታ ይርጋ እንዲቆጠር ተደርጎ እንደሆነ ለማወቅ ጥናቱን ወደዚህ ጉዳይ

መመለስ አግባብ ሆኖ ይገኛል። በርግጥ በብዙ ረገድ ይልቁንም የይርጋ ደንቦችን በሚመለከት ጉልህ ጉድለት የሚታይባቸው በመሆኑ እንዲያ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕጎች በጠቅላላ የግብር አዋጆች ውስጥ የይርጋ ድንጋጌዎች የሚያጋጥሙት እጅግ አልፎ አልፎ ነው? ይሁንና የመንግሥት የፊናንስ ጥቅም ባለበት ሁኔታ የጊዜ ገደብ የሚቆጠር መሆኑን የሚያሳዩ ሁለት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።

የመጀመሪያው ከጉምሩክ ቀረጥ አሰባሰብ ጋር የተዛመደ ነው። በስህተት ዕቃዎች ሊከፈልባቸው ከሚገባው ልክ ያነሰ ቀረጥ የተከፈለባቸው ሲሆን ወይም ለግብር ከፋዩ በስህተት ተመላሽ ገንዘብ እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን ልዩነቱ እንዲከፈል ወይም አለአግባብ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የጉምሩክ መ/ቤት ዲሬክተር በሚመለከተው ግለሰብ ላይ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ (ክስ) ማቅረብ አለበት። ይህ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ልክ ያነሰ ቀረጥ ከተከፈለበት ወይም ግብር ከፋዩ በስሕተት ተመላሽ ገንዘብ እንዲወስድ ከተደረገበት ቀን አንስቶ ነው።

በተፈጸመው ስሕተት ተጠቃሚ የሆነው ግለሰብ በልዩነት የሚፈለግበትን ቀረጥ ወይንም እንዲወስድ የተደረገውን ተመላሽ ገንዘብ ለመንግሥት የመክፈል ወይም ገቢ የማድረግ ሕጋዊ ግዴታ የሚኖርበት የጉምሩክ መ/ቤት ዲሬክተር በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ጥያቄ (ክስ) እስከቀረበ ድረስ በመሆኑ ጊዜው ካለፈ በኋላ ጥያቄው (ክሱ) ሊቀርብ አይችልም።[24]

ሁለተኛው ምሳሌ ከገቢ ግብር አወሳሰን ጋር የተዛመደ ሲሆን ለዚህ ጽሁፍ ጥናት ይበልጥ የቀረበ ነው። አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውን መግለጫ ካቀረበበት ቀን አንስቶ በአለው የ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ የገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚፈለግበትን ግብር አጠናቅቆ የመወሰን ሕጋዊ ግዴታ አለበት። ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ መ/ቤቱ የገቢ መግለጫ ለቀረበለት የግብር ዘመን የዓመቱን ግብር የሚከፈልበት ገቢ የመወሰን መብቱን ያጣል። የተገለጸውም ገቢ ተቀባይነት እንዳለው (እንደጸደቀ) እና ግብሩም በዚሁ ላይ እንደተወሰነ ይቆጠራል። ስለሆነም ይህ ግብር ከፋዩ በገቢ መግለጫው ላይ ሳይገልጸው በቀረው ገቢ ላይ ለሚፈለገው ግብር ያለበትን ኃላፊነት አያስቀርለትም።[25]

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) የጊዜ ገደብ የተደነገገበት ጉዳይ ይህ ብቻ ነው። ታዲያ ከዚህ በመነሳት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ግብርን ለመሰብሰብ ያለው የመክሰስ መብት በጊዜው ያልተወሰነና ቀሪ ሊሆን የማይችል ነው ማለት ይቻላል? በተከታዩ ክፍል መፍትሄ (ምላሽ) ለመስጠት የሚሞከረው ለዚህ ጥያቄ ነው።

2. የፍትሐ ብሔር ሕግ ያለው አግባብነት

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ለ4ኛው መጽሐፍ የተሰጠው ርዕስ (ስለግዴታዎች) የሚል ነው። በሥሩ በመጀመሪያ የሚመጣው ስለውሎች በጠቅላላው በተሰኘ ርዕስ 12ኛው አንቀጽ ነው። የዚህ አንቀጽ 3ኛ ምዕራፍ በስድስተኛው ክፍል ይርጋን የሚመለከቱ 12 ቁጥሮች ይደረደራሉ።[26] ተከታዩ ተግባር እንግዲህ ይህ የፍትሐብሔር ክፍል ግብርን ለሚመለከቱ ክሶች ያለውን አግባብነት መመርመር ይሆናል።

ትንታኔው በዋናነት የሚያተኩረው በቁጥር 1677 እና በቁጥር 1845 ድንጋጌዎች ላይ ነው። ይህም የሆነው አከራካሪ በመሆናቸው ነው። የመጀመሪያው መሠረታዊ የሆነውን የአንቀጽ 12ትን የአፈጻጸም አድማስ የመወሰን ጥያቄን ያስነሳል።[27] ሁለተኛው ደግሞ በስሩ የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ልዩ ባሕሪ ያለው ማለትም አግባብነቱ ለውሎች ብቻ ነው ወይንስ አጠቃላይ ባሕሪ ያለው ማለትም ምንጩ ምንም ይሁን ምን በማናቸውም ግዴታ ላይ ተፈጻሚ ነው የሚለውን ጭብጥ ያነሳሳል።[28] ይሁንና በማስቀደም የግብር ሃላፊነት (ዕዳ) ራሱ ግዴታ መሆኑን ማብራራት አስፈላጊም ሆኖ ይገኛል። ምክንያቱም መላው ትንታኔ ይህንን ነጥብ መሠረት ያደረገ ስለሆነ ነው።

ግዴታ ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተው ይገኛሉ። ሆኖም በራውሊ አገላለፅ ክላሲካዊ ትርጉሙ "በሀገራችን ሕጎች መሠረት አንድን ነገር እንድንፈጽም አስፈላጊነቱ አስገዳጅ የሚሆንብን ሕጋዊ ማሰሪያ።[29] ... አንድን ተግባር በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም የሚገሰጥ በሕግ የተጣለ ጫና..." ነው። በአሁኑ ጊዜ የግዴታ ጽንሰ ሐሳብ በገንዘብ ጠያቂና በባለዕዳ መካከል ያለውን ሕጋዊ ግንኙነት ሁሉ ይመለከታል፣

የሚለው አስተሳሰብ በሰፊው ተቀባይነት እያገኘ ነው። የዚህም ግንኙነት መሠረታዊ ባሕሪያት መብትና በአንጻሩ ያለው ግዴታ (Duty) ነው።[30]

ሰፋ ባለ አነጋገር ከስር አመጣጣቸውን መሠረት በማድረግ ግዴታዎች የውልና የውል ያልሆኑ ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ። የውል ግዴታዎች ተዋዋይ ወገኖች ወደው በሚያደርጓቸው ስምምነቶች የሚፈጠሩ ናቸው። የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ደግሞ የሥር አመጣጣቸው አንድም ግለሰቦች በሚፈጽሟቸው በሕግ የተፈቀዱ ወይም ገደብ የተደረገባቸው ተግባሮች ወይም ከሕጉ ከራሱ ሥልጣን ነው።[31]

በሕግ ምሁራን አካባቢ የግዴታ ጽንሰ ሐሳቦችን በግል ሕግ ይልቁንም በውል ሕግ አግባብ ማብራራት ተቀባይነትን አግኝቶ የቆየና የተለመደ ነው። ይህ አቀራረብ ግን ግዴታዎች የሕዝብ ሕጎች ካላቸው ሥልጣንም የሚመነጩ መሆኑን ሊያጠራጥር አይገባም። ግብሮች እንዲከፈሉ ግዴታዎችን የሚጥሉ የገቢ ሕጎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሣሌ ናቸው።

ግዴታዎች በባሕሪያቸው ወደ ፍትሐብሄር እንጂ ወደ ወንጀል ክስ የሚያመሩ አይደሉም። ስለዚህ እንደደንቡ የግብር አላፊነት የሚያመራው ወደ ፍትሐብሄር ክስ ነው። ያም ሆኖ የገቢ ሕጎች ብዙውን ጊዜ አልማጭ በሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ በተጨማሪ የወንጀል ክስ ሊቀርብ ስለመቻሉ ይደነግጋሉ።[32] ይህ የሆነበት ምክንያት በግብር ጉዳዮች ያለው የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ከጋት በላስ ነው።

ይሁን እንጂ የፍትሐብሄርና የወንጀል ክሶች ሊቀርቡ የመቻላቸው ሁኔታ መጣመሩ የግብር ኃላፊነትን እንደ አንዱ የግዴታ ዓይነት አድርጎ ለመረዳት የሚያውክ ብዥታ መፍጠር አይኖርበትም። ምክንያቱም ከሁለቱ እያንዳንዱ አማራጭ ራሱን የቻለና የሌላው ጥገኛ ስላልሆነ ነው።[33]

የግብር ኃላፊነት በገንዘብ ጠያቂና በባለዕዳ መካከል በውል ከሚፈጠሩት ሕጋዊ ግንኙነት ጋር እጅግ የሚመሳሰሉ ግንኙነቶች የሚታዩበት ነው።

በቀም ትርጉሙ ግብር ዕዳ ነው ማለት ፍች የለሽ መሆኑ አይካድም፣ ምክንያቱም በአስፈላጊነት ላይ የተመሠረተውን የማስገበር ሥልጣን ሕግ አውጭው በመጠቀም በግድ ያሚሰበሰብ መዋጮ ስለሆነ ነው።[34] እንዲህም በመሆኑ፣ ለምሳሌ የማቻቻል ሥርዓት አይፈጸምበትም።[35] ሆኖም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከግብር ከፋዩ አንጻር ያለው እዳም በውል እንዲሁ ገንዘብ ጠያቂ ከባለዕዳው አንጻር ከሚኖረው እዳም ጋር ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ነው። ሁለቱም ያላቸው ተለይቶ በታወቀ ሰው ወይም ተለይተው በታወቁ ሰዎች ወይም በተወሰነ የሰዎች መደብ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሰበነክ መብት (Right in Personam) ነው። በመሠረቱ እነዚህ ያሉት ግዴታዎች ግዴታ ለተገባለት ሰው የባለግዴታውን ተግባሮች ሁሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል መብት እንዲፈጥሩ የታቀዱ አይደሉም። ባለዕዳው ያለበትን ዕዳ ለመክፈል ከንብረቱ ከፊሉን በመሰዋት ከገባበት የውል ግዴታ ነጻ ለመሆን እንደሚችል ሁሉ ግብር ከፋዩም እንዲሁ የግብር ዕዳውን ለመክፈል ከንብረቱ ከፊሉን በመሰዋት ካለበት የግብር ኃላፊነት ነጻ ሊሆን ይችላል።

ልዩ ድንጋጌዎች እስከሌሉ ድረስ ከውል ያልመነጩ ቢሆንም እንኳ አግባብ ያላቸው የዚህ አንቀጽ ቁጥሮች በግዴታዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በቁጥር 1677 ተገልጿል። ይህ ማለት ሕግ አውጭው እነዚህን ግዴታዎች የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች ከደነገገ እነዚህ ድንጋጌዎች በአንቀጽ 12 ባሉት ቁጥሮች ላይ የበላይነት ይኖራቸዋል። በተቃራኒው ልዩ ድንጋጌዎች በሌሉበት ሁኔታ የዚህ አንቀጽ ቁጥሮች አግባብነት እስካላቸው ጊዜ ድረስ የውል ካልሆኑ ግዴታዎች የሚነሳ አንድ ችግርን ለመፍታት ያገለግላሉ።

የዚህ ቁጥር ቋንቋ የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ ከውል ተዳዮች ድንበር ያለፈ መሆኑን ያለምንም ጥርጥር ያረጋግጣል። አግባብ ያላቸው የአንቀጹን ድንጋጌዎች በፍትሐብሄር ውስጥ ለተመለከቱ ከሥር አመጣጣቸው ከውል ላልሆኑ ግዴታዎች ተፈጻሚ ማድረግ የሚቻል መሆኑ አያጠያይቅም። አስቸጋሪው ጥያቄ ግን የአንቀጹ የአፈጻጸም አድስ የተዘረጋው ምንም ልዩነት ሳይደረግ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን ሁሉ እንዲመለከት ለማድረግ ታቅዶ ነውን? የሚለው ነው።

ሕግ አውጭው "ስለ ውሎች በጠቅላላው" የሚለው አንቀጽ ያለውን የአፈጻጸም አድማስ እንዲሰፋ ያደረገው አግባብ ያላቸው የአንቀጹ ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሄር ውስጥ በሚገኙ እንደ status ውርስ፣ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነት፣ አለአግባብ መበልጸግ ካሉ ሕጎች በሚመነጩ የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ በማቀድ ነው የሚል አመለካከት ሊኖር ይችላል። ይህንንም ለመደገፍ ሕጉን ያረቀቁት ኤክስፐርት በቁጥር 1677 ሥር ያስፈሩትንና ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ማብራሪያ መጥቀስና በማብራሪያው ውስጥ እንደቃሉ አጠቃቀም ሕግ የሚለው ቃል የሚመለከተው ፍትሐብሄር ነው በማለት መከራከር ይቻላል።

> "ግዴታዎች ሕጉ ራሱ እና ግለሰቦች የሚያደርጓቸው ውሎች የሚፈጥሯቸው ናቸው። ይሁንና በነዚህ የተለያዩ ምንጮች መካከል መሠረታዊ የሆነ ተቃርኖ የለም ስል ባለው አመለካከት ውሎች የሚኖራቸው የአስገዳጅነት ኃይል እንኳ አመሠራረታቸውን በሚገዛው እና ተፈጻሚነታቸውን በሚያረጋግጠው ሕግ ላይ የተደገፈ ነው። በተጨማሪ ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጓቸውን ስምምነቶች ብዙውን ጊዜ ሕጉ ያጸናል። የውሉ ይዘት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ከመወሰኑ በላይ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በሚያደርጉበት ጊዜ አስቀድመው ይደርሱበ ብለው ላልገመቷቸው ሆኖም ከዚያ በኋላ ሊነሱ ለሚችሉ በርካታ የተለያዩ ችግሮች መፍትሄዎችን ይደነግጋል። በመጨረሻም ሕግ አውጭው ፍትህን ማስፈንና የህብረተሰብ ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ ስላለበት አንዳንድ አዛኝነት ያላቸውን ድንጋጌዎች እንዲኖሩ አድርጓል"።[36]

ከፍ ብሎ በሰፈረው ጥቅስ አግባብ ሕግ የሚለው ቃል ለፍትሐብሄር ሕግ ምትክ ሆኖ የቀረበ መስሎ ይታያል። ምክንያቱም ቃሉ የተጠቀሰው ከውል ጋር በተገናኘ መልኩ ስለሆነ ነው።[37]

ወደ ሕጉ ሲኬድ በቁጥር 1676 እና በቁጥር 1677 መካከል የሚደረግ ማነጻጸር ለችግሩ መፍትሄ እንደሚያስገኝ ይገመታል። እነሱም በዛም ሁለቱ ድንጋጌዎች ተመሳሳይነት ባለው ቋንቋ የተቀረፁ ሲሆኑ "ስለውሎች በጠቅላላው" የሚለው አንቀጽ ያለው የአፈጻጸም አድማስ ከአንቀጹ መደበኛ ክልል አልፎ የተዘረጋ መሆኑን ይገልጻሉ። ያላቸው መሠረታዊ ልዩነት የመጀመሪያው ውሎችን በሚመለከት የሚናገር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን በሚመለከት የሚናገር መሆኑ ነው።

ቁጥር 1676 የአንቀጽ 12 ድንጋጌዎች የተዋዋይ ወገኖችን ማንነት ወይም የውሉን ዓይነት መሠረት በማድረግ ምንም ልዩነት ሳይፈጠር በሁሉም ውሎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ይገልጻል። ይሁንና ከቁጥር 1777 ድንጋጌ በተለየ አኳኋን ስለአንዳንድ የውል ዓይነቶች የተደነገጉ ደንቦች በሕጉ ውስጥ የት እንደሚገኙ በግልጽ ያመለክታል። እነዚህም የፍትሐብሔር ሕግ 5ኛ መጽሐፍና የንግድ ሕግ በመባል ተጠቅሰዋል።[38] ቁጥር 1677 ይህን አያደርግም በመሆኑም ይህን ባያደርግ የቀረበትን በምክንያት የተደገፈ ማብራሪያ መሻት አግባብ ይሆናል። ሕግ አውጭው ቁጥር 1677ትን ሲደነግግ ሳያጣቅስ የተወው ሆን ብሎ ሳይሆን በመዘንጋት ስለሆነ የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ የተዘረጋው በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ ያሉትን የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ብቻ እንዲሸፍን ታቅዶ ነው ማለት ይቻላል። ይሁንና የነዚህ ድንጋጌዎች ቁጥሮች ተከታታይ መሆን እንዲሁ ዓይነቱን አመለካከት ትርጉም የለሽ ሊያደርገው ይችላል። ሕግ አውጭው በአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ ላይ እንዲሁ ያለውን ገደብ ማበጀት አቅዶ ቢሆን ኖሮ በደንቦች ሲደነግግ እንዳደረገው ሁሉ በቁጥር 1677ትም የውል ያልሆኑ ግዴታዎች የት የት እንደሚገኙ በእርግጥ ማመልከት ባላቃተው ነበር።

ስለዚህ ሳያጣቅስ የተወው ሆን ብሎ ነው። ዓላማውም የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ መላውን የፍት/ብሔር ሕግ እንዲመለከት ማድረግ ነው።

የአንቀጹ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ከፍ/ብሔር ክልል አልፎ የሚሄድ ሲሆን ግዴታዎችን በሚፈጥሩ ሕጎች ውስጥ የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን የመሙላት ሚና እንዲኖራቸው የታቀዱ ናቸው። የግብር ህጎች የፊስካል ግዴታዎች ምንጭ እንደመሆናቸውም በዚህ ረገድ የተለዩ ሆነው አይታዩም።

በታሪክ የኢትዮጵያ የፍ/ብሔር ሕግ አውቶሪቲ በመባል ሲታወሱ የሚኖሩት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቹቹ ናሺጅ ስለ አንቀጽ 12 ባቀረቡት ትችት መግቢያ ላይ ስለዚህ ነጥብ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ገልጸዋል ይህም ቀጥሎ ቃል በቃል እንዳለ ቀርቧል።

"በጀርመን የፍ/ብሄር ሕግ ከማናቸውም ምንጭ የተገኙ ግዴታዎችን የሚገዙ ደንቦች ከውል ሕግ ቀድመው ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊው ሕግ አውጭ ተቃራኒውን ቴክኒክ

ተጠቅሟል። የግዴታዎች ዋነኛ መንስኤ በሆነው በውል ይጀምራል። ይሁንና "ስለውሉች በጠቅላላው" የተጻፈው ሕግ በቁጥር 1677 እንደተመለከተው አግባብነት እስካለው ድረስ ከማናቸውም ምንጭ በተገኙ ግዴታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል"[39]

ደራሲ በቁጥር 1677 ስር ባቀረቡት ትችት በዚህ ነጥብ ላይ ያላቸው አቋም ፍጹም የማያወላውል መሆኑን አሳይተዋል። እዚህ ላይ (ስለ ውሉች በጠቅላላው) በሚለው አንቀጽ የታቀፉት ድንጋጌዎች ከየትም በመነጩ ግዴታዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ብቻ አጠናክረው በመናገር አልተወሰኑም። ከዚሁ ጋር ጉዳዩ በሚመለከተው የግል ወይም የሕዝብ ሕግ ዘርፍ ለሚያጋጥም ፍትሐብሄራዊ ባሕሪ ያለው ማናቸውም ችግር መፍትሄ ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ሁሉ ለመፍትሄው አንቀጽ 12 ውስጥ ወዳሉት ድንጋጌዎች መመለስ የተፈቀደ መሆኑን በአፅንኦት ገልጸዋል። አነጋገራቸው ከፍተኛ የማስተማርና የማሳወቅ ፋይዳ አለው።

> "የግዴታዎች ሕግ ለሁሉም የግል ሕግና የሕዝብ (መንግሥት) ሕግ እንዲ ሳይቀር ለምሣሌ የፊስካል ግዴታዎች ታዕታይ የሕግ ምንጭ ነው። ስለዚህ ስለውሉች በጠቅላላው የሚለው አንቀጽ ውሉችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንን ግዴታዎች የሚመለከቱ የውል ድንጋጌዎች የሚገኙበት በመሆኑ ያለው ቦታ እጅግ ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል። የግዴታዎች ሕግን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን፣ ተገቢውን ተግባራዊ በማድረግ በሌሎችም የግል ሕግ መስኮች አጠራጣሪ ሲሆን ላጋጠመው ችግር መፍትሄ ለማግኘት ተመልሰን የምናየው አግባብነት እስካላቸው ድረስ እነዚህ ድንጋጌዎችን ነው። እንዲሁ ያለው ታዕታይ ወይሆነው ሕግ ተመልሶ በማመሳሰል የትርጉም ዘዴ መጠቀም በፍትሐብሄር የተከለከለ አይደለም። በተቃራኒው በማመሳሰል መተርጎም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 2 በግልጽ ተከልክሏል።"[42]

ከዚህ በላይ አንቀጽ 12 የተዘረጋበትን የአፈጻጸም አድማስ በሚመለከት የተነሳው ጭብጥ ምላሽ እንዳገኘ ይገመታል። ይሁንና በአንቀጽ 1677 ውስጥ (Relevant) "አግባብ ያላቸው" በሚለው አባባል በአጭሩም ቢሆን መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል። በአንቀጽ 12 ውስጥ ካሉት ድንጋጌዎች አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ የውል ባሕሪ ያላቸው እንደሆኑ መገንዘብ ያሻል። እንግዲህ የውል ካልሆኑ ግዴታዎች ጋር ጨርሶ ሊጣመሩ የማ

ይችሉ ድንጋጌዎች የሚኖራቸው አፈጻጸም በውል ሕግ ክልል የተወሰነ ነው። በአንቀጽ 12 ካሉት ድንጋጌዎች መካከል የትኞቹ ሙሉ በሙሉ የውል ባሕሪ ያላቸው እንደሆነ መለየት የሚቻለው አእምሮን በመጠቀም ሊሆን በቁጥር 1677 ድንጋጌ ውስጥ የሰፈረው Relevant (አግባብ ያላቸው) የሚለው ቃል ይህንኑ ነጥብ የሚጠቁም ነው። አሁንም ለአንድ ጊዜ ፕሮፌሰር ቫኖ ኖቪች የውል ላልሆኑ ግዴታዎች አግባብነት ሊኖራቸው ስለሚችሉት ድንጋጌዎች የጻፉትን መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል።

"Relevant (አግባብነት ያላቸው) የሚለው አቀባዩ ገላጭ አነጋገር ያግባብነትን የሎጂክ ደንቦች ወይም በተለሙ አገላለጽ ተራ የውል እውቀትን መሠረት በማድረግ ሲታዩ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን የማይመለከቱ ለምሳሌ በምዕራፍ 1 ስለውል አመሠራረት የሚናገሩትን ድንጋጌዎች ከአፈጻጸም ውጭ የሚያደርግ ነው። በሌላ በኩል በምዕራፍ 2 ስለ ውሎች አፈጻጸምና ውልን ባለመፈጸም ከሰፈሩት ደንቦች አንዳንዶቹ እንዳግባብነታቸው የውል ባልሆኑ ግዴታዎች መፈጸም ወይም አለመፈጸም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። በምዕራፍ 3 እዳዎችን በመሻር፣ በመተካት፣ በማቻቻል፣ በመተላለፍና በይርጋ ስለ ግዴታዎች መቅረት የተደነገጉት ደንቦች የውል ባልሆኑ ግዴታዎች መቅረት ላይ በሚገባ ተፈጻሚ ይሆናሉ።"[41]

ከፍ ብሎ የሠፈረው ጥቅስ በቁጥር 1677 አጠቃቀም ሬሌቫንት (አግባብነት ያላቸው) የሚለውን አቀባቢ ገላጭ ሀረግ መረዳት የሚገባው እንዴት እንደሆነ የሚያብራራ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ትንታኔ መነሻ ላይ በተነሳው ጥያቄ አውንታዊ የሆነ ምላሽ የሰጠ ነው። ጉዳዩን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች እስከ ሌሉ ድረስ የፍትሐብሔሩን የአንቀጽ 12 አግባብነት ያላቸው የይርጋ ድንጋጌዎች በግብር ነክ ክሶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ስሕተት እንዳልሆነም ያረጋግጣል።

ይህ እስከሆነ ድረስ የቁጥር 1845 ድንጋጌን አስመልክቶ በተነሳው ጥብቅ ላይ መተቸት ፋይዳ ያለው መስሎ አይታይም። በእርግጥም ቁጥር 1845 የሚናገረው ስለ ውል መሆኑ ማብራሪያ የሚሻ አይደለም። "ስለ ውሎች በጠቅላላው" በሚለው አንቀጽ ስር ያለው እያንዳንዱ ቁጥር የሚናገረው ስለ ውል በመሆኑ በዚህ ቁጥር ላይ ትችት ሊቀርብ ያስፈለገበትም ምክንያት ይህ ሊሆን አይችልም። ትንታኔው የቀረበው የቁጥር

1845 ድንጋጌን አፈጻጸም በውሎች ላይ ብቻ የመወሰን ዝንባሌ ይኖራል በሚል ፍራቻ ነው።

"ቁጥር 1845 የሚመለከተው ከሥር አመጣጣቸው ከውል የሆኑ መብቶችን ነው። ሆኖም ስለ ይርጋ የሚወሰኑ ደንቦች ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ መሆናቸው አያጠራጥርም። በንብረትና በቤተሰብ ሕግ ዘርፎች የይርጋ አስፈላጊነት ሲጤን እነዚህ ውስጥ ከሚገኙት ነጥቦች ጋር አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላሉ። ይህ እውነታ የቁጥር 1845 ድንጋጌ አፈጻጸም እንዲጠብ የተደረገው በአግባቡ እንደሆነ ያመለክታል።"[42]

ይህ ከላይ የሰፈረው ጥቅስ በቁጥር 1845 ስር የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ልዩ ባሕሪ ያለው ግለትም ከውለ የመነጩ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከት ነው፤ የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ሆኖም በሰውሎች በጠቅላላው የሚለው አንቀጽ ካለው አጠቃላይ መሠረታዊ የሆነ ዓላማ አንጻር ሲታይ፣ ይህ አመለካከት ተቀባይነት እንደማይኖረው በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በቁጥር 1677 የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ የተዘረጋው ሕግ አውጭው በጉዳዮች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ በመፍጠር በቀሪው የግል ሕግ ውስጥ የሚመለከተው ድንጋጌ ያልተገኘለትን ግናቸውንም ችግር ለመፍታት እንዲቻል ባለው እቅድ ነው። ከዚሁ ጋርም በዚህ አንቀጽ ሥር የሚገኝ አንድ ድንጋጌ እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ መሆን ወይም አለመሆን መወሰን ያለበት በሎጂክ የአግባብነት ደንቦች መሠረት ብቻ መሆን እንዳለበት በሚገባ ተገልጿል። ስለዚህ ቁጥር 1745 አግባብነት የለውም በሚል ካልሆነ በቀር በግናቸውም ሌላ ከምንያት ያለውን ተፈጻሚነት በውሎች ላይ ብቻ እንዲሆን አድርጎ ማጥበብ አንቀጹ ካለው መሠረታዊ ዓላማ እንደሚፈንገጥ ሆኖ ይቆጠራል።

ቁጥር 1845 የሰር አመጣጣቸው ከውል ላልሆኑ ጉዳዮች መፈጸም ለሚቀርበው ክስ አግባብነት አለውን? የሚለው ጥያቄ ሲታይ መልሱ አውንታዊ እንደሆነ ወዲያውኑ ግልጽ ይሆናል። ድንጋጌው የተቀረፀበት ቋንቋ ያሻውን ያህል ጠባብ ሆኖ ቢታይም የውል

ባሕሪ ብቻ ያለው ነው የሚያሰኝ እንዳች ነገር የለም። የ10 ዓመት ይርጋውንም ለዩ ድንጋጌ ሳልተደነገገለት የሰር አመጣጡ ውል ላልሆነ ግዴታ መፈጸም በሚቀርቡ የክስ መብቶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ ከቶውኑ ሎጂክን የሚጻረር አይሆንም ምናልባት ይህ የ10 ዓመት ይርጋ ከውል ጋር ጨርሶ ግንኙነት የሌለውን አንድ የይርጋ ጥያቄ ለመፍታት የሚጠቅም መሆኑን ለማሳየት ከአንድ ምሁር ሥራ ምሣሌ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል።

> "የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ለፍርዱ አፈጻጸም መቅረብ ያለበት የመጀመሪያ ማመልከቻ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መሆን እንደሚገባው አይደነግግም። የተሰጠው ፍርድ ለፍርድ ባለመብቱ ጥቅም ይህን ግዴታ የሚፈጥር በመሆኑ ግዴታዎችን ለማስፈጸም ስለሚቀርበው ክስ የተደነገገው የተለመደው የ10 ዓመት ይርጋ ተፈጻሚ ሊሆንበት ይገባል። በመሆኑም ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከ10 ዓመት በኋላ ለአፈጻጸም የሚቀርብ ማመልከቻ በይርጋ መከልከል ይኖርበታል።"[43]

ይህ ከሆነ እንግዲህ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የኤክስፐርት አርቃቂውን አነጋገር በምን መልኩ መረዳት ይገባል? ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ ስለቁጥር 1845 ሲተቹ (ሲያብራሩ) በሌሎች ሀገሮች የሕግ ሥርዓቶች ያሏቸውን የይርጋ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ያላቸውን አርዝማኔ በዚህ ቁጥር ሥር ከተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ ጋር አነጻጽረዋል። ይህንንም ሲያደርጉ ይርጋ ከ10 ዓመት በላይ የሆነ ጊዜ ሊኖረው የማይደገፉ መሆናቸውን አልሸሸጉም። እንዲህ ይላሉ፥

> "የፈረንሳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2262 (መልሶ መውሰድ) የማይቻልበትን ጊዜ ከ30 ዓመት በኋላ እንዲሆን ደንግጓል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ እጅግ ረጅም መሆኑን ሁሉም ይስማማበታል። ከዚህ ሌላ እንደ የስዊዘርላንድ የግዴታዎች ሕግ በቁጥር 1277፣ የጃፓን በቁጥር 167፣ የሊባኖስ በቁጥር 347፣ የኢጣሊያ በቁጥር 2946 እንደሚያደርጉት ሁሉ ቁጥር 1845 የ10 ዓመት ይርጋ ደንግጓል።"[44] ምንም ይህ ቢሆን እንኳ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ኮድ የንብረትና የቤተሰብ ሕግ መስኮች ከዚህ የረዘመ ይርጋ የሚደነግጉ አንድ አንድ ቁጥሮች ይገኛሉ።"[45]

ከዚህ አንጻር ስለ ቁጥር 1845 አፈጻጸም የጸናትን መረዳት የሚገባው ከፍትሐብሔር ሕግ ከ10 ዓመት በላይ የሆነ ይርጋ ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች አኳያ ነው። እነጋገሩ የስር አመጣጣቸው የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን ሁሉ የቁጥሩ ድንጋጌ ዓላማ የተፈጻሚነት ክልል ውጭ እንዳደረጋቸው ሆኖ መወሰድ አይኖርበትም።

ለማጠቃለል በቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ አጠቃላይ ባህሪ ያለው ነው። በመሆኑም ልዩ የይርጋ ድንጋጌዎች እስከሌሉ ድረስ ከየትኛውም ምንጭ የተገኘ ማናቸውንም ግዴታ በሚመለከቱ የክስ መብቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። እንዲህ እንደ መሆኑ ግብር ከፋዮች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 (2) መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማድረግ ጥጋ ያለው የይርጋ መከላከያ ሊያነሱና በሕግ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ያልቀረቡትን ግብር ነክ ክሶች ውጤት አልባ ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

3. <u>ስለአፈጻጸም የቀረቡት ሃሳቦች</u>

ከእንግዲህ የቀረው ተግባር የተለያዩ ሁኔታዎችን በመውሰድ በሰንጠረዥ 'ሐ' ከተመለከቱ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ የተጣለውንም ግብር ለመሰብሰብ በሚቀርቡ ክሶች ጋር የተያያዙ የይርጋ ጥያቄዎች እንዴት መወሰን እንዳለባቸው ለማሳየት መሞከር ይሆናል።[46] ይህ የዚህ ጽሁፍ ክፍል ለዚህ ጉዳይ እንዲውል የታቀደው የገቢ ግብር ሕጎችን ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈጸም ኃላፊነት ላለባቸው እንዲሁም በተግባር የሚገለጹ ጥቅሞች ሊኖረው እንደሚችል ተስፋ በመደረጉ ነው።

1. <u>አንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን ሳያቀርብና በዚሁ ላይ ግብር ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ፣</u>

በሠንጠረዥ 'ሐ' ከተመለከቱ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተከፋይ ለሚሆነው ግብር ያለው ኃላፊነት የሚወሰነው ዓመትን መሠረት በማድረግ ነው። ግብር ከፋዮች ሁሉ በያንዳንዱ የግብር ዘመን መጨረሻ ዓመታዊ የገቢ መግለጫቸውን እንዲያቀርቡና በዚሁ

ላይ የሚፈለገውን ግብር እንዲከፍሉ ግዴታ ተተሎባቸዋል።[47] ታዲያ አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በሚመለከት እነዚህን ግዴታዎች እንዳልፈጸመ ሲገመት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በግብሩ ላይ ያሉትን መብቶች ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የዴርጋ ክርክር ሲቀርብበት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባልን?[48] ከዚህ በታች ለማየት እንደሚሞከረው የዚህ ዓይነቱ ጉዳይ አወሳሰን ውስብስብ ነው።

አሁን በመተቸት ላይ ያለውን ሁኔታ የሚመለከቱ ልዩ የዴርጋ ድንጋጌዎች የሉም። ስለዚህ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ሥር የሚገኘው አጠቃላይ ዴርጋ ፊሱን ቻለ ማለት ነው። በመሆኑም አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው ግብር የመወሰንና የመሰብሰብ መብቶች 10 ዓመት ካለፈ በኋላ ሥራ ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ይሆናሉ ማለት ነው። የቀረበበትን ክስ ውጤት አልባ ለማድረግ ግብር ከፋዩ የዴርጋ መከላከያ ያነሳ ከሆነ አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ማናቸውም በግብር ዴርጋው ሳይቋረጥ ካለፈ በኋላ በተደረገና የግብር ውሣኔ መሠረት ሊሰበሰብ አይቻልም።

የግብር ከፋዩ ማንነት ወይንም የሥራና የመኖሪያ ቦታው በግብር ባለሥልጣኑ መ/ቤት ዘንድ ባልታወቀበትና የዴርጋው ማለፍም ምክንያት ይህ ሆኖ በተገኘበት ሁኔታ ከፍ ብሎ የቀረበው የአፈጻጸም አሳብ አጠያያቂ ይቻል ይሆናል። ሕጉ አሁን ባለበት መልክ የሚነሳውን የዴርጋ መከላከያ የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ባለመኖሩ ምክንያት ውድቅ ለማድረግ ይፈቅዳልን? የሚለውን ጥብቅ መመርመር ያሻል።

የሐብትነት መብት ሥራ ላይ ሳይውል የጊዜ ገደብ በማለፉ ቀሪ የሚሆንበትን ሁኔታ በሚመለከት ስለመብቱ መኖር አለማወቅ የሚነሳውን የዴርጋ መከላከያ በቂ ሕጋዊ ምክንያት አለመሆኑ ተመልክቷል።[49] ስለ ውሎች በጠቅላላው ለሚለው አንቀጽ በ3ኛው ምዕራፍ በስድስተኛው ክፍል ውስጥ ግን ይህን የመሰለ ድንጋጌ አይገኝም፣ ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሰውን የዴርጋ ደንብ በማመሳሰል የአተረጓጎም ዘይቤ ከግዴታዎች ጋር የተያያዙ መብቶችን ለማስቀረት ታቅደው ለተደነገጉ ዴርጋዎችም አግባብነት እንዳለው መመልከት የተከለከለ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1853 ሕግ አውጭው የይርጋ መከላከያን ውድቅ የሚያደርጉ ምክንያቶች እንዴት ያሉት ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ትኩረት ሳይሰጥ እንዳላለፈ የሚያሳይ መሆኑን መረዳት ያሻል። ሕግ አውጭው መከላከያው ስለማያገለግልባቸው ሁኔታዎች ሲደነግግ የመብት መኖር አለማወቅን አልጠቀሰም።[50]

በመጨረሻ የይርጋ መከላከያ ቅን ልቡና በሌላው ተከሳሽ እንዲ ሊነሳ እንደሚችል በቁጥር 1854 የተመለከተ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።[51] እንግዲህ ከፍ ብሎ በተገለጹት ምክንያቶች ምንም እንኳ ይርጋው ሊያልፍ የቻለው መ/ቤቱ የግብር ከፋዩን ማንነት ወይም የሥራና የመኖሪያ አድራሻ ሳያውቅ በመቅረቱ የተነሳ ቢሆን ግብር ከፋዩን የይርጋው ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከልከል ሕጋዊ መሠረት አይኖርም።[52] እንዲህ ያለው ጉዳይ ሊያጋጥም ሌላው መጤን ያለበት ነጥብ የይርጋው መጀመሪያ መቼ ነው የሚለው ጥያቄ ነው። አጠቃላይ በሆነው ደንብ መሠረት ማናቸውም ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው አንድም ግዴታው መፈጸም ካለበት ወይም ግዴታው እንዲፈጸም የመጠየቅ መብት ሥራ ላይ ሊውል ከሚችልበት ቀን አንስቶ ነው።[53] በአንዳንድ ሁኔታዎች ግዴታው መፈጸም ያለበት ቀን የደረሰ ቢሆንም እንዲፈጸም ለመጠየቅ ያለው መብት ገና ወደፊት ያለ ቀን እስከሚደርስ ድረስ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም። ይህ አንድም የፍርድ ወይንም ከዚህ በታች እንደሚታየው የሕግ ውጤት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ባሉ አጋጣሚዎች የይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ግዴታው መፈጸም ካለበት ቀን አንስቶ ሳይሆን መብቱን ሥራ ላይ ለማዋል ከሚቻልበት ቀን አንስቶ ነው። እንግዲህ ይህንን አጠቃላይ ደንብ በመከተል ከይርጋው መቆጠር አጀማመር ጋር ተያይዞ ለተነሳው ጭብጥ መፍትሄ ለማግኘት ይሞከራል።

ማናቸውም ግብር የመክፈል ግዴታ መፈጸም ያለበት በያንዳንዱ የግብር ዘመን መጨረሻ ሲሆን ይህም ዘመን እንደ ኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ነው።[54] ይሁን እንጂ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው ግብር ከፋይ ያለበትን የግብር ዕዳ ወስኖ የመጠየቅ መብት ወዲያውኑ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል አይደለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ግብር ከፋዮች ያለባቸውን ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር

የመክፈል ግዴታዎች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈጸም እንደሚኖርባቸው የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች ስላሉ ነው።

የነዚህ ግዴታዎች አለመከበር የግብሩ አንድ አካል ሆነው ሊሰበሰቡ የሚችሉ መቀጫዎችን ያስከትላል፤ ስለዚህ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ግዴታዎቹ ስለመጣሳቸው ጉዳይ እርግጠኛ ለመሆን በሕግ የተደነገገው ወቅት ማለፍ እስማለፉን መከታተል አለበት። እንግዲህ መ/ቤቱ ያለውን የግብር ከፋዮችን የግብር ዕዳ ወስኖ የመጠየቅ መብት ሊሠራበት የሚችለው ለእነዚህ ግዴታዎች መፈጸሚያ ተብለው በሕግ ከተደነገጉት መጨረሻ አንስቶ ስለሆነ የ10 ዓመት ይርጋው ከዚሁ ቀን አንስቶ መቆጠር ይጀምራል። ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የመቅረብና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች እንደነገሩ ሁኔታ፣ በአራ ወራት፣ በሁለት ወራትና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸሙ ሕጉ ይደነግጋል። ሁሉም ሁኔታ በሕግ የተደነገገው ወቅት መቆጠር የሚጀምረው ግብሩ ከሚመለከተው የግብር ዘመን መጨረሻ አንስቶ ነው።[55]

ለግዴታዎቹ መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች ግብር ከፋዮች ከተመደቡባቸው ደረጃዎች ማለትም ሀ, ለ እና ሐ ጋር የተገናኙ ናቸው።[56] በዚህም የተነሳ እያንዳንዱ ግብር ከፋይ በተመለከተ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ አንስቶ ነው? የሚለው ጥያቄ መወሰን የሚገባው ግብር ከፋዩ የተመደበበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ ነው። ይህን ጉዳይ የ1968 የግብር ዘመንን እንደምሳሌ በመውሰድ በይበልጥ ለማብራራት ይሞከራል።

ከሐምሌ 1/1967 እስከ ሰኔ 30/1968 ያለው ጊዜ የተባለው የግብር ዘመን ነው። ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች መቆጠር የሚጀምሩት ከሐምሌ 1/1968 አንስቶ ነው። ግብር የመክፈል ግዴታው የበሰለው ሰኔ 30/1968 ስለሆነ በደረጃ ሀ, ለ እና ሐ ለተመደቡት ግብር ከፋዮች አግባብ የሆኑት በሕግ የተደነገጉ ወቅቶች የሚያከትሙት እንደቅደም ተከተሉ ጥቅምት 30/1969፣ ነሐሴ 30/1968 እና ሐምሌ 30/1968 ይሆናል። ይኸውም የይርጋን አቆጣጠር ስለሚመለከቱ ደንቦች በሚገልጸው ቁጥር ሥር አግባብ በሆነው ድንጋጌ መሠረት ነው።[57] (የግርጌ ማስታወሻ

ቁጥር 55ትን ይመለከቷል)። የያንዳንዱን በሕግ የተደነገገ ወቅት ማከተሚያ ተከትሎ ወዲያውኑ የሚመጣው ቀን እንግዲህ የ10 ዓመቱ ይርጋ መቆጠር የሚጀምርበት ይሆናል። ይርጋው የሚሞላበት የመጨረሻ ቀንም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1848 በተገለጹት ደንቦች መሠረት ይወሰናል።[58]

2. አንድ ግብር ከፋይ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ውስጥ አንድን የግብር ዘመን የሚመለከተውን ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሙሉ የከፈለበት ሁኔታ፥

አሁን ለማየት በሚሞከረው ሁኔታ የሚነሳው የይርጋ ጭብጥ የሚወሰንበት መንገድ እምብዛም ውስብስብ አይደለም። የገቢው ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 ልዩ ድንጋጌ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ የበላይነት ይኖረዋል። በመሆኑም የዚሁኛውን ቁጥር እዚህ ላይ ማምጣት አስፈላጊ ሆኖ አይገኝም። በአንቀጽ 41 ድንጋጌ መሠረት የግብር ዘመኑን በሚመለከት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው የግብር ከፋዩን የግብር ዕዳ የመወሰን መብት ግብር ከፋዩ የገቢ መግለጫውን ካቀረበበት ቀን ከ5 ዓመት በኋላ ቀሪ ይሆናል። ይህ የ5ዓመት የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ግብር ከፋዩ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የገቢ መግለጫውን ካቀረበበት ከማናቸውም ቀን ሊሆን እንደሚችልና የግድ ለግዴታዎቹ መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች ከሚያከትሙበት ቀን ማግሥት መሆን እንደሌለበት ማስተዋል ያሻል።

የ5 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ መ/ቤቱ የተጠቀሰውን ዘመን ዓመታዊ ገቢ የሚመለከት የግብር ውሣኔ ማድረግ አይችልም። ይህ ብቻ አይደለም። ግብር ከፋዩ ዘመኑን የሚመለከተውን ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሙሉ በሕግ በተደነገገው አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ የከፈለ በመሆኑ መ/ቤቱ የሚሰበስበው ምንም ተጨማሪ ግብር አይኖርም። እንደ እውነቱ ከሆነ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ውስጥ ዓመታዊ ገቢ ሁሉ በተገለጸበትና በዚሁ ላይ የሚፈለገው ግብር በሙሉ በተከፈለበት ሁኔታ መብቱ ላይሠራበት የ5 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ መ/ቤቱ ስለሚኖረው ግብር የመሰብሰብ መብት መናገር ትርጉም የለሽ ይሆናል።

ግብር ከፋዩ በሕግ የሚጣብ መዛግብትና ደጋፊ ሠነዶች የመያዝ ግዴታ ያለበት ሆኖ ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረበት ሁኔታ እንዴት ይታያል?[59] ግብር የመወሰን መብት እንዲሠራበት ተብሎ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ መ/ቤቱ ላይ የተጠቀሰው ግዴታ በመጣሱ የሚጣለው መቀጫ ሊሰበሰብ ይችላልን? ይህ የሚያጋጥመው እጅግ አልፎ አልፎ ቢሆንም ጥያቄ የሚያስነሳም ይሆናል። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ መቻል አለበት የሚል አቋም አለው። በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የተከፈለው ግብር መቀጫው የሚሠላበት መሠረት ይሆናል። መቀጫውን ለማስከፈል ክስ የማቅረብ መብቱ በአጠቃላይ ይርጋ ይገዛል።

3. <u>አንድ ግብር ከፋይ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት አንድን የግብር ዘመን የሚመለከተው ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ፣ ሆኖም በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ፣</u>

በዚህ ሁኔታ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ወይም አለመክፈል የአንቀጽ 41ድን አፈጻጸም የሚነካ ነውን? የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። አወንታዊ የሆነውን ምላሽ የሚደግፍ አቋም ሊኖር እንደሚችል የሚገመት ስለሆነ ያለምንም ማምታታት የጥብቡን መፍትሄ መሻት ግድ ይሆናል። በዚህም ረገድ አወንታዊ የሆነውን ምላሽ የሚደግፉት ክርክሮች በቅድሚያ ቀርበው የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በጉዳዩ ላይ ያለውን አቋም የሚያሳዩት ክርክሮች ይከተላሉ።

ዓመታዊ የገቢ መግለጫ በመቅረብ ብቻ ግብር የመወሰን መብትን የሚመለከተው የ5 ዓመት የጊዜ ገደብ መቆጠር አይኖርበትም፣ የሚለው ሙግት መሠረቱ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 46 ነው። ይህም ዓመታዊ ገቢው ሲገለጽ በዚሁ ላይ የሚፈለገው ግብር ወዲያውኑ መከፈል እንዳለበት ይናገራል። እንግዲህ አንቀጽ 46 በዚህ ረገድ ያሰፈረው ድንጋጌ ግልጽ ስለሆነ አንቀጽ 41 ተፈጻሚ መሆን ያለበት ሁለቱም ዓመታዊ ገቢን የመግለጽና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች ተሟልተው በተገኙበት ሁኔታ ብቻ ነው፣ የሚል ሙግት ሊቀርብ ይችላል። የዚህንም አስተሳሰብ ትክክለኛነት አጉልቶ ለማሳየት አንቀጽ 41 የታቀደው ለግብር ከፋዮች ጥቅም የሚሆን መብት ለመፍጠር እንደመሆኑ ግብር ከፋዮች ግዴታዎቻቸውን ሁሉ ባላሟሉበት ሁኔታ

ሊጠቀሙበት አይችሉም፤ የሚል ተጨማሪ ክርክር ሊሰነዘር ይችላል። ከፍ ብሎ የቀረቡት ክርክሮች አሳማኝ መስለው ይታዩ ይሆናል። ይሁንና በሕግ መነጽር ሲመለከቷቸው የተዛቡ ናቸው።

በመጀመሪያ አንቀጽ 46 በሚገኝበት ክፍልና አንቀጽ 41 በሚገኝበት ክፍል መካከል ያለው የአላማ ልዩነት ከላይ የተገለጸውን አቋም የሚደግፍ አይደለም። አንቀጽ 46 የሚገኝበት ክፍል የታቀደው ግብር የመክፈል ግዴታን አፈጻጸም ለመወሰን ሲሆን ተደራሲውም ግብር ከፋዩ ነው።[60] በተቃራኒው አንቀጽ 41 የሚገኝበት ክፍል የታቀደው የግብር አወሳሰን ሥልጣንን አጠቃቀም ለመቆጣጠር ሲሆን የሚናገረውም ከግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አንፃር ነው።[61] እቅጩን ለመናገር የአንቀጽ 41 ድንጋጌ በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ግብር የመወሰን ሥልጣን ላይ የተደረገ ገደብ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ በአንቀጽ 41 ድንጋጌ ውስጥ ግብር የመክፈል ግዴታው መካተት በሰፊው ተቀባይነት ካላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች ውጭ መሥራት ይሆናል። የአንቀጹ ቋንቋ ግልጽና ምንም ዓይነት የአሻሚነት ምልክቶች የማይታዩበት ነው። ትርጉም በሚሰጥ መልክ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልባቸውም ሁኔታዎች ስላሉ ድንጋጌው ፍቺህ አልባ ነው ሊባል አይቻልም። እንግዲህ አንድ ሰው በአንቀጽ 41 ውስጥ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ እንዲካተት የሚያደርገው የሕግ አውጭውን ተግባር ነጥቆ ወሰዷል የመባል ስጋት እንዳለበት ይሆናል።

የሕግ ድንጋጌዎች እስከተቻለ ድረስ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አድሎአዊ በሆነ አኳኋን መተርጎም አለባቸው፣ የሚል አጠቃላይ ደንብ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የአተረጓጎም ደንብ ግን ቋንቋቸውና ዓላማቸው የጠራና የማያሻማ በሆኑ ድንጋጌዎች ውስጥ በዘፈቀደ ባይተዋር የሆኑ የማቋቋሚያ ሁኔታዎችን በማካተት የሚፈጸመውን ስሕተት አግባብ እንደሆነ አድርጎ ለማሳየት ያገለግላል ብሎ መቀበል አይቻልም። እንዲህ ያለው አድራጎት ከላይ የተጠቀሰውን ደንብ አግባብ ባልሆነ አኳኋን መጠቀም ይሆናል።

በሦስተኛ ደረጃ በመሠረቱ የግብር ድንጋጌዎች በትክክል የታቀደላቸውን የአፈጻጸም ወሰንና የሚኖራቸውን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ አግባብ በሆኑና በሕሊና ርትዕ

ሆኖ በሚታይ ትርጉም ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል። ከአንቀጽ 41 ቋንቋ ለመረዳት እንደሚቻለው የሕግ አውጭው ዓላማ ማናቸውም ሌላ ባይሆን በተገለጸው ገቢ ላይ በሆን ያህል ጊዜ ውስጥ ግብር መወሰን እንዳለበት መደንገግ ነው። ለዚህም ድንጋጌ አንድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀርጦ የተባለው ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበት ቀን ዓመታዊ የገቢ መግለጫው ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቀረበበትን ቀን እንዲሆን አድርጓል። በመሆኑም በድንጋጌው ውስጥ ዓመታዊ መግለጫ የተጠቀሰው በዶርጋ አግባብ ማለትም የጊዜ ገደቡ መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን ለማመልከት ብቻ መሆኑን መረዳት ይገባል።

አንቀጽ 41 የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚቀርበው ዓመታዊ የገቢ መግለጫ አማካይነት ስለግብር ከፋዩ ገቢ መነሻ መረጃዎች ካገኘ በኋላ የግብር ልኩን በመወሰን ረገድ እንዲተጋ የማድረግ ዓላማ ያለው ድንጋጌ ነው። የጊዜ ገደብ ድንጋጌ እንደመሆኑም የአንቀጹ ሚና ጊዜው ሲያከትም[62] የባለሥልጣን መ/ቤቱን ግብር የመወሰን መብት ቀሪ ማድረግ እንጂ የግብር ከፋዮችን ዕዳ (ግዴታ) ማስቀረት አይደለም። የአንቀጽ 41 ዓላማም ለግብር ከፋዮች ጥቅም የሚሆን መፍጠር አይደለም። ይህ ነው ብሎ ማሰብ እንግዲህ የጊዜ ገደብ ያለውን ሚናና ዓላማ በቅጡ አለመገንዘብን ያሳያል።

በአራተኛ ደረጃ በአንቀጽ 41 ድንጋጌና በአዋጅ ቁጥር 77/1968 (እንደተሻሻለው) ውስጥ በሚገኘው አቻው ማለትም አንቀጽ 2 መካከል ንጽጽር ማድረግ ለጊዜ ገደቡ አፈጻጸም ወሳኝ የሆነው ምንድነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ሕግ አውጭው ያለውን የዓላማ አንድነት ያሳያል።[63] አንቀጽ 26 ከእርሻ ሥራ የተገኘ ዓመታዊ ገቢ ሲገለጽ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰን መብት አስመልክቶ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር አንድ ዓይነት የሆነ የጊዜ ገደብ ይደነግጋል። ይህንንም ሲያደርግ ለጊዜ ገደቡ አፈጻጸም በተገለጸው ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ጨርሶ አልጠቀሰም። እንዲያው የሚገልጸው የጊዜ ገደቡ መቆጠር የሚጀምረው ዓመታዊ የገቢ መግለጫው ከቀረበበት ቀን አንስቶ መሆኑን ብቻ ነው። እንግዲህ ከፍ ብሎ ትችት በቀረበበት ድንጋጌ ውስጥ ካለው አቀራረብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይህ አቀራረብ ተቃራኒውን አመለካከት ላይሆን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የያዘውን አቋም የሚደግፍ ሆኖ ይገኛል። እንግሬመንጊሎን የግብር ክፍያ ለጊዜ ገደቡ መቆጠር ቅድመ ሁኔታ ሆኖ በግልጽ የተጠቀሰባቸውን የትራንስክሽን ታክስ አዋጅ ቁጥር 205/1955 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 15 ሐ እና አንቀጽ 21 ሐን ይመለከቷል።[64]

በዚህ ረገድ መባል ያለበት ሁሉ እንደተባለ ይገመታል። ሆኖም በአንቀጽ 46 ዓመታዊ ገቢን የመግለጽና በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች በአንድ ጊዜ ይፈጸሙ በማለት የተደነገገበት ምክንያት ምን ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ማጤን ተገቢ ይሆናል። ይህም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በቀዳሚ ላይ ካለው አቋም የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ሐሳብ እንደሚያረጋጋ ተስፋ ይደረጋል። ቀዳሚ የግዴታዎች አለመከበር ከሚያስከትለው መቀጫ አንጻር መታየት ይኖርበታል። ምንም እንኳን በአንቀጽ 46 የተነገረው ያለ ቢሆንም ሕጉ ከሁለቱ ግዴታዎች እያንዳንዱን መጣስ የሚያስከትለውን እራሱን የቻለ መቀጫ ደንግጓል። በሕግ በተደነገገው ወቅት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አለማክበር በአዋጁ አንቀጽ 66 የተመለከተውን መቀጫ ያስከትላል።[65] በተገለጸው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሕግ በተደነገገው ወቅት የመክፈል ግዴታን መጣስ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 67 የተደነገገውን መቀጫ ያስከትላል[66] ሁለቱ ግዴታዎች በአንድ ጊዜ ይፈጸሙ በማለት ያሰፈረውን ሃሳብ ያሳያል። አለማክበር ግን የሚያስከትለው መቀጫ በሕጉ አልተደነገገም። ግልጽ በሆነ አነጋገር አንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ ግዴታውንና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታውን በአንድ ጊዜ አልፈጸመም በሚል ብቻ የሚጣልበት መቀጫ የለም። በመሆኑም ዓመታዊ ገቢውን በሕግ በተደነገገው ወቅት ውስጥ የገለጸ ሆኖም በተገለጸው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በወቅቱ ያልከፈለ ግብር ከፋይ መቀጫ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት በአንቀጽ 67 መሠረት ብቻ እንጂ በአንቀጽ 66 ጭምር አይደለም።

ይህ ከሆነ እንግዲህ በመተቸት ላይ ያለው የአንቀጽ 46 ኃይለቃል የታቀደው ግብር ከፋዮች ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ግዴታቸውን ለመመላት ወደ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ዘንድ በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ የገለጹትን ገቢ መሠረት በማድረግ ተሰልቶ የሚፈለግባቸውን ግብር ለመክፈል እንዲችሉ በቂ ገንዘብ ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ለማስታወስ ነው። የዚህም ዓላማ የግብር አሰባሰብ ተግባርን ቀናና አመቺ ማድረግ ነው።

የታክስ ድርጋ

ለማጠቃለል አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ በተደነገገው ወቅት ዓመታዊ ገቢውን በገለጸበት ሁኔታ፣ ባለሥልጣኑ አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ ሳይመረምርበት ከቀረ ግብር ከፋዩ የገቢውን መግለጫ ካቀረበበት ከ5ዓመት በኋላ የተባለውን ዘመን በሚመለከት ግብር የመወሰን መብቱ ቀሪ ይሆናል። በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ አለመክፈል የሚያስከትለው በአዋጁ አንቀጽ 67 የተደነገገውን መቀጫ ነው። በማናቸውም መንገድ በአንቀጽ 41 የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ እንዳይሆን የማድረግ ውጤትን የሚያስከትል ሕጋዊ ምክንያት አይሆንም።

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር ለመሰብሰብ ያለው መብት ሊፋታፋይ ነው። በመመርመር ላይ ባለው ሁኔታ፣ ግብር ከፋዩ የግብር ዘመኑን በተመለከተ የከፈለው ምንም ግብር የለም። እንዲሁ እንደመሆኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገው ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት የሚገዛው አጠቃላይ በሆነው የ10 ዓመት ድርጋ ነው። ዘመኑን በሚመለከት መ/ቤቱ ያለው ግብር የመወሰን መብት የ5ዓመት የጊዜ ገደቡ በማለፉ የተነሳ ቀሪ ከሆነ በኋላ እንኳ አጠቃላይ የሆነው የ10 ዓመት ድርጋ እስካላለፈ ድረስ ግብር የመሰብሰብ መብቱ ሊሠራበት እንደሚችል ማብራሪያ የሚሻ አይደም።

4. አንድ ግብርከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ የተደነገገው ወቅት ካለፈ በኋላ ዓመታዊ ገቢውን በሙሉ ገልጾ ሆኖም በገቢው ላይ የሚፈለገውን ግብር ጭራሽ ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ፣

የግብር ከፋዩ እንዲሁ ያለው አድራጎት ቀጥሎ የተገለፁትን ሕጋዊ ውጤቶች ያስከትላል።

1. በመጀመሪያ መሥሪያ ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰንና ክፍያውን የመጠየቅ መብቶች አስመልክቶ መቆጠር የጀመረውን የአሥር ዓመት ይርጋ ያቋርጣል።

2. የመሥሪያ ቤቱን ግብር የመወሰን መብት በተመለከተ የአምስት-ዓመቱ የጊዜ ገደብ መቆጠር እንዲጀምር ያደርጋል።

3. የመሥሪያ ቤቱን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት በተመለከተ ደግሞ የአሥር ዓመቱ ይርጋ መቆጠር እንዲጀምር ያደርጋል።

ግብር ከፋዩ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን ሲያቀርብ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ማመኑ ነው። እንዲህ ያለው በጽሁፍ የተደረገ እምነት የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰንና የመሰብሰብ መብቶችን በሚመለከት አግባብ የሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ካለፈበት ጊዜ አንስቶ መቆጠር የጀመረውን አጠቃላይ ይርጋ እንዲቋረጥ ያደርጋል።

ዓመታዊ ገቢ የሚገለጸው ለዚሁ ጉዳይ የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ እንደመሆኑ ቅጹን መሙላትና መፈረም ግብር የመክፈል ግዴታን በጽሁፍ መቀበልን ያሳያል።[67] በዚህም የተነሳ መግለጫው ከቀረበበት ቀን አስቀድሞ ያለፈው ጊዜ ሁሉ መታሰቡ ቀሪ ሆኖ አዲስ የአሥር ዓመት ይርጋ መቆጠር ይጀምራል።[68] ይርጋ ግን የሚቆጠረው ግብር የመሰብሰብ መብትን በተመለከተ ብቻ ነው። ምክንያቱም የገቢ መግለጫው መቅረብ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 የተመለከተ ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው።

የአምስት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ተፈጻሚነት የሚኖረው አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ አግባብ በሆነው ወቅት በቀረበበት ሁኔታ ብቻ መወሰን አለበት የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። እንዲህ ያለው አቋም ትክክለኛ ያለመሆኑን ለማሳየት ሲባል ቀደም ብሎ የአንቀጽ 41ን ዓላማ በሚመለከት የተገለጸውን እዚህ ላይ መልሶ መድገም ፋይዳ አይኖረውም። ስለዚህ በድንጋጌው ውስጥ የዚህን ሁኔታ አስፈላጊነት በግልጽም ሆነ በውስጠታዋቂነት የሚጠቁም አንዳች አነጋገር አለመኖሩን አጠናክሮ ማስገንዘብ ብቻ በቂ ይሆናል። አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ሕግ በደነገገው ወቅት ውስጥ አለመቅረብ ከወቅቱ ውጭ ደግሞ ከመቅረቡ ጋር ሊቀርብ የሚችል ሲሆን በሁለቱም ሁኔታዎች አድራጎቱ አንቀጽ 41 ያለውን አፈጻጸም የሚነካ አይደለም። እንደመንገዱን ዓመታዊ የገቢ መግለጫ በሕግ በተደነገገው ወቅት ውስጥ የማቅረብ ግዴታን አለመፈጸም የሚያስከትለው ሌላው ሕጋዊ ውጤት ግብር በግምት እንዲወሰን ማድረግ እንደሆነ ይገነዘበዋል።[69]

5. አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ የተደነገገው አግባብ የሆነው ወቅት ካለፈ በኋላ ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ሙሉ ግብር የከፈለበት ሁኔታ

ከፍ ብሎ የቀረቡት የአፈጻጸም ሐሳቦች በመብራራታቸው የተነሣ ይህንን ሁኔታ በሚመለከት የሚደረገውን ትንታኔ ለመረዳት ያን ያህል አያዳግትም። ግብር ከፋዩ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን አቅርቦ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ገቢ ሲከፍል ለግዴታዎቹ መፈጸሚያ በሕግ የተደነገገው አግባብ የሆነው ወቅት በማለፉ ምክንያት የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያለውን ግብሩን የመወሰንና እንዲከፈል የመጠየቅ መብቶች አስመልክቶ መቆጠር የጀመረው የአሥር ዓመት ይርጋ ይቋረጣል። በምትኩ በአዋጅ

በአንቀጽ 41 ያለው የጊዜ ገደብ መቆጠር ይጀምራል። የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ከፍ ብሎ በተራ ቁጥር 2 በቀረበው የአፈጻጸም ሃሳብ የተገለጸውን ነው። ይሁንና ይህ ሁኔታ የመቀጫ ጥያቄ የሚያስነሣ ሲሆን በተራ ቁጥር 2 የተብራራው ሁኔታ ግን የመቀጫ ጥያቄን የማያስነሳ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

6. <u>የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ላንድ ግብር ከፋይ እንዲደርሰው የተደረገበት ሁኔታ</u>

አጠቃላይ በሆነ አነጋገር በሕጉ አግባብ ለአንድ ግብር ከፋይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ወጪ ሆኖ እንዲደርሰው መደረጉ ግብር የመወሰን መብት እንደተጠቀመበት ያመለክታል። በመሆኑም ስለ ይርጋ መናገር የሚቻለው በውሳኔው መሠረት ግብር እንዲከፈል ከመጠየቅ መብት በተያያዘ ነው።

ከይርጋ አኳያ አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዋጋ ያለው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው መደረግ ያለበት:-

ሀ/ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ጨርሶ ያልቀረበ ሲሆን በ10 ዓመት ውስጥ

ለ/ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቀረበ ሲሆን ደግሞ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው።

ይህ ዓይነቱ ዋጋ ያለው የመጀመሪያ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ሲደረግ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት

እስመልክቶ መቆጠር የጀመረው ማንኛውም የጊዜ ገደብ ይቋረጣል። ይህም የሚሆነው ከዚህ በታች የተገለፁትን ሕጋዊ ውጤቶች በማስከተሉ ነው።

አንድ ግብር ከፋይ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ውሣኔ እንደደረሰው ቀጥሎ ከተመለከቱት ነገሮች አንደኛውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲፈጽም ሕጉ ይፈልግበታል።

1. ከግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር ተሳስቦ የሚፈለግበት ግብር ካለ እንዲከፍል /የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 46 ይመለከቷል/

2. የግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኝ በማቅረብ መብቱ እንዲጠቀም /የአዋጅ ቁጥር 173/53 እንደተሻሻለው አንቀጽ 54 ይመለከቷል/

ግብር ከፋዩ ከላይ ከተጠቀሱት አማራጮች አንዱን እንኳ ሣይፈጽም የቀረ እንደሆነ ይርጋው የተቋረጠበት ምክንያት የሚፀናው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያው በአግባቡ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን አንስቶ አንድ ወር ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ወዲያውኑ ተፈፃሚ እንዲሆን ሕጉ ስለሚደነግግ ልክ በፍ/ቤት እንደተሠጠ የፍርድ ውሳኔ ሆኖ ይታያል።[70] ሕጉ በግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ላይ የተገለፀውን የግብር ዕዳ የመጨረሻና ትክክለኛ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥረዋል። እንዲሁም በመሆኑ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጥቅም የሚሆን የማስፈፀም ኃይል ይፈጥራል።[71]

የግብር ውሣኔን ለማስፈፀም የመጀመሪያውን ማመልከቻ የማቅረብ መብት ልክ በፍ/ቤት እንደተሰጠ የፍርድ ውሣኔ በአጠቃላይ የአሥር ዓመት ይርጋ ውስጥ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል። ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ግብር ከፋዩ ከግብር ባለሥልጣን

መ/ቤቱ ጋር ለመተሣሰብ ወይም በአማራጩ ይግባኝ የማቅረብ መብቱን ለመጠቀም የተሰጠው የአንድ ወር ጊዜ የተፈፀመበት ቀን አንስቶ ነው። መ/ቤቱ በተባለው የአሥር ዓመት ይርጋ ውስጥ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያውን ለማስፈፀም ለፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ ካላቀረበ ግብሩ እንዲከፈል የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ይሆናል።

ግብር ከፋዩ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባሳለፈው የግብር ውሣኔ ላይ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኙን አቅርቦ ክርክሩ በመካሄድ ላይ እያለ የመ/ቤቱ ክሶ ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት ሥራ ላይ ሊውል እንደማይችል ግልጽ ነው። የኮሚሽኑ ውሣኔ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሆነ ከፍ ባለ የይግባኝ ደረጃ ሊሰጥ መቻሉ ሣይነካ፣ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ተፈፃሚ ይሆናል።[72] በመሆኑም በግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ውሣኔ መሠረት በአፈፃፀም ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት አሥር ዓመት ከማለፉ አስቀድሞ ለፍ/ቤት በሚቀርብ የአፈፃፀም ማመልከቻ ካልተሠራበት መብቱ ቀሪ ይሆናል።

የኮሚሽኑ ውሳኔ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱን የሚደግፍ ሲሆን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብቱ ታግዶ በሚቆይበት ልክ ይርጋው ይራዘማል። እዚህ ላይ መ/ቤቱ ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ለመደበኛው የይግባኝ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ መብት አለው። ጉዳዩም የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኘው በጠቅላይ ፍ/ቤት ደረጃ ሊሆን ይችላል።[73] ለመ/ቤቱ የተወሰነ እንደሆነ እንዲሁ ያለውን ውሣኔ አፈፃፀም የሚገዛው ይርጋ የማናቸውንም ሌላ ፍርድ የሚገዛው ነው። በመሆኑም በአሥር ዓመቱ አጠቃላይ ይርጋ ውስጥ መ/ቤቱ ውሣኔውን ለማስፈፀም ምንም የአፈፃፀም ማመልከቻ ካላቀረበ ግብር እንዲከፈል መብቱን ያጣል።

7. የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ አሳልፎት የነበረውን የግብር ውሳኔ ለመለወጥና ለማሻሻል ያለው መብት

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 እና 55 ድንጋጌዎች ያፈነገጠ እንደሆነ የሚገመተው የዚሁ ሕግ አንቀጽ 71 ሐ ግብር ከፋዮች በፈፀሙዋቸው የማጭበርበር ተግባሮች የተነሣ አንድን የግብር ዘመን በሚመለከት መክፈል በሚገባው የግብር ልክ ላይ የደረሰውን ጉድለት ለማስተካከል እንዲቻል ታቅዶ የተደነገገ ነው።[74] ግብር ከፋዮች፣

1. የገቢያቸውን ሙሉና ትክክለኛ መግለጫ ያላቀረቡ ወይም ለማቅረብ እምቢተኛ የሆኑ፣

2. የገቢያቸውን ልክ ምንጭና የሥራቸውን እንቅስቃሴ መጠን በሚመለከት መግለጫ ለማቅረብ እምቢተኛ የሆኑ ወይም እነዚሁኑ ጉዳዮች አስመልክቶ ሐሰተኛ የሆኑ መረጃዎች ያቀረቡ፣

3. በወንጀለኛ መቅጫ መሠረት የሚያስቀጣ ማናቸውንም ግብር ነክ ወንጀል የፈፀሙ ሆነው ሲገኙ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀደም ሲል አሳልፎ የነበረውን የግብር ውሳኔ የማሻሻል ወይም የመለወጥ መብት ተሠጥቶታል። እንግሊ መንገዱን አንቀጽ 70 ሐ 1 የአንቀጽ 41 ድንጋጌ የመጨረሻው ሐይለ ቃል ያስከተለው ውጤት ሆኖ እንደሚገመት ያስገነዝቧል። የተጠቀሰው ሐይለ ቃል የአምስት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ማለፍ ግብር ከፋዮችን በገቢ መግለጫቸው ባልገለፁት ገቢ ላይ ለሚፈለገው ግብር ከመጠየቅ እንደማያድናቸው ይገልፃል።[75]

እንቀጽ "70 -ሐ-" ከዶርጋ አንፃር ሲታይ በድንጋጌው ውስጥ ያሉት ቁልፍ የሆኑ ቃላት "በማናቸውም ጊዜ" የሚሉት እንደሆኑ መረዳት አያስቸግርም እነዚህ ቃላት የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት የማጭበርበር አድራጎቶች መፈፀማቸውን ከማወቁ ጋር ተጎዳኝተው ሲታዩ ምን ዓይነት አስተሳሰብ ያሳድራሉ። ወሳኙ ጥያቄ ይህ ሲሆን ጥያቄውን በሁለት መንገዶች ማየት ይቻላል።

በመጀመሪያ "በማናቸውም ጊዜ" የሚሉትን ቃላት ጥሬ በሆነው ጊዜ አገባብ መመልከት ይቻላል። በዚህ አመለካከት መሠረት የአለፉት ዓመታት ብዛት የቱን ያህል ቢሆንም መ/ቤቱ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ አንድ ግብር ከፋይ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የማጭበርበር አድራጎቶች ማናቸውንም መፈፀሙን በደረሰበት ጊዜ ሁሉ የግብር ዘመኑን የሚመለከተውን የቀድሞ የግብር ውሳኔ አሻሽሎ ወይም ለውጦ ግብሩን እንደአዲስ መወሰን ይችላል። ይህ አስተሳሰብ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለውን አማልሎ የነበረውን የግብር ውሣኔ የማሻሻል ወይም የመለወጥ መብት ከዶርጋ ደንቦች አፈፃፀም ከሞላ ጎደል ውጪ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሳል።

እርግጥ በዚህ ሁኔታ መ/ቤቱ የማጭበርበር አድራጎት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ባለው የ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በተባለው መብት ሳይመራበት በመቅረቱ መብቱ ቀሪ ሊሆን በሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ይገመት ይሆናል። ይህ ግምት ግን እጅግ በጣም የራቀ ነው። ምክንያቱም መ/ቤቱ ይህን ያወቀበትን ትክክለኛ ቀን አስረድቶ በዶርጋ መከላከያ ለመጠቀም ግብር ከፋዩ መቻሉ የማይመስል ነገር ስለሆነ ነው።

በሁለተኛው መንገድ "ማናቸውም ጊዜ" የሚሉትን ቃላት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 በተመለከተው አጠቃላይ የዶርጋ ድንጋጌ አገባብ ማየት ይቻላል። በዚህ አመለካከት ላይ በመመሥረት የሚከተለው ሃሳብ ቀርቧል።

የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አንድን የግብር ዘመን የግብር ውሣኔ በሚመለከት የተፈጸመውን የማጭበርበር አድራጎት ተከታትሎ ሊደርስበት (ሊያውቀው) የሚገባውና የግብር እዳውን እንደገና የመወሰን መብቱን ሊሠራበት የሚችለው በ10 ዓመት ውስጥ ሲሆን ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው፡

1. አንቀጽ 41 ድንጋጌ መሠረት ግብር ከፋዩ በገለጸው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር ትክክለኛ እንደሆነ ከሚቆጠርበት ቀን አንስቶ፣[76]

2. ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው የተደረገው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በአንቀጽ 55 መሠረት የመጨረሻና ትክክለኛው ሆኖ ከሚቆጠርበት ቀን አንስቶ ይሆናል፣[77]

ከፍ ብሎ ከቀረቡት ሁለት አስተሳሰቦች የኋለኛው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል። ይህም የሚባልበት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

1. አጠቃላይ በሆነ አነጋገር ቀደም ሲል የደረጃ ደንቦች ለምን መደንገግ እንዳስፈለጋቸው ሲወሳ የተገለጹት የቲዎሪና ሕግ ነክ ምክንያቶች ሁሉ ሁለተኛውን አስተሳሰብ የሚደግፉ ናቸው።

2. ይልቁንም የቀድሞውን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ሽር ግብሩን እንደአዲስ የመወሰን መብት በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱና በግብር ከፋዩ መካከል የቆየ ግንኙነት እንዳለ ግምት የሚያሳድር ስለሆነም የተሰጠው መብት ለሁል ጊዜ ፋይሉን እንደያዘ እንዲቆይ መፍቀድ ምክንያት የለሽ ይሆናል።

3. ሁለተኛው አማራጭ በአንድ የሂሣብ ዓመት በንግድ ከፋዩ ላይ የሚጫለውን የንግድ ዕዳ በቁጥር ተወስኖ የሚታወቅበትን ቀን ለመለየት የሚያስችል ትክክለኛና ትርጉም የሚኖረው የስሌት መንገድ የሚሰጥ ነው።

4. የቀዳሚ የንግድ ውሣኔ ማስታወቂያን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ንግዱን እንዳይኤሊስ የመወሰን መብት በገቢ ላይ ወንጀል ሬጻሚ የሆኑ ግብር ከፋዮችን እድና የመያዝ ግዴታን ስለሚያካትት ሁለተኛው አስተሳሰብ መ/ቤቱ ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት በትጋት እንዲተር ከግድሬታ ጋር በተሻለ የተቀናጀ ሆኖ ይገኛል። መ/ቤቱ በሥሩ ያለውን የኢንስፔክሽን ኃይል በብቃት እንዲያሰማራና ለተባለው ዓላማም አግባብ ካለው የመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች በተለጠፈ አኳኋን ዕርዳታና የሥራ ትብብር እንዲጠይቅ ተጽእኖ ያደርጋል።

የግብር ሕጎች የዴርጋ ትላይን በቂ በሆነ መንገድ የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዙ እንዲሆኑ ማድረግ ግድ ነው። ይህን በሚመለከት መደረግ ስለሚገባቸው ነገሮች ኃሳቦች ማቅረብ ያን ያህል ከባድ ላይሆን ይችላል። ላሩ ግን በልምድ እንደታየው እንዲህ ያሉ የግብር ማሻሻያ ሃሣቦች ፈጥነው በተግባር ለመተርጎም አልታደሉም። ሆኖም እስከዚያው ድረስ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንደተነሱት ላሉ የሕግ ችግሮች አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እየታገዙ መፍትሄ መስጠት ግድ ይሆናል። ተደም ሲል በተገለጸው አኳኋን በፍትሐብሔር ሕግ መገልገል በሕግ ያልተከለከለ በመሆኑ በዚህ ሕግ ባግባቡና ባያወላውሉ መገልገልን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያበረታታል።

ከፍ ብሎ ስለ ዴርጋ አፈጻጸም የቀረቡት ሃሣቦች በግብር ከሶች ላይ አሁን ካለው አመለካከት የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፍ/ቤቶች ግብር ነክ የዴርጋ

ጭብጦችን በመወሰን ረገድ ሊከተሉት ከቆዩት ሥር ነቀል በሆነ መንገድ ሊለዩ ይችላሉ። ይሁንና በግብር መስክ ይርጋን የሚገዙ ዝርዝር ደንቦች በሌሉበት ሁኔታ የተረሱት ሃሳቦች ከማናቸውም ይልቅ በተግባር ሊገለጡ የሚችሉ እንደሆነ ይገመታል። በዚህም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እርካታ ያገኛል።

ማስታወሻዎችና ማጣቀሻዎች

1. የላቲኑ አገላለጾች እንደተራ ቀደማቸው "በይርጋ ቀሪ የማይሆኑና" እና "በይርጋ ቀሪ የሚሆኑ" ተብለው ይተረጎማሉ።

2. Rudof Shom, The Institute of Roman Law (Oxford: Clarendon Press, 1901), ከገጽ 298-300.

3. ዝኒ ከማሁ

4. International Encyclopaedia of Comparative Law "Period of limitation" (Dordrechf, Boston, Lancaster: Tuebirgen and Martinus Nijahoff Publishers, 1986, Vo. XI, part II, Chapter 13, ገጽ 23.

5. በኮመን ሎው ሥርዓት ላቸስ በመባል የሚታወቀው መከላከያ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱን ሳይጠቀምበት መዘግየቱን ምክንያት በማድረግ የተጀመረ ክስ እንዳይቀጥል ተከሳሽ ሊያነሳው የሚችል መከላከያ ነው። የዘገየበት ጊዜ ከተከሳሽ ቸልተኝነት ወይም የትጋት ጉድለት መንጭቶ የተከሳሽን ጥቅም ይነካል፣ የሚያሰኝ መሆን ወይም ከሳሽ የመክሰስ መብቱን ፈቅዶ ትቷል ሊያሰኝ በሚችል መጠን የረዘመ መሆን ይኖርበታል። እዚህ ላይ "ይርጋ" ና "ላቸስ" አንድ አለመሆናቸው ያስተውሏል። የመጀመሪያው ክስ ለማቅረቢያ በህግ የተደነገገውን ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን የኋለኛው በህግ ድንጋጌዎች ላይ ሳይመሠረት ክስን በማቅረብ ረገድ በሀሊና ግምት ከተገቢው በላይ መዘግየትን የሚያመለክት ነው።

6. <u>International Encyclopoedia of Comparative Law,</u> ገጽ 23

7. በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. 1165(2)፣ 1192፣ 1000፣ 1810፣ 1024፣ 2143 የወንጀለኛ መቅጫ ቁ. 226-231.

8. Philip S. James, <u>Introduction to English Law</u> (London: English Language Books Society and Butter Worth, 10th Edition, 1984 p. 301.

9. Rene David, <u>Commertany on Contracts in Ethiopia</u>, Translated by Michael Kindred (Addis Ababa, Haile Selassie I University, Faculty of Law. 1973), ገጽ 89.

10. Marcel Planiol. <u>Treatise on the Civil Law</u>, Transated by Louisiana State law Institute (Paris: Loulsiara State law Institute, 1959, ከገጽ 345-356.

11. Corpus Juris Secundum, Taxation (St. Pau, Minne Sota, West Publishing Co., 1954), Vol. 84, p. 1429.

12. ዝኒ ከማሁ ገጽ 1430.

13. እዚህ ሁኔታዎች ከግብር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ያስተውሏል። እንደጠፉ ወይም ባለቤት አልባ እንደሆኑ የተቀመጡ ንብረቶችን በሚመለከት የባለሃብትነት መብቶችን ከማስተላለፍ ጋር የተያያዙ ናቸው።

14. Planiol, ከገጽ 378-380.

15. Corpus Juris Secundum, ገጽ 46.

16. የግብር ዕዳ መግረን በተመለከተ ምሳሌ ይሆን ዘንድ አዋጅ ቁጥር 173/1958 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 72/35 የአዋጅ ቁጥር 77/1968 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 45ን ይመለከቷል።

17. World Tax Series, <u>Taxation in Brazil</u> (Boston, Toronto; Little, Brown and Company Limited, 1957, ገጽ 262.

18. ዝኒ ከማሁ

19. ዝኒ ከማሁ ከገጽ 262-263.

20. <u>World Tax Series, Taxation in Italy</u> (Chicago: Common Clearing Houses Inc., 1964), ከገጽ 248-249.

21. Word Tax Series, <u>Taxation in Sweden</u> (Canda: Little Brown and Company Limited, 1959), ገጽ 592.

22. World Tax Series,, <u>Taxation in the Federal Repubic of Germany</u> (Chicago; Commerce Clearing House Limited, 1963), ከገጽ 686-688.

23. ዝኒ ከማሁ

24. አዋጅ ቁ. 145/1947, አንቀጽ 106 ማናቸውም ቀረጥ በሙሉ ሳይሆን በጎደል በተቀረጠ ወይም በስህተት በተመለሰ ጊዜ ቀረጡን በሙሉ ሳይከፍል የቀረ ወይም ቀረጡ በስህተት የተመለሰለት ሰው ቀረጡ ጎድሎ ከቀረበበት ወይም ከተመለሰለት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ዲሬክተሩ በጠየቀው ጊዜ የጎደለውን ቀረጥ ወይም በስህተት የተመለሰለትን ቀረጥ ይከፍላል።

25. አዋጅ ቁ. 173/1953 አንቀጽ 4/ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውን ማስታወቂያ ለአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን አቅርቦ የተባለው የገቢ ማስታወቂያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) ዓመት ጊዜ ውስጥ ከተገለጸው ተከፋይ ግብር የተለየ የግብር ውሳኔና መደብ ማስታወቂያ ግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ካልተደረገ በስተቀር ግብር እንዲከፈልበት የተገለጸው ገቢ በቂ ሆኖ ግብሩ የተወሰነውና የተመደበው በዚሁ ገቢ ላይ ብቻ ሆኖ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ በዚሁ በአንቀጽ 41 ውስጥ የተሰጠ ውሳኔ በተባለው የገቢ ማስታወቂያ ውስጥ ካልተገለጹት ገቢዎች ግብር ከፋዩን የገቢ ግብር ከመክፈል ነፃ አያደርገውም

በዋናው አዋጅ አንቀጽ 41 የተመለከተው የሦስት ዓመት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 65/1968 ወደ አምስት ዓመት መሻሻሉን ይገነዘቧል።

26. የፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 1845-1856

27. <u>የፍትሐብሄር ሕግ ቁ 1677። የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም</u>

   1. ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀጽ ደንቦች ይፈጸሙባቸዋል።
   2. የአንዳንድ ግዴታዎችን ከበር እመጣጣቸውን ወይም አይነታቸውን በመመልከት ከዚህ ደንብ የተለዩት ደንጋጌዎች የተጠበቁ ናቸው።

28. <u>የፍታብሄር ሕግ ቁ 1875። የድርጋ ጊዜ</u>

    ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሣ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በዐሥር ዓመት ድርጋ ይቀራል።

29. Rober Warden Lee, <u>The Elements of Roman Law</u> (London: Sweet and Maxwell, 1956), ገጽ 256.

30. ዝኒ ከማሁ።

31. Amos and Walton, <u>Introduction to French Law</u> (Oxford: Calredon Press, 1969), ገጽ 140.

32. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 70 (ሀ) በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ውሳኔዎች የሚተላለፍ ወይም የሚጥስ ግብር ከፋይ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

33. <u>የፍትሐብሔር ሕግ ቁ 2139። የወንጀል ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ስላለው ሥልጣን።</u>

በፍትሐብሔር በኩል ጥፋት ተደርጓል ብሎ ለመወሰን በወንጀል ፍርድ ተከሳሹ ነፃ መለቀቁ ወይም በወንጀል አያስከስሰውም ተብሎ መበየኑ ዳኞችን አያግዳቸውም፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 232። <u>በፍትሐ ብሔር በኩል የይርጋ ዘመን መጽናት የሚያስከትለው ውጤት</u>

ስለ ጉዳት ማቻቻያ ካሳ አከፋፈል በፍትሐ ብሔር በኩል እንዲሁና የሚቀርበውን የይርጋ ዘመን ጊዜ ውሳኔ የሚመለከተው ነገር ከወንጀል ክስ ጋራ ቢቀርብም ባይቀርብም ይጸናል የሚያስኘበት ስርዓትና የጊዜው ውሳኔም ሆነ የይርጋው መፅናት በሚያስከትለው ውጤት በኩል ያለው የጉዳዩ አፈፃፀም የሚመራው በፍትሐብሔር ህግ ደንበኛ ድንጋጌዎች ውስጥ ነው።

በፍትሐ ብሔር በኩል ያለው ክስ በይርጋ ቀሪ ባይሆን የወንጀሉ ክስ ማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እንደሆነ ይህ የፍትሐብሔር ጉዳይ በወንጀል ፍርድ ቤት ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችል በመሆኑ የክፍሉ ባለሥልጣን በሆነው በፍትሐብሔር ፍርድ ቤቶች ችሎት ፊት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል።

34. <u>Corpus Juris Secundum,</u> ገጽ 32.

35. በዚህ ረገድ የሚከተሉትን ሁለት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ያነጻጽሩአል። <u>1833። መቻቻያን የሚያስቀርጉ ሁኔታዎች።</u>

ቀጥሎ ከተዘረዘረው በቀር የዕዳው ምክንያት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን ማቻቻያ ይደረጋል።

(ለ) ለመንግሥትና ለመሥሪያ ቤቶች የሚከፈል ገንዘብ ሲሆን፣ ቁ <u>3178 ስለ ማቻቻል</u>

ተቀባይ ዕዳ ይቻቻልልኝ ብሎ ያስተላልፍን መሥሪያ ቤት ለመጠየቅ የሚችለው ያቻቻልልኝ የሚለው ዕዳ የቀረጥ ዕዳን የሚመለከት ያልሆነ እንደሆነ ነው።

በአማርኛው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥ 1833 (ለ) እና ቁ 3178 መካከል በእንግሊዝኛው ቅጂ እንደሚታየው ያለ መቃረን አለመኖሩን ይገነዘቡአል። ሁለቱም ዕዳን የግብር ዕዳን ለማቻቻል መታወቂያ ማቅረብ አለመፈቀዱን ይገልጻሉ።

36. David, ገጽ 7.

37. George Krzeczunowicz, <u>Formation and Effects of Contracts in Ethiopian Law</u> (Addis Ababa: Faculty of Law, Addis Ababa University, 1983), p.v. (preface).

38. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1676 ውሎች የሚመሩባቸው ደንቦች</u>

1. ውሎች በይነታቸው ምክንያታቸውም ማንኛውም ቢሆን በዚህ አንቀጽ በተጻፉት ጠቅላላ ደንቦች ይመራሉ።

2. እነዚሁን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ልዩ የሆኑ ደንቦች በዚህ ሕግ በ5ኛው መጽሐፍና በንግድ ሕግ ውስጥ ተመልክተዋል።

39. Krzeczunowicz, ገጽ 1.

40. ዝኒ ከማሁ

41. ዝኒ ከማሁ

42. David, ገጽ 89.

43. Robert Allen Sedler, <u>Ethiopian Civil Procedure</u> (Addis Ababa: Faculty of Law, HSIU in Association with Oxford University Press, 1968). p. 271.

44. David, ገጽ 89

45. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1288። መሠረት።</u>

1. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ (ባለይዞታ) የሆነ ሰው የዚሁ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት በሰላም ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል።

ይህ ድንጋጌ የግል ባለርስትነት ቀሪ ባደረገው ሕግ ከ1967 ወዲህ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ሆኖአዋል።

<u>ቁ 1000 (2) ጥያቄውን ለማቅረብ የተወሰነ ጊዜ።</u>

1. ከሳሽ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለ ወራሽነት ጥያቄ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም።

2. እንደዚሁም ሟቹ ባለንብረት ወይም ከሳሹ በመብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንሥቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም።

46. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው)። አንቀጽ 4 (ለ) በገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር፣ አዋጅ ቁጥር 77/1968 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ከንግድ፣ የፕሮፌሽን (ሙያ) ከማልቃ ገብ ሥራ (ቮኬሽን) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ እና ረ ከተመለከቱት ውጭ ከማናቸውም ሌላ የሥራ እንቅስቃሴ በሚገኝ ገቢ ላይ ከዚህ በታች ከአንቀጽ 12 እስከ 17 ቁጥር (ሠንጠረዥ ሐ) በተመለከተው መሠረት።

47. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው)

<u>5ኛ/ ሠንጠረዥ "ሐ"</u>

አንቀጽ 12 (ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 በንዑስ አንቀጽ (ለ) ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች ላይ ግብር እየተወሰነና እየተመደበ በየዓመቱ ይከፈላል፥ ይሁን እንጂ የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የተለየ የሒሣብ ዓመት እንዲሆን ካልፈቀደ በስተቀር ግብሩ የሚከፈለው ከኢትዮጵያ መንግሥት የበጀት ዓመት ጋር ተመሳሳይ ከሆነው ከኃላፊው የሒሣብ ዓመት ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ነው።

48. የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ስለ ግብር ከፋዮች የሥራ እንቅስቃሴና ገቢ መረጃዎች የማግኘት መብቱን በሚገባ የሚጠቀምበት ቢሆን (አዋጅ ቁ 173/1953 እንደተሻሻለው አንቀጽ 23-27). እንዲሁም ንግድን ወይም መድበልን ለማካሄድ የንግድ ፍቃድ ማውጣት አስፈላጊ በለመሆኑ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሚገባ ሥራ ላይ የሚውሉ ቢሆን (የአዋጅ ቁ 294/1963 አንቀጽ 3(1) በአዋጅ ቁ 76/1968 አንቀጽ 11 እንደተሻሻለው) ይህ ሁኔታ የሚያጋጥመው እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው።

49. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1196። ሀብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን።</u>

ግዙፍነት ያለው ያንድ የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ ወይም ሀብቱ መሆኑን ባለማወቅ ዐሥር ዓመት ያልተገለገለበት እንደሆነ መብቱን ያጣ ሆኖ ይቀራል።

50. <u>የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁ ፲853። የመታዘዝ ወይም የቤተዘመድ ግንኙነት</u>

1. ፍርድ ቤቱ ይርጋን አልቀበልም ለማለት የሚችለው ባለገንዘቡ የሚፈልገውን ያልጠየቀበት ምክንያት ባለዕዳውን የመፍራትና የማክበር ስሜት ኑሮት ለእሱም የተቀራረበ ዝምድና ወይም ታዛዥነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው።

2. እንዲህ ሲሆንም ዕዳውን ለመክፈል ዋስ የሆኑት ሰዎች ከግዴታቸው ነፃ ይሆናሉ።

51. <u>የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁ ፲854። ክፉ ልቦና።</u> ይርጋ እንዳይቆጠርበት ክፉ ልቡናን መቃወሚያ አድርጎ ለመከራከር አይቻልም።

52. አንዳንድ ሰዎች በቀረበው ክርክር አቶሬ ግብር ከፋዮች ሊጠቀሙ ይችላሉ በሚል ሐሳብ ቅሬታ ይገባቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ ትንታኔውን በሕጉ ዓይን ቢመዝኑት የተሻለ ይሆናል። እንደውነቱ ከሆነ ይበልጥ ከባድ እንደሆኑ የሚቆጠሩት የወንጀል ክሶች እንኳን፣ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ። እንግዲ መንገዱን ከባድ ለሆነው የግብር ወንጀል የተደነገገው መደበኛ የይርጋ ዘመን 5 ዓመት ነው። (የወንጀለኛ መቅጫ ቁ 226 (ሠ) ን ከ 355 (1), 360 (1) እና 361 (1) እንዲሁም ከአዋጅ ቁ 214/1973 አንቀጽ 15 ጋር አጣምሮ ይመለከቷል።) በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 231 በተመለከቱት ደንቦች መሠረት ከባድ ለሆነ የግብር ወንጀል የተደነገገው ፍጹም የሆነ የይርጋ ዘመን አስር ዓመት ነው። ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ወንጀል ፈጻሚው የመጀመሪያ የወንጀል ድርጊቱን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ነው። (የወንጀለኛው መቅጫ ሕግ ቁ 228 (2) ይመለከተዋል።)

53. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ ፩866። የይርጋው መነሻ ጊዜ።</u>

የይርጋ ቀን መቁጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሠራበት ቀን ጀምሮ ነው።

54. አዋጅ ቁ 162/1951 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 2 የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ድረስ ላለው የአንድ ዓመት ጊዜ ይሆናል።

አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 35 (ሐ) በዚሁ አዋጅ በሠንጠረዥ "ሐ" በተመለከተው መሠረት ግብር ከሚከፈልበት የገቢ ምንጭ ስለሚገኝ ገቢ በየዓመቱ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ማስታወቂያ ይቀርባል።

1. የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው ደንብ መሠረት ግብር ከፋይ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ እንዲኖር የተወሰነ እንደሆነና በየዓመቱ መጨረሻ ለአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን ከአስፈላጊው ዝርዝር መግለጫ ጋር ባላንስ ሺትና የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ የሚያቀርብ ሲሆን፥ ግብሩን ከሚከፈልበት የሂሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ አራት 4/ ወር ድረስ፥

2. የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው ደንብ መሠረት ከፋዩ ለአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የየቀኑን ጠቅላላ ገቢና ወጪውን ተከፋፍሎ ወይም ሳይከፋፈል ወይም ደረጃ በደረጃ/በግሩፕ ለማቅረብ በሚቻልበት አኳኋን ብቻ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ እንዲኖር የተወሰነ እንደሆነ ግብሩ የሚከፈልበት የሂሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ(፫) ወር ድረስ፥

3. ግብር ከፋዩ የሒሳብ መዝገብ ወይም መግለጫ እንዲኖረው ካልተወሰነ ግብሩ ከሚከፈልበት የሒሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ ሠላሳ(ን) ቀን ድረስ፡

56. የግብር ከፋዮች አመዘጋገብና የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሠነዶች የመያዝን ግዴታ በተመለከተ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ 258/1955, ከአንቀጽ 25-95 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመለከቷል።

57. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1808። በወሮች የተወሰነ ጊዜ።</u>

1. ጊዜውን በወር ወይም በብዙ ወሮች የተወሰነ እንደሆነ ዕዳውን ለመክፈል የሚገባው ውሉ በተደረገበት ቀን በመጨረሻው ወር መጨረሻ ቀን ነው። 3 ጳጉሜ እንደ አሥራ ሦስተኛ ወር አይቆጠርም።

58. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1838። የጊዜው አቆጣጠር።</u>

1. የይርጋ መጀመሪያ ቀን ከይርጋው ዘመን ሂሳብ ውስጥ ገብቶ አይታሰብም።
2. የይርጋው ቀን የሚያልቀው ለይርጋው የተወሰነ መጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ነው።
3. ምናልባት ይህ ቀን ገንዘቡ በሚከፈልበት ቦታ በሕግ የታወቀ የበዓል ቀን የሆነ እንደሆነ ይርጋው የሚያልቀው ከበዓሉ ተከታይ በሆነው በዓል ባልሆነው ቀን ነው።

59. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 68 ከዚህ በታች ከተመለከቱት መደቦች በአንደኛው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ግብር ከፋይ የገንዘብ

ሚኒስትሮችን እንዲሠራባቸው በደንብ የሚያወጣቸውን ሂሳቦች መዝገቦች የማይዝ ግብር ከፋይ በሚከፍለው ግብር ላይ በመቶ ሃያ (20) መቶኛ ይከፍላል።

60. አዋጅ ቁ. 173/1953 (እንደተሻሻለው) 11ኛ <u>የግብር አከፋፈል</u> ከአንቀጽ 44-46 ጥምር።

61. አዋጅ ቁ. 173/1953 (እንደተሻሻለው) 10ኛ <u>የግብር አወሳሰን</u> ከአንቀጽ 38-43. ጥምር

62. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ.2ሺ974። የማይገባውን ስለ መክፈል።</u>

1. ሊከፈል የማይገባውን ነገር የከፈለ ሰው እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው።
2. የሚከፈለው ነገር የተቀበለው እምነትን የሚያጓድል ሁኔታ እንደሆነ የማይገባውን ነገር የከፈለው ሰው ከከፈለበት ቀን አንስቶ ይህ የከፈለው ነገር የሰጠውን ፍሬ ወይም ሕጋዊውን ወለድ ጥምር እንዲመለስለት ለመጠየቅ ይችላል።

63. አዋጅ ቁ 77/1967 (እንደተሻሻለው), አንቀጽ 26.

64. አዋጅ ቁ 205/1955 (እንደተሻሻለው), አንቀጽ 15 (ሐ)፥ ባለፋብሪካስ የየወሩን መግለጫ (ዲክላሬሲዮን) አቅርቦና ቀረጡንም በተወሰነው ጊዜ ከከፈለ በኋላ መግለጫ (ዲክላሬሲዮን) ለቀረው ባለሥልጣን ከቀረበበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት (5) ዓመት ድረስ የተለየ የሂሳብ መጠየቂያ ውሳኔ ካልቀረበለት

በመግጫው (በዲክላሬሲዮን) 15 (ሐ) የተደነገገው በመግለጫው (በዲክላሬሲዮኑ) ላይ ላልተመለከተው ገቢ ቀረጥ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም።

65. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 66 ከዚህ በታች በ35ኛው አንቀጽ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የሥራውን ገቢ ያላስታወቀ ማናቸውም ግብር ከፋይ በመጨረሻ ያገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን በሚወሰነው ግብር ላይ በተጨማሪ በመቶ ሃያ (20) መቀጫ ይከፍላል።

66. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 67^E ግብሩ ከሚከፈልበት ቀን ጀምሮ እስከ ሠላሳ (30) ቀን ድረስ ግብሩን በሙሉ ሳይከፍል የቀረ ማናቸውም ግብር ከፋይ፣ ለየሰላሳው (30) ቀን ከግብሩ በላይ በመቶ ሁለት (2) መቀጫ እየተጨመረበት ይከፍላል። ጠቅላላው የመቀጫው ድምር በመቶ ሃምሳ (50) አያልፍም።

67. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው አንቀጽ 37 የገቢው ማስታወቂያ የሚሰጠው፣ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን የሚያስችል የገቢና የወጪ ዝርዝር ያለበት ያገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን በሚሰጠው ልዩ ፎርም ነው።

68. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. ፲ 1852 የይርጋ ማቋረጥ ውጤት።</u>

1. ይርጋው ከተቋረጠበት ጀምሮ እንደገና አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር ይጀምራል።

2. ዕዳው በአንድ ማስረጃ ወይም በአንድ ፍርድ የተረጋገጠ እንደሆነ አዲሱ የይርጋ አቆጣጠር ዘመን ሁል ጊዜ ዐሥር ዓመት ነው።

69. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 40

አንቀጽ 40 ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡንና ሰነዱን ያገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም <u>ግብር ከፋዩ ከዚህ በላይ በ35ኛው አንቀጽ በተወሰነው ጊዜ እንደሆነ፣</u> የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል። (ሰርዝ የተጨመረ)

70. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው)

አንቀጽ 55 ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የግብሩ ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰላሳ (30) ቀን ውስጥ ነው። ይግባኝ ባዩ በዚሁ በተባለው ጊዜ ውስጥ ምንም ይግባኝ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣ ወይም በዚሁ ጊዜ ውስጥ በአንቀጽ 54 በንዑስ አንቀጾች (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) ወይም (ሠ) የተወሰነውን ገንዘብ ባያሲዝ ወይም ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ በአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን የተወሰነው ግብር ትክክለኛና የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ በዚያው መሠረት በፍጥነት ይፈፀማል።

71. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 62ን ይመለከቷል።

72. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 57 ና 61ን ይመለከቷል።

73. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) ከአንቀጽ 58-6 ይመለከቷል።

74. ከእንግሊዝኛው ቅጂ በመለየት የአማርኛው ቅጂ አንቀጽ 706 (1) "በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 41 እና በዋናው አዋጅ በአንቀጽ 55 የተመለከቱት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው..." በማለት ይናገራል። ታዲያ የአማርኛውን ቅጅ ተከትሎ የሚፈፀም ከሆነ የአንቀጽ 7(ሐ)ን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ተርጓሚ የሚያደርገው ሆኖ ይታያል።

75. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 70 (ሐ)

አሠሪዎችና ሠራተኞች የየራሳቸውን ጥቅም ለማራመድ ሲሉ በውል በሚመሠረቱትና አልፎ አልፎም አወዛጋቢ ግጭቶች ሊከሰቱ በሚችሉበት በኢንዱስትሪ ግንኙነት ሥርዓት ውስጥ አሠሪው የኢኮኖሚ የበላይነቱንና የሥራ አመራር ችሎታውን በማቀናጀት ከማምረትና አገልግሎት ከመስጠት ሂደቱ የሚገኘውን ጥቅም በተቻለ መጠን አብልጦ ለመውሰድ ጥረት ሲያደርግ፣ ሠራተኞችም ድርጅታዊ ጥንካሬያቸውን መሣሪያ በማድረግ ከሚገኘው ትርፍ የተሻለ ድርሻ ለማግኘት፣ አመች የሥራ ሁኔታዎችንና አስተማማኝ የሥራ ዋስትና ለመፍጠር የበኩላቸውን ትግል ማካሄዳቸው የሚጠበቅ ነገር ነው። ሠራተኞች እነዚህንና መሰል ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞችን ለማግኘትና ለማስከበር ሲሉ በሕብረት የሚያካሂዱት የሥራ ማቆም እርምጃም የዚህ ትግል አንዱ ገጽታ ነው። እርምጃው "በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በኅብረት ሆነው ለአሠሪው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት በማጣቱ ምክንያት አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድ አሠሪውን የሚያስገድዱበት ነው።"2

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ረዳት ፕሮፌሰር፣ ቀደም ሲል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩ፣

የሥራ ማቆም እርምጃ የተጀመረውና ያደገው ለሠራተኞች የሙያ ማኅበራት መፈጠርና መጎልበት፣ እንደዚሁም ለኀብረት ድርድር ሥርዓት በር ከከፈተውና ሠራተኞች ምንዳ እየተቀበሉ አገልግሎታቸውን ለአሠሪው ከሚሸጡበት የዘመናችን የካፒታሊስት ሥልተ ምርት ነው። ሥራው የሚቆመው በጊዜያዊነት እንደመሆኑ መጠን በሁለቱ ወገኖች መሀል ያለውን የሥራ ውል ከነአካቴው የሚያቋርጥ አይደለም። ሠራተኞቹ ከሚሠሩበት ድርጅት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደተጠበቀ ነው ወደዚህ ዓይነቱ እርምጃ የሚሠማሩት። ለእርምጃው መነሻ የሚሆኑት ብዙውን ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ሲሆኑ እነኚህ የተለመደው ከመደወዙ ጥያቄ ጋር የተያያዘው ነው። የሥራ ሁኔታዎችን ለማሻሻል፣ የሥራ ደህንነት እንዲጠበቅ፣ ወይም የሥራ ሰዓት እንዲቀንስ የሚነሱ ጥያቄዎችም በዚሁ ይካተታሉ። በተጨማሪም የሙያ ማኅበራት ዕውቅና እንዲያገኙ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና አድሎአዊ የሆነ የሠራተኛ አቀጣጠር መመርያዎችን በመቃወም የሚነሱ አለመግባባቶችም ለሥራ ማቆም እርምጃ እንደመነሻ ይወሰዳሉ። እርግጥ እነዚህ የጓለኞቹ የውዝግብ ነጥቦች ከኢንዱስትሪ ግንኙነትም ባሻገር ሌሎች ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ መሆናቸው ግንዛቤ ሊያገኝም ይገባል።

የፖለቲካ ዓላማ ያላቸውን የሥራ ማቆም እርምጃዎች የተመለከትን እንደሆነ ብዙውን ጊዜ መነሻዎቻቸው የሥራ ውል ወይም አጣዳፊ የሆኑ የሠራተኞች የጥቅም ጥያቄዎች አይደሉም። በይበልጥ በሙያ ማኅበራት ፌዴሬሽኖች፣ ኮንፌዴሬሽኖች ወይም በሌሎች ኃይሎች ግፊት የሚካሄዱት የዚህ ዓይነት እርምጃዎች ዓላማቸው የሚያደርጉት ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ነው።[3]

ምንም እንኳ በቅድሚያ አለመግባባቶችን ለመፍታት የተለያዩና ተጨባጭ ጥረቶች መከናወን አለባቸው የሚሉ ሕጎች በብዛት የሚገኙ ቢሆንም የሥራ ማቆም መብት በመብትነቱ በበርካታ ሀገሮች ተቀባይነትንና ዕውቅናን አግኝቷል። ይሁም ስለተባለ የዚህ አጠቃላይ ሂደት ተስፈንጣሪ የሆኑና ማናቸውም ዓይነት የሥራ ማቆም እርምጃ ሥርዓታችንን ለማደፍረስና ለማናወጥ የታቀደ ነው የሚል አስተሳሰብ ዛሬም የሚያስተናግዱ የሕዝቦቻችውን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በፈላጭ ቆራጭነት የሚቆጣጠሩ

አገዛዞቹም አይታጡም። ዳሩ ግን በብዛት ተቀባይነት ያገኘው አመለካከት ለዚህ መሠረታዊ መብት ዕውቅናን የሚሠጥ ነው።

በግዳጅ ላይ ያለው ዓለም ዓቀፍ ሕግም ከዚህ ጋር የሚጣጣም ነው። ማንም ሰው ... የመሥራት መብት፣ የሚሠራውን ሥራ የመምረጥ መብት፣ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሥራ ሁኔታዎችን የማግኘት መብት ... እንዳለው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባወጣው ሁለተናዊ የሰብዓዊ መብት መግለጫ አንቀጽ 23 ተመልክቷል። ከዚህም በተያያዘ የሥራ ማቆም መብት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በተቀበለው የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 8 ላይ በማያሻማ ሁኔታ ተቀምጧል።

የዓለም የሥራ ድርጅትም እንደዚሁ የሠራተኛውን ወገን የመደራጀት ነፃነትና የሕብረት ድርድር የማካሄድ መብት የሚደነግጉ ብዛት ያላቸው የቃል ኪዳን ስምምነቶችና የድጋፍ ሀሳቦች አጽድቆ አውጥቷል። ፈራሚ ሀገሮች እነዚህን መብቶች አውቀው እንዲቀበሉ፣ በግዛታቸው ውስጥም ለተግባራዊነታቸው ተገቢውን ማረጋገጫ እንዲሰጡ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።[6]

እነዚህ የቃል ኪዳን ስምምነቶችና የድጋፍ ሀሳቦች ሠራተኞች እንደምርጫቸው ማህበር ለማቋቋምና አባል ለመሆን፣ የመተዳደርያ ደንቦቻቸውን ለማውጣት፣ ተወካዮቻቸውን ለመምረጥ፣ የውስጥ አስተዳደራቸውንም በሙሉ ነፃነት ለማካሄድ ያሏቸውን መብቶች ያረጋግጣሉ። የሠራተኞች ማኅበራትን በጊዜያዊነት የሚያግዱ፣ ወይም ለዘለቄታው የሚያፈርሱ፣ ወይም በሠራተኛ አቀጣጠርና በዕድገት አሰጣጥ ረገድ የሚወሰዱ አድሏዊ ፀረ-ማኅበር እርምጃዎችን፣ እንደዚሁም ሠራተኞች በማኅበር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ከሥራ የማባረር ድርጊቶችን፣ አጥብቀው ይከላከላሉ። ማኅበራት የተቋቋሙበትና ተመዝግበው የሚሠሩበት ብሄራዊ ሕግም ቢሆን እነዚህን መብቶች በሚያጠብ ወይም በሚያጣምም መልኩ ገቢራዊ መሆን እንደሌለበት ያመለክታሉ።

የሥራ ማቆም መብት

የዚህ ጽሁፍ ቁልፍ ፍሬ ነገር አወዛጋቢ የሆነው የሥራ ማቆም መብት በኢትዮጵያ ያለውን ገጽታ መመርመር ሲሆን ቀጥለን ይህንኑ ጉዳይ ካለፉትና አሁን በሥራ ላይ ካሉት ሕጎች ጋር በማነፃፀር፣ ከፍ ብለን ካየናቸው መለኪያዎች ጋርም በማስተያየት ጠቅለል ባለ መልክ እናያለን።

2. <u>ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 210/1956</u>፡

የኢትዮጵያን ሕግጋት ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ ይህ አዋጅ የኢንዱስትሪ ግንኙነት አስመልክቶ ከወጡት ሕግጋት ውስጥ ቀዳሚውን ሥፍራ መያዙን እንረዳለን። በአዋጁ መግቢያ የተገለጸው የሕጉ ዓላማ ከሚገልጻቸው ቁም ነገሮች አንዱ አመች የሥራ ሁኔታዎችን መፍጠርና የሥራ ክርክሮችም በሕብረት ድርድር የሚፈቱበትን ዘዴ መቀየስ ነው። የሥራ ክርክር ማለትም ስለሠራተኞች ሁኔታ ስምምነት ወይም አያያዝ፣ ወይም ስለሠራተኞች ሁኔታ ለመነጋገር፣ ስምምነቱን ለመወሰን፣ ለመጠበቅ፣ ወይም የሠራተኞችን ሁኔታ በማሻሻል ረገድ የአሠሪዎች ወይም የሠራተኞች ወኪል ለመሆን መብት አለን ስለሚሉ ሰዎች ተገቢነት ወይም ሥልጣን የሚያነሳ ማናቸውም ክርክር ነው ተብሎ ተተርጉሟል።[5]

የሥራ ክርክሮችን አይቶ የሚወስን የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የተባለ አካል እንዲቋቋምም ተደርጓል። የዚህ ቦርድ ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባሮችም የሥራ ክርክሮችን ማየት፣ ተከራካሪዎችን ማስታረቅና መገላገል፣ ተገቢ ስላልሆነ የሥራ አፈጻጸም የሚቀርቡ ማናቸውንም አቤቱታዎች ማየት፣ እንደዚህ ያለውን አፈጻጸም መከላከልና ይህንን ተግባር እንዲተውት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማዘዝ፣ ውሳኔዎቹንና ብይኖቹን አግባብ ባለው መንገድ ማስፈጸም፣ ድርጅቶች እንዲፈርሱ ለሕዝባዊ ኑሮ እድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር አሳብ ማቅረብ፣ ነበሩ።[6] ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ወገን ይግባኙን በጊዜው ለነበረው የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ነበረው። ለይግባኙ መሠረት ይደረግ የነበረው የቅሬታ ነጥብ ግን ቦርዱ በፍሬ ነገር ጉዳዩ ላይ በወሰደው አቋም ላይ ሳይሆን በሕግ አተረጓጎም ረገድ ፈጸሟል በተባለው ስህተት ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን ይጠበቅ ነበር። ፍርድ ቤቱም የቦርዱ ውሳኔ በሕግ ረገድ የተሳሳተ ሆኖ ካገኘው

መፈጸም አለበት ብሎ ያመነበትን የራሱን ትእዛዝ በማስፈር በርዱ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ መልሶ ይልክለታል።[7]

በተጨማሪም ይህ አዋጅ የአሠሪዎችንና የሠራተኞችን የመደራጀት መብት ያወቀና የኅብረት ድርድር ሊካሄድ የሚችልበትን ሥርዓት የዘረጋ ነበር። ከዚህም በሻገር የሠራተኞች ማኅበራት በዘርፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ ማኅበራት የሚያቋቁሙበትንና የሚቀናጅበትን መርሆ በመብት ደረጃ ተቀብሏል።[8] በሕግ ደረጃ የሥራ ማቆም እርምጃ ምን እንደሆነ አዋጁ ሲተረጉም፣

> ... በአንድ የሥራ ክርክር ምኞታቸው እንዲፈጸም ለማድረግ ብዙ ሠራተኞች ተስማምተው ለጊዜው የሚያደርጉት ሥራ ማቋረጥ ማለት ነው።[9]

ይለዋል። ምንም እንኳ ይህ አረተጓጎም በአዋጁ የሠፈረ ቢሆንም ሠራኞች ምላሽ አልባ የሆነው ጥያቄያቸው ተፈጻሚ እንዲሆን ብለው የሥራ ማቆም እርምጃ መውሰድ የሚችሉ መሆናቸውን በግልጽ የሚያመለክት አንቀጽ አይገኝበትም። እርምጃውን መውሰድ አይችሉም ተብሎ በግልጽ የተደነገገ ነገርም የለም። በተዘዋዋሪ አዋጁ ተገቢ የልሆኑ የሥራ አፈጻጸሞች የተከለከሉ ናቸው ይልና አንዳንድ የሥራ ማቆም እርምጃዎችን በእነዚህ በተከለከሉ ተግባሮች ውስጥ የካትታቸዋል።[10] በተከለከሉትና በተፈቀዱት የሥራ አፈጻጸሞች መሀል ያለውን ችግር በውል ማመልከቱ አስቸጋሪ መስሎ ቢታይም ይህንን አንቀጽ በመጠኑም ቢሆን ቀጥለን እንመረምራለን።

በሁሉም ዓይነት የሥራ ማቆም እርምጃዎች ላይ የተጣለው የመጀመርያው ማዕቀብ ከሠራተኞች ማኅበራት በስተቀር ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን የሥራ ማቆም እርምጃ ለማነሳሳት፣ ለማደራጀትና ለማካሄድ ያለመቻሉ ጉዳይ ነው። የቱንም ያህል የከበደ የሥራ ክርክር ከአሠሪያቸው ጋር ቢኖራቸው፣ የሙያ ማኅበር የሌላቸው ሠራተኞች የሥራ ማቆም እርምጃን መወጠንም ሆነ ማካሄድ አልተፈቀደላቸውም ነበር። ምንም እንኳ ከሌሎች የሥራ ተቋሞች ሠራኞች ጋር በመሆን አጠቃላይ የሙያ ማኅበር ማቋቋም ይችሉ የነበረ ቢሆንም ከሃምሳ በታች ሠራተኞች በነበሩበት የሥራ ተቋም ማኅበር ለማቋቋም አዋጁ አልፈቀደም። በጊዜውም አጠቃላይ የሠራተኛ ማኅበራትን ማቋቋም እምብዛም የተለመደ አልነበረም።

ለሠራተኞች ማኅበራት በሕግ ከተፈቀደው የሥራ ድርሻ ወሰን አልፎ የሥራ ማቆም እርምጃ ማነሳሳትና ማካሄድም በአዋጁ ትርጉም ተገቢ ያልሆነ የሥራ አፈጻጸም ነበር። የማኅበራት የሥራ ድርሻ ተብለው ከተመለከቱት ውስጥ በአዋጁ የተገለጹትን የሥራ ሁኔታዎችና አፈጻጸሞች መወሰን፣ የአባላትን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሞራል ጥቅሞች ማጥናት፣ መጠበቅ ማሳደግ፣ የሚሉት ይገኙበት ነበር። በተጨማሪም የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ያለሥጋትና በፈቃደኝነት መነጋገር፣ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቁ ማድረግ ከማኅበራት ተግባር ሌላው ዘርፍ ነበር።[11]

በዚህ መሠረት ሳይፈጸምና በቅን ልቦና የተደረገ ንግግር ሳይኖር በእልህ ተጀመረ የተባለን የሥራ ማቆም እርምጃ አዋጁ ተገቢ ባልሆነ የሥራ አፈጻጸም ውስጥ ይመድበው ነበር። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ አወዛጋቢ ጥያቄዎች የሚነሱት። በእልህ የተጀመረ የሥራ ማቆም እርምጃ ማለት ምን ማለት ነው? ማህበራት በቅን ልቦና ለመደራደር ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው የሚታወቀው እንዴት ነው? ለመሆኑ "ቅን ልቦና" እና "እልህ" ስንል ምን ማለታችን ነው? የእነዚህን ፍሬ ነገሮች መኖርና አለመኖር የሚወስነውስ ማን ነበር? ለእነዚህና በተጓዳኝ ለሚነሱ አስቸጋሪ ጥያቄዎች አዋጁ የሚሰጠው መግለጫ ባይኖርም አተረጓጐሙ በጊዜው ይህንሕግ ለማስፈጸምና ደንቦችንም ለማውጣት ሰፊ ሥልጣን ተሠጥቶት ለነበረው የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የተተወ ነበር ብሎ መገመት ይቻላል።[12] ሌሎች አካላት ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድና የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ነበሩ።

ሌላው በዚህ አዋጅ የተከለከለና ሕጋዊ አይደለም የተባለ አፈጻጸም ደግሞ ለሥራ ማቆም እርምጃው መንስኤ ነው የተባለው የሥራ ክርክር ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ከመቅረቡ በፊት የተደራጀና የተጀመረ፣ ወይም የቦርዱን የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በመቃወም የተደራጀና የተጀመረ የሥራ ማቆም እርምጃ ነበር። በቅድሚያ ለውዝግብ መንስኤ በሆነው ጉዳይ ላይ ከአሠሪው ጋር መወያየት ግድ ነበር። ንግግሩ ሁሉቱንም ወገኖች የሚያመረቃ ውጤት ካለመጣ ጉዳዩ አቦርዱ ዘንድ መቅረብ ነበረበት።

ቦርዱ አለመግባባቱን ለመፍታት አመቺ የሆኑትን ዘዴዎች ተጠቅሞ አጥጋቢ ውጤት ላይ መድረስ ካልቻለ ሁለት አማራጮች ነበሩት። አንዱ ተገቢ ናቸው የሚላቸውን መፍ ሀሳቦች በማስፈር የሠራተኞች ማኅበሩ ያቀረበውን የሥራ ማቆም እርምጃ ጥያቄ እንዲያነሳ ማዘዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው የሥራ ማቆሙ እርምጃ እንዲቀጥልና አሠሪው በዚህ እርምጃ እንዲገደድ ማድረግ ነበር። እንደዚሁም የሠራተኞች ማህበሩ ጥያቄውን ለቦርዱ ካቀረበና ይህም አካል በስድሳ ቀን ጊዜ ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ሕጋዊ የሥራ ማቆም እርምጃ መውሰድ ይችል እንደነበር አዋጁ ይጠቁማል። የተባለው ጊዜ ካለፈ የቦርዱ ዝምታ ብቻውን እርምጃውን ሕጋዊ ያደርገዋል።

ማዕቀቡ በዚህ ብቻ አያበቃም። የሥራ ማቆም እርምጃ በኃይል ተግባር ከተደገፈ፣ የማስፈራራት ጉዳይ ካለበት ወይም አግባብ ያልሆነ መግለጫ የተሰጠበት ከሆነ አሁንም ሕገ-ወጥ ነበር። የኃይልና የማስፈራራት ሁኔታዎች የሚሉትን አባባሎች መረዳት አዳጋች አይደለም። "ሕገ-ወጥ የሆነ መግለጫ" የሚለው ሀሳብ ግን አወዛጋቢ ነው። ሕጋዊና ሕገ-ወጥ ተብለው የሚለዩት የመግለጫ ዓይነቶች እንዴት ያሉት ነበሩ? ማኅበራት የሥራ ማቆም እርምጃውን በሚመለከት ጽሁፎችንና በራሪ ወረቀቶችን ለአባላትና ለሕዝብ ማሠራጨት አይችሉም ማለት ነውን? ስለእርምጃው የሚሰጡትን ዜና በመንግሥት ቅድመ ምርመራ /ሳንሱር/ ክፍል ማሳለፍ ይጠበቅባቸው ነበርን? ስለእርምጃው ጋዜጣዊ መግለጫ ቢሰጡ ሕጋዊ አይደለም ይባል ነበርን? የመግለጫውን ሕጋዊነትስ የሚወስነው ማን ነበር?

ከዚሁ ጉዳይ ሳንወጣ በመጨረሻ የምንመለከተው ሕጉ ሥራ ማቆም በሚችሉና በማይችሉ ሠራተኞች መሀል የሚያደርገውን ልዩነት ነው። ይህ ልዩነት የተፈጠረው በሚሠራው ሥራ ሕዝባዊ ጠቀሜታና በአገልግሎቱ አስፈላጊነት ላይ ነው ተብሎ በአዋጁ ተገልጿል። ለምሳሌም ያህል በኤሌክትሪክ፣ በውሃ፣ በሌሎችም የሕዝብ አገልግሎቶች፣

በቴሌፎንና በቴሌግራፍ መገናኛዎች፣ እንደዚሁም በትራንስፖርት አገልግሎቶች የተሰማሩ ሠራተኞች ሥራ ቢያቋርጡ ድርጊቱ ሕጋዊ አልነበረም። ከትራንስፖርት አገልግሎቶች በስተቀር የተቀሩት አገልግሎቶች የዝያን ጊዜም ሆነ ዛሬ በመንግሥት ባለቤትነትና አመራር ሥር የነበሩና ያሉ ናቸው።[13]

የሥራ ማቆም ገደቡ በእነዚህ ሠራተኞች ብቻ የተወሰነ እንዳልነበር የአዋጁ አነጋገር ይጠቁመናል። ታዲያ ዝርዝሩን እንዴት አድርጎ መገደብ ይቻል ነበር? ይህም ጉዳይ ለሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትሩ የተተወ ነበርን? ነገሩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርዱንና የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤትን የሥራ ብቃትና የዳኝነት ነፃነት የሚፈታተን ነበር ማለት ይቻላል። አሠሪዎችና ሹሞች የሚታሰብባቸውን የሥራ ማቆም እርምጃ ለመከላከል ሥራው እጅግ አስፈላጊ ነው ብለው ክርክር ቢያነሱ የሚያገኙቸው ነገር ነበርን? የሥራ ማቆም እርምጃ በመሠረቱ የሚፈለግ ክስተት አይደለም። በአመዛኙ ሠራተኞች ይህን እርምጃ ለመውሰድ የሚገደዱት ክርክሩን በመግባባት ለመጨረስ የሚያደርጉዋቸው ጥረቶች ሁሉ ፍሬ አልባ ሆነው ሲቀሩ ነው። ጥያቄያቸውን ገቢራዊ ለማድረግ የሚጠቀሙበት የመጨረሻው የትግል መንገድ ነው። "የሕዝብ አገልግሎት" ለሚለው ሐረግ ሚዛናዊ ትርጉም ካልነበረ ውጤታማ የሥራ ማቆም እርምጃ በዚህ አዋጅ ይቻል ነበር ብሎ በልበ ሙሉነት መናገር አዳጋች ነው።

3. <u>የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 64/1968</u>

ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 210/1956 የተተካው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በሀገሪቱ የፖለቲካ ሥልጣን መንበር ከተቀመጠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባወጣው የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 64/1968 ነው። በኋለኛው አዋጅ የቀድሞው አዋጅ መሻሩን የሚያመለክት ግልጽ የሆነ አንቀጽ ባይኖርም በቁጥር 111

ላይ "ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ደንቦችና ውሳኔዎች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም" የሚለው ኃይል ቃል የተደገፈው አዋጅ በኢንዱስትሪ ግንኙነቶች ላይ የነበረውን ተፈጻሚነት አስቀርቷል። የአሠሪዎች ማኅበራትን የሚመለከት እንጋገርም በአዋጁ አይገኝም። ሆን ተብሎ ይሁን ወይም በሌላ ሰበብ "አሠሪ" የሚለው ቃል "ድርጅት" በሚለው መተካቱን እንገነዘባለን። እንዚህ የፅንፍ ሀሳብና የቃላት ለውጦችና ግድፈቶች በዘመኑ የነበሩት ፖሊሲ አውጭዎች በማስመሰልም ሆነ ከልብ ለኮሙኒስታዊ አስተሳሰብ ያላቸው የነበረውን ዝንባሌ የሚጠቁሙ መሆናቸውን መገመት ይቻላል።

ይህ አዋጅ የኢንዱስትሪ ግንኙነቶችን በተመለከተ ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን ያካተተ ቢሆን የራሱ የሆኑ በጎና ደካማ ጎኖች ነበሩበት። የአንዳንዶቹ አንቀጾች ትርጉምም እጅጉን ሊያወዛግብ የቆየ ነበር። ወደ ዝርዝሩ መግባት የጽሁፉ ዓላማ ባለመሆኑ ፍተሻችንን የመደራጀትንና የሥራ ማቆም መብትን በሚመለከቱት አንቀጾች ዙሪያ ብቻ እናሰባስባለን።

ሠራተኞች በዚህ አዋጅ ማዐበር ለማቋቋምና በአባልነት ለመሳተፍ መብት የነበራቸው መሆኑ፣ የሠራተኞች ማኅበራት የኢንዱስትሪ ማኅበራትን ለማቋቋምና በአባልነት ለመሳተፍ መቻላቸው፣ የኋላኞቹም በደረጃቸው የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር /መኢሠማ/ እየተባለ ይጠራ የነበረውን ሀገር አቀፍና ብቸኛ አጠቃላይ ማኅበር ለመመሥረት መቻላቸው እርግጥ ነበር።[14] የማኅበራቱ ድርጅታዊ አወቃቀር ከላይ እስከታች የተዘረጋና አንድ ወጥ የሕዝ ሠንሰለትን ኀቢራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተቀመጠ ቢሆን ዓላማው "ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት" እየተባለ ይሞካሽ የነበረውን የአደረጃጀት መርህ የተከተለ ነበር። በአዋጁ መሠረት በአንድ የሥራ ተቋም ውስጥ የሚቋቋመው አንድ የሠራተኞች ማኅበር ብቻ ነበር። የበታች ማኅበራት

ለበላዮቻቸው ታዛዥ እንዲሆኑና አባሎቻቸም ጠንካራ ዲሲፕሊን እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸው ነበር። እንደዚሁም እነዚህ ያሉት ማኅበራት የላይኞቹን መመርያዎችና ውሳኔዎች ተቀብለው ከሥራ ላይ እንዲያውሉ ይገደዱ ነበር።[15]

ሁሉም ማኅበራት የመንግሥት አካላትን በተለይም ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ "አመራር የመስጠት ኃላፊነት" በሕጋዊ ቡራኬ የተረከበውን በወቅቱ የነበረውን ፓርቲ ደንቦች የማክበርና ትእዛዙንም የመፈጸም ግዴታ ነበረባቸው።[16] በተጨማሪም ማንኛውም ማኅበር ሠራተኛው ሕጎችን፣ደንቦችን፣ ስምምነቶችን፣ የሥራና የአሰተዳደር ሥርዓቶችን አክብሮ መሥራቱን የመከታተል ኃላፊነት ነበረበት።[17] ከአዋጁ በፊት ተቋቁመው የነበሩት የሠራተኛ ማኅበራት በሙሉ ፈርሰው መብትና ግዴታዎቻቸው በዚህ አዋጅ መሠረት በምትካቸው ለተቋቋሙት ማኅበራት ተላለፈ። በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ተቋቁመው የነበሩት በርካታ ማኅበራት በነፃ ፈቃዳቸው በአንድነት ሆነው የመሠረቱትና የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር /ኢሠአማ/ በመባል ይታወቅ የነበረው አጠቃላይ ማኅበር ዕጣ ፋንታም ከእነበተኞቹ ማኅበራት የተለየ አልነበረም። ማኅበሩ ፈርሶ መብቶችና ግዴታዎቹ በሙሉ ለመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ተላልፈዋል።[18] ይህ የጓለኛው አገር አቀፍ ማኅበር በሕግ ደረጃም ቢሆን በሀገሪቱ ያሉ ሠራተኞች ተጠሪ መሆኑ ተገልጾ "... የሠራተኛውን እንቅስቃሴ በበላይነት የመምራት፣ የመቆጣጠርና ማኅበሮች ተግባራቸውን በኅብረሰብዓዊነት ፍልስፍና መሠረት እንዲያካሂዱ መመርያዎች የመስጠት ..." ሥልጣን ተሠጥቶት ነበር።[19]

ዳሩ ግን ይህ ማኅበራትን ከአንድ ቋቱ እየፈለፈሉ የማዋቀርና የማደራጀት ስልት፣ ሠራተኞች በፈቀዱት መንገድ እንዳይደራጁከ የሚያደርግና ምርጫቸውንም የሚያጠብ ነው እየተባለ በብዙ አካላት ቢነቀፍ ቆይቷል። ይህን በተመከተ ለምሳሌ ያህል

አንድ የዓለም የሥራ ድርጅት የባለሙያዎች ቡድን አዋጁን መርምሮ በሰጠው አስተያየት አዋጁ ሠራተኞች በመረጡት መንገድ ማኅበር ለመመሥረትና በሚፈልጉት ማኅበር ውስጥም አባል ለመሆን ይችላሉ ተብሎ በዚሁ ዓለም አቀፍ ድርጅት የወጣውን፣ የመደራጀት ነፃነትንና የማኅበራትን አቋም የሚጠብቀውን፣ በቁጥር 87 የሚታወቀውን፣ ኢትዮጵያም ብትሆን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ ከረዥም ጊዜ በፊት የተቀበለችውን፣ የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 2 የማይከተል ነው ብሎታል።[20] ይኸው ሪፖርት በተጠናከረና በተጠቃለለ መልክ የሚዋቀር የሠራተኞች ማኅበር አስፈላጊ በሆነ መንገድ ተበታትነው ከሚሠሩ ማኅበራት አንጻር የሚኖረውን ጠቀሜታ ያወሳና ይህ ሲባል ግን ማኅበራት መጠቃለል ያለባቸው በራሳቸው ፈቃድና ፍላጎት ብቻ እንጂ በአዋጅ መሆን እንደሌለበት ያስገነዝባል። ሪፖርቱ ይህንኑ አባባል በመቀጠል፣

> ...የሠራተኞችን ማኅበራትን በሞኖፖል /በብቸኝነት/ ለማጠቃለል በአዋጅ መልክ በሚወሰድ እርምጃና፣ ሠራተኞች ራሳቸው ወይም ማኅበሮቻቸው የነገሮችን ነባራዊ ሂደት በሚገባ አጢነው፣ የአዋጅ መውጣት አስፈላጊ ሳይሆን፣ በገዛ ፍላጎታቸው በአንድ አጠቃላይ ድርጅት በሚታቀፉበት የአደረጃጀት ስልት መሀል መሠረታዊ የሆነ ልዩነት እንዳለ ...[21] መገንዘብ ያስፈልጋል ይላል።

የሥራ ማቆም እርምጃን በተመለከተ አዋጁ፣ የሚሰጠው ትርጉም ቀደም ሲል ከነበረው አዋጅ አተረጓጎም ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። በተጨማሪም ሥራን ማቀዝቀዝ፣ ሁከት መፍጠርና ሠራተኞችን እንዳይሠሩ ማድረግም በዚሁ ትርጉም ውስጥ ተካትተዋል።[22] ይህም አዋጅ ቢሆን የሥራን ማቆም መብት በግልጽ የሚያረጋግጡ አንቀጾች የሉትም። ዳሩ ግን ሕገ ወጥ የሆነ የሥራ ማቆም እርምጃን ምንነት ሲያመለክት፣

በማናቸውም ድርጅት ውስጥ

1. የሠራተኞች ማኅበር ተካፋይ የሆነበት የወል የሥራ ክርክር ሳይኖር፣ ክርክር ቢኖርም በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ከመቅረቡ በፊትና ከቀረበም በኋላ ውሳኔ ሳይሰጥበት፣ ሃምሳ (50) ቀን ከመፈጸሙ በፊት በሠራተኛ ወይም በሠራተኛ ማኅበር የተጀመረ፣

2. የአመራር ወይም የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ችሎት የሠጠውን ውሳኔ በመቃወም የተጀመረ፣

3. በማኅበሩ መተዳደርያ ደንብ ከተወሰነው ውጭ የተደረገ፣[23] ሥራ ማቆም ነው ይላል።

የአንቀጹ ተግባራዊነት የሚያስከትለውን ችግር መገመት ከባድ ባይሆንም በውስጡ ያለውን መልዕክት በቅጡ የሚመረምር ሁሉ ቀጥሎ ያሉትን ነጥቦች ሳያስተውል አያልፍም።

እላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳ አዋጁ የሥራ ማቆም እርምጃን በመብትነት በግልጽ ባያውቅም፣ ይህን አንቀጽ በተዘዋዋሪ በመተርጎም በሕግ የተፈቀደው የሥራ ማቆም እርምጃ እንዴት ዓይነቱ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በባሕርያቸው የሥራ ማቆም እርምጃዎች ያልተፈቱ አለመግባባቶች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች ናቸው። ይሁንና ሁሉም ዓይነት የሥራ ክርክሮች ወደዚህ እርምጃ እንደማያደርሱ አዋጁ ይናገራል። በመጀመርያ ደረጃ የውዝግቡ ዓይነት የግል ሳይሆን የወል የሥራ ክርክር መሆን ያስፈልገው ነበር። እርምጃውን ማቀነባበርና ማካሄድ የሚችለውም በሥራ ተቋሙ የተቋቋመው የሠራተኛ ማኅበር ብቻ ነበር። እዚህ ጋ

ጥያቄዎች ቢነሱ አግባብ ይሆናል። የግልና የወል የሥራ ክርክር ስንልም ማለታችን ነው? በግል የሥራ ክርክር በአሠሪው ከፍ ያለ በደል ለተፈጸመበት ባልደረባቸው ሠራተኞች የሚያበረክቱት የትግል ድጋፍ በምን መልኩ እንዲገለጽ ይጠበቅ ነበር?

እርግጥ የሁለቱም የሥራ ክርክር ዓይነቶች ትርጉም በአዋጁ ተቀምጧል። ልዩነቶቹን በውል መረዳት ግን አዋጁን በግርድፉ የማንበብን ያህል ቀላል አልነበረም።[24] ይሁንና አንድ ጊዜ ክርክሩ የወል ነው ከተባለ የሥራ ማቆም እርምጃውን ለማቀነባበርና ለማካሄድ መብት የነበረው ማኅበሩ ብቻ ነበር። የክርክሩ ጉዳይ የቱንም ያህል የከበደና ሠራተኞቹን በጥቅል የሚመለከት ቢሆንም ከማኅበሩ ውጭ ሌላ አካል ወይም ግለሰብ ሠራተኞች ሥራን የማቆም እርምጃን ማካሄድ አይችሉም ነበር። የክርክሩ ጉዳይ ራሱ የሙያ ማኅበሩ ባለበት የሥራ ተቋም ያሉትን ሠራተኞች ብቻ የሚመለከት እንዲሆን ይጠበቅ ነበር። ሌሎች ጉዳዮችን ከቶውንም ማንሳት አይቻልም። ይህም ገደብ ጠቅላላና ድጋፍ ሰጭ የሥራ ማቆም እርምጃዎች ማካሄድን የማይፈቅድ አድርጎት ቆይቷል።

አለመግባባቱን በሰላም ለመጨረስ መከተል ያስፈልግ የነበረውን ስርዓት ስንዳስስ ደግሞ ቀጥሎ ያሉትን እናገኛለን። ውጤት ያለው የሥራ ማቆም እርምጃ ከመወጠኑ በፊት የሠራተኛ ማኅበር ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ማቅረብ ነበረበት። እዚያም ከቀረበ በኋላ በሕግ የተመለከተው የሃምሳ ቀን ጊዜ እስኪያልፍ መጠበቅ አስፈላጊ ነበር። ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ካልተቀበለ ነገሩ እዚያው ያልቅለታል። ውሳኔውን ባለመቀበል በእርምጃው መግፋት በነፃነት ወይም በገንዘብ እንደሚያስቀጣ የወንጀል ተግባር ይወሰዳል።

ሌላው መሰናክል ደግሞ የማኅበር መተዳደርያ ደንብን በተመለከተ የተቀመጠው ነበር። በዚህ ዓይነት ደንብ ከተመለከተው ውጭ የሥራ ማቆም እርምጃ ማካሄድ እንደ ሕገ ወጥ ድርጊት ይገመት ነበር። የማኅበራት መተዳደርያ ደንቦች መያዝ ከሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ የማኅበሩ ዓላማ፣ የማኅበርተኞች መብትና ግዴታ፣ የመሪዎች ተግባርና ሀላፊነት። ጠቅላላና ልዩ ስብሰባዎችን የሚመለከቱት እንደሚገኙበት በአዋጁ ተመልክቷል።[25] የሥራ ክርክሮች የሚፈቱበት ሥርዓት በመተዳደርያ ደንቡ መመልከት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ አዋጁ የሚለው የለም። ነገር ግን በመተዳደርያ ደንብ ወስጥ የሚገቡ ጉዳዮች በአዋጁ የተገደቡ ባለመሆኑ አዋጁን እስካልተጻረሩ ድረስ ማኅበራት ውዝግብን በመፍታት ረገድ መከተል ያለባቸውን ሥርዓት በደንቡ ውስጥ ከማስቀመጥ አይከለከሉም ነበር ብሎ መገመት ይቻላል። እንዲህ ከሆነም ደንቡን ሳይጠብቁ የሥራ ማቆም እርምጃ መውሰድ አይቻልም ነበር።

በእነዚህ በሥራ ማቆም እርምጃ ላይ በተደቀኑ እሰቸጋሪ መሰናክሎች ላይም የእለም የሥራ ድርጅት ባለሙያዎች ነቀፋ ሳይሠነዝሩ አላለፉም። እላይ የተጠቀሰው እንቀጽ የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በዘገባቸው ሲተቹ "ሠራተኞች መብታቸውን ለማስከበር ሊሉ መውሰድ ያለባቸውን የሥራ ማቆም መብት የሚያሽመደምድ "እስከማለት ደርሰዋል። አያይዘውም "...ከልክላው ለሠራተኞች የተከፈተውን የመብት ማስከበር ጎዳና የሚዘጋ ነው..." ካሉ በኋላ ብሄራዊ ሕግም ቢሆን ይህን በዓለም አቀፍ የቃል ኪዳን ሰምምነት የተጋገጠውን መብት ለማደናቀፍ በታቀደ ዓላማ ኀቢራዊ ሊሆን እንዳማይገባው ጠቅሰው "... የሠራተኞች ማኅበራት ጉዳያቸውን በነፃነት የመምራት መብታቸው ..." እንዳከበር በመጠየቅ ዘገባቸውን ደምድመዋል።[26]

4. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985

የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ኃይሎች [27] ሀገሪቱን ከተቆጣጠሩና የደርግ ዘመን መንግሥት ካከተመ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የዛሬው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ተመሥርቷል። አዲሶቹ መሪዎች በበኩላቸው የሀገሪቱን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መዋቅር ይበጃል በሚሉት አስተሳሰብ ለማነጽ ከወሰዱዋቸው እርምጃዎች አንዱ ሌላ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ እንዲወጣ ማድረግ ነው።

አዲሱ አዋጅ አሠሪዎችና ሠራተኞች በየበኩላቸው ማኅበራቸውን ለማደራጀትና በንቃት ለመሳተፍ ያላቸውን መብት ይቀበላል። የአሠሪዎችም ሆነ የሠራተኞች ማኅበራት በፌዴሬሽንና በኮንፌዴሬሽን ለመደራጀት የሚችሉ መሆናቸውንም ያመለክታል።[28] ይሁንና በአንድ የሥራ ተቋም ውስጥ ማቋቋም የሚቻለው አንድ የሠራተኞች ማኅበር ብቻ ነው። ይህም ማኅበር የሚቋቋመው በሥራ ተቋሙ ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ብዛት ከሃያ ያላነሰ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው። ቁጥራቸው ከሃያ በታች የሆኑ ሠራተኞች ባሉባቸው የሥራ ተቋሞች የሚገኙት ሠራተኞች ማኅበር ማቋቋም የሚችሉት በሌሎች ተመሳሳይ ተቋሞች ካሉ ሠራተኞች ጋር በመቀናጀትና ሕግ የጠየቀውን ቁጥር በማሟላት ነው።[29] ይህ አካሄድ ቀደም ሲል ከነበረው የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተወሰደ ነው።

የማኅበራትን ድርጅታዊ አወቃቀርና አቋም የሚናገሩትን የአዋጁን አንቀጾች ስንመለከት አዲሱ አዋጅ ቀደምሲል በነበረው በአዋጅ ቁጥር 64/1968 የነበሩትን አንዳንድ ማዕቀቦች እንዳስወጣ እንረዳለን። የሕጉ ተግባራዊ አፈጻጸም ወደፊት የሚታይ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ አጠቃላይ ማኅበር ወይም ኮንፌዴሬሽን ብቻ ይቋቋማል የሚል አንቀጽ አይገኝበትም። ይልቁንም ቃሉን "ኮንፌዴሬሽኖች" ብሎ

በማስቀመጥ ከአንድ በላይ አጠቃላይ ማኅበሮች ሊቋቋሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ይጠቁማል። ማዕከላዊ አሠራርንና ከአባላት ይጠበቅ የነበረውን የጥብቅ ዲሲፕሊን መመዘኛ የሚመለከቱ ጉዳዮችም ከሕጉ እንዲወጡ ተደርጓል። የመንግሥት ሹማምንትና የፖለቲካ ቡድኖች በማኅበራት ጉዳይ ሊያደርጉ የሚችሉትን ጣልቃ ገብነት እስከተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመቀነስ አዝማሚያ በሕጉ ይታያል።

የሠራተኞች ማኅበራት፣ ፌዴሬሽኖችና ኮንፌዴሬሽኖች የሚቋቋሙበት ዋና ዓላማ የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር መሆኑ የማያከራክር ነው። እንግዲህ ከዚህ መሠረታዊ ነጥብ በመነሳት አዋጁን ስንመረምር ሕግ አውጭዎቹና ሕጉን በማርቀቁና በማስፈጸሙ ረገድ ሃላፊነት ያለባቸው አካላት ይህን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለባለቤቶቹ ለመተው ያላቸውን ፍላጎት እትርጓሜ ላይ የሚገኝ አንቀጽ እናገኛለን። ይህም ትርጓሜ የሚመነጨው ማኅበራት፣ ፌዴሬሽኖቻቸውና ኮንፌዴሬሽኖቻቸው፣

> ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና መግለጫዎች በአባሎች እንዲታወቁ፣ እንዲከበሩና በተገቢው ሁኔታ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣[30]

ተግባራቸው ይሆናል ተብሎ ከተገለጸበት የአዋጁ አንቀጽ ነው።

እዚህ ላይ አንድንድ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። በመሠረቱ ይህን አባባል በሕግ ቀርጾ ማስቀመጥ ለምን አስፈለገ? የሠራተኛ ማኅበር የሕግ አስፈጻሚ አካላትን ተግባርም እንዲያከናውን ሊጠበቅበት ነውን? አባላቱስ እንዴት አድርገው ነው የመንግሥት ሕጎችን፣ደንቦችን፣ መመርያዎችንና መግለጫዎችን የሚያስፈጽሙት? ይህን ተግባር ባልፈጸመ ሠራተኛ ላይ ማኅበሩ የሚወስደው እርምጃ ምንድን ነው?

ሕግን ማክበር በማንም ሰው ላይ የተጣለ ግዴታ ነው። ስለማኅበራት ምሥረታና ስለመደራጀት መብት በአለም የሥራ ድርጅት የወጣው የቃል ኪዳን ስምምነትም ቢሆን

ይህን ጉዳይ እሌ አይለውም። ይህ ማለት ግን ሕጎችንና ደንቦችን የማሳወቅና የማስከበር ተግባር የሠራተኛ ማኅበራት ሥራ ነው ማለት አይደለም። ለዚሁ ጉዳይ ብሎ ራሱ መንግሥት ያቋቋማቸው አውታሮች አሉ። አንድ ሠራተኛ በማኅበር የሚታቀፈውም እነዚህን ጉዳዮች ለመፈጸምና ለማስፈጸም ሳይሆን ከሌሎች መሰሎቹ ጋር በመሆን ጥቅሙን ለመጠበቅና ለማራመድ ነው። ማንም ሰው ሕግን ማክበር ያለበት መሆኑ አያጠያይቅም። የሚያጠያይቀው ሁሉንም ሰው የሕግ አስከባሪነት ሚና እንዲያከናውን የመጠበቁ ነገር ነው።

ይህን አወዛጋቢ አንቀጽ ጨረፍ አድርገን ካየን በኋላ እስኪ ደግሞ አዲሱ አዋጅ ሥራ በሚያቆሙ ሠራተኞች የሚለውን እንመልከት። አዋጁ የሥራ ማቆም እርምጃ ትርጉምና አፈጻጸምን የሚመለከት አንድ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ይዞ ወጥቷል። ከዚሁ ምዕራፍ ውስጥ መሪ የሆነው አንቀጽ፣

1. ሠራተኞች በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሥራ ማቆም እርምጃ የመውሰድ መብት አላቸው።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 136 (2) ለተመለከቱት ድርጅቶች፣ ሠራተኞችና አሠሪዎች ተፈጻሚ አይሆኑም።[31]

የሚሉ ሀሳቦችን የያዘ ነው። ይህን አንቀጽ ገባ ብሎ የሚመረምር ሁሉ ሦስት ቁልፍ የሆኑ ቁም ነገሮችን ይጨብጣል። እነዚህም የሥራ ማቆም መብት ያላቸውና የሌላቸው ሠራተኞች መኖራቸው፣ ሥራ የማቆም መብት ያላቸውም ቢሆኑ መከተል ያለባቸው ሥርዓቶች እንዳሉ፣ የእርምጃው ምክንያት ምን መሆን እንዳለበት በሕግ መገለጹ ናቸው። በየፈርጃቸው እንመለከታቸዋለን።

4.1 የሥራ ማቆም መብት የሌላቸው ሠራተኞች

ሁሉም ዓይነት ሠራተኞች የሥራ ማቆም እርምጃን የመጠየቅ፣ የማቀናበርና የማካሄድ መብት የላቸውም። ከእነዚህም በመጀመርያ የምናገኘው በዚህ አዋጅ የማይሸፈኑ ሠራተኞችን ነው። የመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የጦርና የፖሊስ ኃይል አባላት፣ በሥራ አመራር ላይ የሚገኙ ሠራተኞች በዋንኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከእነዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የውጭ ሀገር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች እንደዚሁም በሃይማኖትና በበጎ አድራጎት ተቋማት ውስጥ ያሉ ሠራተኞችን ሁኔታ ለመወሰን ይችል ዘንድ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣን ይሰጣል።[32]

በመንግሥት የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞችና የጦርና የፖሊስ ኃይል አባላትን ጉዳይ የሚሸፍኑ ሕጎች እንዳሉ የሚታወቅ ነው። ለምሳሌም ያህል የመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞች የሚተዳደሩት በሥራ ላይ ባለው የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደርያ ደንብ ነው። ይህም ደንብ በማናቸውም መልክ ቢሆን የመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞች በተቀናጀ የሥራ ማቆም እርምጃ ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚከለክል ነው።[33]

የእኛን ሀገር ጨምሮ ብዙ ሀገሮች በመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞች የሚወሰዱ የሥራ ማቆም እርምጃዎችን በአደገኛ አህማምያነት የሚመለከቱ ስለሆነ፣ እዚህ ላይ የዓለም የሥራ ድርጅት በቁጥር 151 ያወጣውን የቃል ኪዳን ስምምነትና አያይዞም በቁጥር 159 ያስተላለፈውን የድጋፍ አስተያየት መመልከቱ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ነው። የተጠቀሰው የቃል ኪዳን ስምምነት የመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞች በማኅበር ለመደራጀት ያላቸውን መብት የሚያውቅና የሥራ ሁኔታዎቻቸውም እንዲጠበቁ ፈራሚ መንግሥታትን የሚጠይቅ ነው። ስምምነቱ በመስኩ ያለው የሠራተ

ዎች ተሳትፎና ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እያደገና እየሰፋ መምጣቱን በማመልከት ፍሬያማ የሆነ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚኖርበትን መንገድ የሚጠቁም ነው። በኑሮ ልማድ ዕውቀት ፖሊሲ አውጭ እየተባሉ ከሚታወቁት ከከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የሥራ አመራር ሃላፊዎች፣ የሥራቸው ባሕርይ ጥብቅ የሆነ ምስጢራዊ ተግባር እንዲያከናውኑ ከሚጠብቅባቸው ሠራተኞች በስተቀር ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች በዚህ የቃል ኪዳን ስምምነት የሚሸፈኑ ናቸው።[34] በሌሎች የሥራ መስኮች ለተሠማሩ ሠራተኞች ቀደም ብለው በዓለም የሥራ ድርጅት በወጡት የቃል ኪዳን ስምምነቶች የተሰጡት ሠራተኞችን ፀረ ማኅበር ከሆኑ አድሎአዊ አሠራሮች የመጠበቅ መብቶች በዚህ ስምምነት ለመንግሥት የአስተዳደር ሠራተኞችም ተፈጻሚ መሆን እንዳለባቸው ተመልክቷል። በማኅበር የመደራጀትና በሕብረት የመደራደር መብታቸው ታውቋል። በሌላ የሥራ ዘርፍ ለተሰማሩ ሠራተኞችና ለማኅበሮቻቸው የተሰጠው ማናቸውም ጥበቃ ሁሉ ለመንግሥት የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሠራተኞችና ለማኅበሮቻቸውም ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል።

የሥራ ክርክርን በመወሰን ረገድ መፈጸም ያለበትን ሥርዓት አስመልክቶም፣

> የሥራ ውሎችንና ሁኔታዎችን አወሳሰን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በየሀገሩ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ በተከራካሪ ወገኖች መሀል በሚደረጉ ድርድሮች፣ ይህ የማይቻል ሲሆን ደግሞ የግራ ቀኙን አመኔታ ባገኙ ነፃና ገለልተኛ በሆነ አስማሚ ወይም ገላጋይ እየታየ መወሰን ይገባዋል።[35]

በማለት የቃል ኪዳን ስምምነቱ ይደነግጋል።

ሀገራችን እስከዛሬ ይህን ስምምነት ተቀብላ ማጽደቅ አለማጽደቋ በዚህ ጽሑፍ በኩል አይታወቅም። የመንግሥት የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ቀደም ሲል ሲደረግ እንደነበረው ሁሉ በአሁኑም አዋጅ አይሸፈኑም ተብለው ከዚህ መብት መገለላቸው ግን ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ነገር ነው፤

የሥራ ማቆም መብት

የሥራ ማቆም መብት የሌላቸውና በሁለተኛው ምድብ የተፈረጁት ሠራተኞች ደግሞ እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎቶች ናቸው ተብለው በአዋጁ በተገለጹት የሥራ ዘርፎች ውስጥ የተሠማሩት ናቸው። አዋጁ እነዚህን የሥራ ተቋሞች "ለሕዝብ የማያቋርጥ አገልግሎት የሚሰጡ" በሚል ሀረግ ይተረጉማቸውና የሚከተሉትን እንደሚጨምሩ ያመለክታል።

ሀ) የአየር መንገድ እና የምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎቶች፣

ለ) የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣

ሐ) የውሃ አገልግሎት የሚሰጡና የከተማ ጽዳት የሚጠብቁ ድርጅቶች፣

መ) በከተማ ውስጥና ከከተማ ውጭ የአውቶብስ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችና ነዳጅ ማደያዎች፣

ሠ) ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የመድሃኒት ማከፋፈያ ድርጅቶችና የመድኃኒት መሸጫ ቤቶች፣

ረ) ባንኮች፣

ሰ) የእሳት አደጋ አገልግሎት፣ እና

ሸ) የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች፣[36]

ሕጉ እጅግ አስፈላጊ ናቸው እያለ በሚጠራቸው በእነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተሠማሩት ሠራተኞች በሀገሪቱ ውስጥ በሠራተኛ ማኅበር ከታቀፉት ሠራተኞች አንጻር ውስጥ ጠቀም ያለውን የሚይዙ ናቸው። ከፍ ያለ ሥልጠናና የዳበረ የፖለቲካ ንቃት ያላቸው ሠራተኞች በእነዚህ ዘርፎች እንደሚገኙም የሚጠበቅ ነገር ነው። ታድያ እነዚህ ሠራተኞች የተከለከሉትን ይህን ቁልፍ መብት በሌላ መንገድ ለማካካስ ሕጉ የሚሰጣቸው ምርጫ ምንድን ነው? ለጥያቄው ምላሽ ፍለጋ ፊታችንን አሁንም ወደ አዋጁ አንቀጾች ስንመልስ የምናገኘው አመርቂ ውጤት የለም።

ሠራተኞችን የሥራ ማቆም መብት ለመከልከል የሚቀርበው ምክንያትም ቢሆን አወዛጋቢ ነው። በእነዚህ ዘርፎች የተሠማሩት ሠራተኞች የሚያበረክቱት አገልግሎት ለሕብረተሰቡ እጅግ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ሥራ በማቆም እርምጃ የሚከተለው ውጤት የማይመለስ ጉዳት ያስከትላልና መብቱን አለመስጠቱ ተገቢ ነው

የሚሉ ወገኖች አሉ። ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩም የሥራ ማቆም እርምጃ በመብትነቱ ሊታወቅ የሚገባው ቢሆንም እነዚህ ሠራተኞች ሥራ ቢያቆሙ የሚመጣው ጣጣ ከእነርሱም አልፎ ጠቅላላውን ሕብረተሰብ ጉዳት ላይ የሚጥል ነው እያሉ ይከራከራሉ።

ይህን አባባል የማይቀበሉት ወገኖች ደግሞ ሥራን የማቆም መብት የቅንጦት ሳይሆን የሠራተኞች ቁልፍ የመብት ማስከበርያ መሣሪያ ስለሆነ ከቶውኑም ችላ ሊባል አይገባውም ባዮች ናቸው። ከሁሉም በፊት፣ ይላሉ እነዚህ ወገኖች፣ ክልክላው በበርካታ የዓለም የሥራ ድርጅት የቃል ኪዳን ስምምነቶችና የድጋፍ አስተያየቶች፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁለንተናዊ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ በዚሁ ድርጅት በጸደቀውና ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ለብዓዊ መብቶችን በሚያከበረው ዓለም አቀፍ የቃል ኪዳን ስምምነት፣ እንደዚሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎች የተወቀውን የመደራጀት ነፃነት መርሆ የሚጻረር ነው። አባባላቸውን ሲያጠናክሩም የሥራ ባሕርያቸውን ብቻ ምክንያት በማድረግ በሠራተኞች መሀል ልዩነት ማድረግ በሕግ ፊት በእኩልነት የመታየትን አስተሳሰብ የማይከተል ነው ይላሉ።

ከዚሁ ጋር አብረው መታየት ያለባቸው ተዛማጅ ጉዳዮች እጅግ አስፈላጊ ናቸው በሚባሉትና በሌሎች አገልግሎቶች መሀል ያለውን ልዩነት በማረጋገጥ ረገድ የሚያጋጥመው ችግር ነው። አዋጁ እነዚህን አገልግሎቶች ለሕዝብ የማያቋርጥ አገልግሎት የሚሰጡ ብሎ ይተረጉማቸዋል። በግልጽ ከተመለከቱት የሥራ ዘርፎች በተጨማሪ የአዋጁ አንቀጽ አነጋገር ሌሎች አገልግሎቶችም አስፈላጊ ሊባሉ በእንደሚችሉ ፍንጭ ይሰጣል። ታዲያ ይህን የአንቀጹን አተረጓጎም እንዴት ጠበብ ማድረግ ይቻላል? ለመሆኑ አንድን ዓይነት አገልግሎት ከሌላው ዓይነት ለይቶ ሕዝባዊ አገልግሎት ወይንም እጅግ ጠቃሚ አገልግሎት የሚያሰኘው ምንድን ነው? በከተማና ከከተማ ውጭ ያሉ የአውቶቡስ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሠራተኞች የሥራ ማቆም እርምጃ መውሰድ እንደማይችሉ ከፍ ብለን አይተናል። የከባድ የጭነት ማመላለሸ

ካሚዮን ሹፌሮች፣ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የሚገኙት፣ ሥራ ለማቆም ቢወስኑ ምን ይደረጋሉ? እነዚህ ሰዎች የሚሰጡት አገልግሎት የአውቶቡሶች ሹፌሮች የሚሰጡትን ያህል እጅግ አስፈላጊ አይደለም ሊባል ነውን? አንድንድ ሰዎች ይህንን ጥያቄ በአዎንታ ሌሎች ደግሞ በአሉታ ሊመልሱት ይችሉ ይሆናል። ሁለቱም የሚሰጡት ምላሽ እንደተነሱበት አቋም ወይም እንደየግል አመለካከታቸው የተለያየ ነው የሚሆነው። ክርክር በሚነሳበት ጊዜ አንዱን ምላሽ መቀበልና ሌላውን መጣል ለሚቋቋመው የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ አባላትና በፍትሕ ሥራ ለሚሰማሩ ዳኞች ፈታኝ እንደሚሆን አያጠያይቅም።

ያም ሆነ ይህ "እጅግ አስፈላጊ ናቸው" የሚባሉትን የሥራ ዘርፎች ያለቅጥ በማብዛት በረቂቅ ሕጋዊ ቡራኬ ሽፋን የሥራ ማቆም መብትን ዋና ዋና ናቸው ተብለው በሚገመቱ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ አውታሮች ማሸመድመድ አይገባም። መብቱ ለአጠቃላዩ የሠራተኞች ድርጅታዊ ነፃነት ቁልፍ ጉዳይ ስለሆነ ፍትሕንና ዲሞክራሲን እራምዳለሁ የሚል ማንኛውም ሥርዓት ሊያከብረው ይገባል። ይህ ሲሆን ነው ቆሚለታለሁ ለሚለው ዓላማ ያለውን ጽናት የሚያስመክረው።

4.2 የሥራ ማቆም መብት አፈጻጸም ሥርዓትና ይዘቱ፣

በአዋጁ የሥራ ማቆም መብት ያላቸው ሠራተኞችም ቢሆኑ እርምጃውን ከመውሰዳቸው በፊት በሕጉ በዝርዝር የተመለከቱትን የሥነ ሥርዓት ደንቦች እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል። ወደ እርምጃው ከማምራታቸው በፊት ምክንያቶቻቸውን በመግለጽ ሠራተኞቹ በማኅበራቸው አማካይነት ለአሠሪያቸው የቅድምያ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የሥራ ክርክሩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣ እርምጃው አብዛኛው የማኅበሩ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ባያንስ በሁለት ሦስተኛው ድምፅ መደገፉን ማሳየት፣

የሥራ ተቋሙ የደህንነት መመርያዎችና የአደጋ መከላከያ ዘዴዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ፥ ይጠበቅባቸዋል።[37]

ለአሠሪው ብቻ በትንሹ የአሥር ቀን የቅድሚያ ማስጠንቀቅያ መስጠት በቂ አይደለም። ይህንኑ ማስጠንቀቅያ በአካባቢው ለሚገኘው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ወይም አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤትም መስጠት ያስፈልጋል። ለእነዚህ ለኋለኞቹ መሥሪያ ቤቶች ይህን ማስጠንቀቅያ መስጠት ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ግልፅ የሚመስለው ምክንያት የፀጥታ ጥያቄ ነው። ሌሎች ድግሞ ፖሊሲነክ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የሠራተኞች ማኅበራትን እንቅስቃሴ ከመንግሥት በኩል ሆኖ የሚከታተል አካል በመሆኑ ነው። እስኪ ሌላ ቢኖር እርስዎም ይጨምሩበት!

ከማስጠንቀቅያ ቀጥሎ የሚመጣው ውዝግቡን በስምምነት የመጨረሱ አስፈላጊነት ነው። የሠራተኞች ማኅበራት በዚህ ረገድ የሚነሱ ክርክሮችን ሁሉ በተቻለ መጠን በስምምነት እንዲያልቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በአዋጁ ትርጓሜ ማስማማት ማለት፥

> ...የሥራ ክርክር ያለባቸው ወገኖች በአንድነት በመረጡት ሰው ወይም ሰዎች፥ ወይም በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት በሚኒስቴሩ በሚመደብ አስማሚ ተከራካሪ ወገኖች በፈቃዳቸው በራሳቸው ጥረት ስምምነት ላይ ለመድረስ በማይችሉበት ጉዳይ ባለጉዳዮችን አቀራርቦ የጉዳዩን ፍጻሜ ለማስገኘት የሚደረግ ጥረት ነው።[38]

አስማሚው ዘንድ የሚቀርቡ ጉዳዮች ሠራተኞችን በወል የሚመለከቱ እንደ ደመወዝ፥ የሥራ ሁኔታዎች፥ የኅብረት ድርድር፥ ወዘተ፥ ያሉት ናቸው። እነዚህም ጉዳዮች ሠራተኞችን በጥቅልና የሥራ ተቋሙንም ሕልውና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይነካካሉ። አስማሚው የዚህ ዓይነት ጉዳዮች ሊቀርቡለት በሠላሳ ቀናት ውስጥ ክርክሩን

ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ጥረት ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ውጤት ለማስገኘት ካልቻለ ምክንያቱን በዝርዝር ለሚኒስትሩ ገልጾ ከጉዳዩ ውጭ ይሆናል።[39]

ክርክሩ አስማሚው ዘንድ ቀርቦ አመርቂ ውጤት ካልተገኘ፣ ተከራካሪዎቹም ጉዳዩን ለአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ ካላቀረቡት እንደዚሁም የቅድሚያ ማስጠንቀቅያው ከተሰጠ የሥራ ማቆም እርምጃው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ይቀጥላል ብሎ መገመት ይቻላል።[40]

ዳሩ ግን ጉዳዩን ገፋ ብለን ስናየው ነገሩ በዚሁ አያበቃም። ተከራካሪዎች ጉዳዩን ለቦርዱ የማቅረብ መብት ስላላቸው አንዱ ወገን ወደዚያ ከወሰደው እርምጃው ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን እንዲያስችለው የተፈቀደውን ሰላሳ ቀን መጠበቅ አለበት ማለት ነው። ክርክሩ በምን ያህል ጊዜ ከአስማማው ወደ ቦርዱ መቅረብ እንዳለበት አዋጁ አይገልጽም። ቢሆንም የችግሩ አስቸኳይነት አጣዳፊ እርምጃን ይጠይቃል። አጣዳፊ እርምጃ ማለትም ሚዛናዊ በሆነ መለኪያ በሚጠቀም ሰው አስተያየት የሚወሰን ነው።

በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ከፈለገ የቦርዱ ውሳኔ በጽሑፍ ከተነበበት ወይም ለተከራካሪዎቹ ወገኖች ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው። የይግባኝ ቅሬታው ነጥብ ቦርዱ በሕግ ትርጉም በሠጠውና የይግባኝ ባዩን መብት ያለአግባብ አጣቧል በተባሉ ስህተቶች ብቻ መወሰን አለበት።[41] የሕግ ትርጉም ስህተት ሲባል እንዴት ዓይነቱ እንደሆነና ከፍሬ ነገር ግንዛቤ ስህተት በምን እንደሚለይ የመወሰኑ ተግባር ጉዳዩን ለሚመለከቱት ለማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች የተተወ ነው። ያም ሆኖ ይህ አንድ ጊዜ ይግባኙ ለዚህ ፍርድ ቤት ከቀረበ የሠራተኛ ማኅበሩ የሥራ ማቆም እርምጃውን ከመቀጠሉ በፊት እንደገና ሰላሳ ቀን መጠበቅ አለበት።

ይግባኙ የሚቀርብለት ማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በሁለት መንገድ ለመጨረስ ሥልጣን አለው። ቀላሉ መንገድ የቦርዱን ውሳኔ ማጽናት ነው። ይህ ሲሆን ማኅበሩ እንደ ቦርዱ ውሳኔ የሥራ ማቆም እርምጃውን ሊቀጥል ወይም ሊያቆም ይችላል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቦርዱ የተረሰውን ጉዳይ በሕግ አንጻር በአግባቡ አልተመለከተውም፥ ይህም የነገሩን አካሄድ ተገቢ ያልሆነ አቅጣጫ ያስይዘዋል የሚል አቋም ላይ ከደረሰ፥

> ... የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ከዝርዝር ወይም ከአጠቃላይ መምርያ ጋር ስለሕግ ጉዳይ ሊፈጽመው የሚገባውን ትእዛዝ በመስጠት በዚሁ ትእዛዝ መሠረት እንዲሠራ ውሳኔውን ወደ ቦርዱ መመለስ አለበት። ስለሆነም ፍርድ ቤቱ የቦርዱን ውሳኔ ለመሻር ወይም ለማሻሻል አይችልም።[42]

ይህን ንዑስ አንቀጽ ገባ ብሎ የሚመረምር ሰው ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ሊያነሳ ይችላል። አንድ የቦርድ ውሳኔ በሕግ ጉዳይ ስህተት አለበት፥ ይህም ስሕተት ውሳኔውን ያዛባ ነው የሚባለው በምን አኳኋን ነው? ፍርድ ቤቱ የቦርዱን ውሳኔ ለመሻር ወይም ለማሻሻል ካልቻለ በምን አኳኋን ነው ጉዳዩን ወደ ቦርዱ መልሶ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያዝዘው? ጉዳዩን ወደቦርድ ከዝርዝር ወይም ከአጠቃላይ መመርያ ጋር መልሶ መላክ ውሳኔውን ከማሻሻል ወይም ከመለወጥ ውጭ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ጉዳዩ ከተመለሰ በኋላ ቦርዱ አሁንም የፊተኛው ውሳኔዬ ትክክል ነው ብሎ በዝያው አቋሙ ቢጸና ውጤቱ ምን ሊሆን ነው?

እነዚህን አወዛጋቢ ምላሾች ሊያስከትሉ የሚችሉ ጥያቄዎችን ከነሳን በኋላ ማኅበራት ሕጋዊ ነው የሚባል የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ማለፍ ወደሚገባቸው መሰናክሎች ፊታችንን ስንመልስ ጉዳዩ ከግራ ቀኙ የጋራ ድርድር አንስቶ በአስማሚው የሚደረግ የማግባባት ጥረትን፥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚካሄድ ሙግትንና በማዕከላዊ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሚታይ የይግባኝ ክርክርን ሁሉ የሚያልፍ

በች ሁኔታ እንዳለ እንገነዘባለን። ይህም እስኪሆን ከእርምጃው በፊት ቢያንስ ቢያንስ አንድ መቶ ሰላሳ ቀናት ያልፋሉ። ይህም ለአሠሪው የሚሠጠውን የአሥር ቀን የቅድምያ ማስጠንቀቅያ፣ ለአስማሚው፣ ለቦርዱ እና ለማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለእያንዳንዳቸው የሥራ ማከናወኛ የተፈቀዱትን ሰላሳ ቀናት እንደዚሁም ከቦርዱ ወደ ማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለሚል ወገን የተፈቀደውን የሰላሳ ቀን የይግባኝ ማቅረብያ ጊዜ የሚያካትት ነው። እንግዲህ በዚህ መሀል የሚመጣውን የሚያውቀው እግዚአብሄር ብቻ ነው።

ሌሎቹን የሥነ ሥርዓት መለኪያዎች ስንቃኝ ደግሞ እርምጃው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሠራተኛ ማኅበራት አባላት ውስጥ ሕግ በጠየቀው የሠራተኞች ቁጥር መደገፍ ያለበት መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም። የሚያከራክረው የድርጅቱ የደኅንነት መመርያዎችና የአደጋ መከላከያ ዘዴዎች በቅድሚያ መጠበቅን ማረጋገጥ ያስፈልጋል የሚለው ኃይለ ቃል ነው። አንድ ሠራተኛ ይህን እንዲያከብር የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? የሥራ ማቆም እርምጃ ሠራተኞች በአንድነት በአሠሪው ላይ የሚወስዱት የመብት ማስከበርያ አንዱ አማራጭ አይደለምን? እነዚህ መመርያዎችና ዘዴዎች ይከበሩ መባሉ ለምንድነው? ደንቦችን ማክበርና አስማክበር ከሥራ ማቆም እርምጃ ጋር የሚያያዝ አይደለም። በአሠሪው ወይም በሠራተኛው የግል ሃላፊነትና ጥፋት ላይ የተመሠረተ የፍትሐ ብሄር ተጠያቂነት፣ አልፎ አልፎም የወንጀል ቅጣትን የሚያስከትል ተግባር እንጂ።

የሥራ ማቆም እርምጃ መነሻ ምክንያቶች እንዴት ያሉት ናቸው የሚለውን ጥያቄ ከአዋጁ ጋር ስናገናዝብ ማናቸውም የዚህ ዓይነቱ እርምጃ የእርምጃው ተሳታፊ የሚሆኑትን ሠራተኞች ጥቅም የማስከበር ዓላማ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ይሁንና "ጥቅም ማስከበር" የሚለው ሐረግ በራሱ አነጋጋሪ ነው። የአዋጁን አንቀጾች እርስ በርሳቸው እያዛመድን በሁለተናዊ መልክ ስንመረምር ሕግ አውጭው ለእርምጃው መነሻ

የሚሆኑት የክርክር አይነቶች የወል ባህርይ ያላቸው እንዲሆኑ መፈለጉን እንረዳለን። በአዋጁ ውስጥ ግን የወልና የግል የሥራ ክርክሮች ምን እንደሆኑ ተለይተው አልተተረጎሙም። ይሁንና አዋጁ አልፎ አልፎ ሁለቱንም የክርክር ዓይነቶች ጠቅስ ጠቀስ ያደርጋል። ለምሳሌም ያህል በአንቀጽ 138 (1) እና 142(1) ያለውን ይመለከቷል። የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን በሚመለከቱበት ጊዜ ቀደም ሲል የተሰጡ ፍርዶችን ለመከተል ስለማይገደዱ የሁለቱን የክርክር ዓይነቶች በውል ለይቶ አለማስቀመጥ በዚህ ረገድ የሚነሱ ውዝግቦችን በመፍታት ረገድ እስካሁን ያለውን ችግር የሚያባብስ መስሎ ይታያል።

አሁን በተሻረው በአዋጅ ቁጥር 64/1968 ለሁለቱ የክርክር ዓይነቶች ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለማዋሃድ የተደረገ በሚመስል ጥረት አዲሱ አዋጅ "የሥራ ክርክር" የሚለውን ሐረግ ጠቅለል አድርጎ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል።

> ሕግን፣ የኅብረት ስምምነትን፣ የሥራ ደንብን፣ የሥራ ውልን ወይም ሲሠራበት የቆየ ልምድን መሠረት በማድረግ እንዲሁም በሕብረት ስምምነት ድርድር ወይም ከሕብረት ስምምነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚመለከት በሠራተኛና አሠሪ ወይም በሠራተኞች ማኅበርና በአሠሪዎች መካከል የሚነሳ ክርክር ነው።[43]

ትኩረት የሚሻውና ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚዛመደው ሌላው ጉዳይ ደግሞ ለመሆኑ ሠራተኞች አጠቃላይ ወይም ድጋፍ ሰጭ የሥራ ማቆም እርምጃዎችን ለማካሄድ ቢፈልጉ በሕግ የሚኖረው ውጤት ምንድነው የሚለው ጥያቄ ነው። አዋጁ የሚናገረው በአንድ የሥራ ተቋም ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በማኅበራቸው አማካይነት ስለሚያካሂዱት ኢኮኖሚያዊ የሥራ ማቆም እርምጃ ብቻ ነው። ሠራተኞቹ ለእርምጃው ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ያላቸውን ቀራቢ ጥቅም እንዲያሳዩ ሕጉ ይጠብቅባቸዋል። ከዚህ የምንረዳው በአዲሱ አዋጅም ቢሆን ሠራተኞች ለሌሎች መሰሎቻቸው ጥያቄዎች የትግል አንድነት ለመግለጽ ብለው የሚጠሩዋቸው ጠቅላላ ወይም ድጋፍ ሰጭ የሥራ

ማቆም እርምጃ የማካሄድ መብት እንደሌላቸው ነው። ምንም እንኳ ፌዴሬሽኖችንና ኮንፌዴሬሽኖችን ማቋቋም ቢችሉም እነዚህ አካላት የሥራ ማቆም ጥሪ ማድረግ አይችሉም። በአስማሚ፥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ወይም በፍርድ ቤቶች ዘንድ በሚደረጉ የሥራ ክርክሮች ውስጥም የመሳተፍ መብት የላቸውም። እንደዚህ ከሆነ ታድያ እነዚህን አካላት የማቋቋሙ ፋይዳ ምንድነው ብሎ መጠየቅ ይቻላል። ምላሹ አይገኝም እንጂ።[44]

4.3 በሂደቱ የአሠሪው ሚና፥

ይህን በመሰለ የሥራ ክርክር አንዱ መጤን ያለበት ነገር አሠሪው የሚኖረው ሚና ነው። በመሠረቱ የቅጥር ግንኙነት የሚመነጨው በአሠሪውና በሠራተኛው መሀል ከሚደረግ ውል ነው። የዚህ ዓይነት ስምምነት ሠራተኛው ለአሠሪው፥

> ... አንድ ግዴታነት ያለው ወይም የአእምሮ ሥራ በተወሰነ ወይም ባልተወሰነ ጊዜ ውስጥ አሠሪው ሊከፍለው በተስማማበት አንድ ደመወዝ በርሱ አገልግሎትና በርሱ መሪነት ሥራውን ለማከናወን ግዴታ የገባበት ውል ነው።[45]

የቅጥር ውል ያለው ለየት ያለ ባሕርይ፥ የውሉ ተዋዋይ የሚመለከተው የሰው ልጅን አገልግሎት መሆኑ፥ አሠሪው በግንኙነቱ ያለው ኢኮኖሚያዊና የሥራ አመራር የበላይነት፥ የተለየ ትኩረት የሚያሻቸው ነገሮች ቢሆኑም፥ ዞሮ ዞሮ ውል ነውና የውሉ ወገኖች በጉዳዩ ላይ በሀሳብ መግባባት እንደሚገኝ ውል ሁሉ በሥራ ውልም ወሳኝ ነው።

አስቸጋሪነታቸውን ሳንዘነጋ፥ ሕጉ የሚጠይቃቸው የሥነ ሥርዓት ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብንልና ጥያቄውን ያቀረቡትም ሠራተኞች በሕግ ይህ መብት ከተሰጣቸው ውስጥ ናቸው ብንል፥ የሥራ ማቆም እርምጃውም ቢቀጥል፥ አሠሪው እስከመጨረሻው

የሠራተኞቹን ጥያቄ ላለመቀበል ከቆረጠ ውጤቱ ምን ይሆናል? ነገሩን ከዚህም በላይ አባብሶ በሕግና በሕብረት ስምምነት ያሉትን መብቶች በመጠቀም የሥራ ውሉን እቋርጣለሁ ቢልስ?

የባለንብረትነት መብት በማይገሠሥበት፣ በሕግና በሕገ መንግሥትም ጭምር በቂ ጥበቃ በሚያገኝበት በነፃ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ባለሀብቱ በሕግ ካልሆነ በቀር ሊቀነስ ወይም ሊከፋፈል የማይችል ከሁሉ የሰፋ መብት በንብረቱ ላይ ይኖረዋል።[46] ታድያ ይህ መብት ያለው አሠሪ ለሠራተኞቹ ጥያቄ ካልተንበረከከ እርምጃው እስከመቼ ሊቆይ ይችላል? ሠራተኞቹ በዚህ ጊዜ የሚኖሮዋቸው ሌሎች አማራጮች ምንድናቸው? የዚህ ዓይነት ሁኔታዎች እምብዛም የሚያጋጥሙ ባይሆኑም ከቶውኑም ሊከሰቱ አይችሉም ማለትም አዳጋች ነው። ሕጉ ይህን ችግር ያስተዋለው አይመስልም።

4.4 የቅጣት ድንጋጌዎች

የሥራ ክርክሩ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ወይም ለማዕከላዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ከማግኘቱ በፊትና ለዚህ የተመደበው የሰላሳ ቀን ጊዜ ሳይሞላ የሥራ ማቆም እርምጃን ማቀነባበርና ማካሄድ በአዋጁ አነጋገር ሕገ ወጥ ድርጊት ነው። እንደዚሁም ቦርዱ የሥራ ክርክሩን በተመለከተ የሚሰጠውን ውሳኔ ባለመቀበል የሚደረግ ሥራ ማቆም ወይም ውሳኔውንና ትእዛዙን ያለበቂ ምክንያት ሳይፈጽሙ መዘግየት ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ነው።[47] ይህን አለማክበር በወንጀልም ጭምር የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣቱም መጠን አጥፊው ማኅበር ሲሆን ብር 1,200 ግለሰብ ሠራተኛ ከሆነ ብር 300 ሊደርስ ይችላል ተብሎ ተመልክቷል። ይሁንና ድርጊቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚሸፈን ሲሆንና በዚህ ሕግ ያለው ቅጣት ከፍተኛ ከሆነ ጥፋተኛው የሚቀጣው ከፍተኛ ቅጣት ባለው አንቀጽ መሠረት ነው።[48]

5. የማጠቃለያ አስተያየቶች

ምንም ዓይነት ምክንያት ቢኖረው ሥራን ላቆም የሚል ሁሉ አደፍራሽና ተቃዋሚ ነው ብሎ ማሰብ ከዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ጋር አብሮ የማይሄድ ግንዛቤ መጨበጥ ነው። እርምጃው የተወሳሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚያመጡት ውጤት በመሆኑ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወገኖችም ሆነ በመንግሥት በኩል በእርጋታና በማስተዋል መመርመር ያለበት ነው። የሥራ ማቆም እርምጃ ከመሠረቱ የማይፈለግ ክስተት ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን አይቀሬ ነው። ማኅበራዊ መስተጋብር እስካለ ድረስ ቅሬታዎች ይፈጠራሉ። የሥርዓቱ መዘውር በትክክለኛው ሰቅ ላይ የሚሽከረከረው ይህን ችግር በቅጡ ተረድቶ ሚዛናዊ መፍትሄ ሲፈለግለት ነው። በአለመግባባትና በፍጥጫ መሀል ጉልህ ልዩነት እንዳለ መገንዘቡ ብልህነት ነው። አለመግባባት ማኅበራዊ ግንኙነት ካለ ተያይዞ የሚመጣና የማይቀር ነገር ሲሆን፣ ፍጥጫን ግን ከእኔም፣ ከአንተም፣ ከእንችም፣ ይቅር በመባባልና ፍትሐዊ ፖሊሲን በመንደፍ ማስቀረት ይቻላል። እኔ እንደማስበው ማሰብ፣ እኔ እንደምመኘው መመኘት፣ እኔ የማደርገውን ማድረግ አለብህ ብሎ ልዩነት ማፈን ችግሩ የከፋ ክበሮውን እየደለቀ ውሎ አድሮ እንዲመለስ በቀጠሮ ማቆየት ነው።

እስከዛሬ ያለው የዚህች ሀገር ታሪክ የሚያሳየን ሠራተኞች ከአሠሪዎቻቸውና ከመንግሥት ጋር ያላቸው ግንኙነት ማስፍያ ነው በሚባልበት ወቅት እንኳ ከመሽቀጥቀጥ ያልዘለለ መሆኑን ነው። በዚህ ጽሁፍ ሠራተኞች ለመደራጀት ያላቸውን ነፃነትና ሥራ ለመቆም የሚኖራቸውን መብት በኢትዮጵያ ከነበሩት ሕጎችና አሁንም ካለው አዋጅ ጋር በማነፃፀር ለመመልከት ሙከራ ተደርጓል። እነዚህ ሕግጋት ያበረከቱትን ገንቢ አስተዋፅኦ ሳንዘነጋ፣ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ በዓለም የሥራ ድርጅት የወጡት በርካታ የቃል ኪዳን ስምምነቶችና የድጋፍ አስተያየቶች፣ እንደዚሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎችና

ስምምነቶች፣ ከሚያስቀምጧቸው መለኪያዎች ጋር ሲነፃፀሩ ገና ብዙ መንገድ እንዳለብን እንረዳለን።

በግለሰብ ደረጃም ይሁን በቡድን የሌሎችን መብት አውቀን ተቀብለናል ስንል አባባላችን ከአንጀታችን መሆኑ የሚረጋገጠው ተግባራዊ አፈጻጸማቸውን የሚያደናቅፉ የተለያዩ መሰናክሎችን ከሕይወታችን ያልደቀንን እንደሆንነው። በመብቶች ገቢራዊነት ላይ የሚጣል ማዕቀብ የራሱን የመብቱን መሠረታዊ መንፈስ ያላዘነጋና የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ደህንነት ከመጠበቅ አንጻር ብቻ የታየ ሊሆን ይገባዋል። ሲፈልግ የማይተገበር መብት ልክ እንደተጻፈበት ወረቀት ግዑዝ ነውና።

በዴሞክራሲ ጎዳና መራመድና ነፃ የገበያ ሥርዓትን ማስፈን የወቅቱ አበይት ተግባሮች እንደመሆናቸው መጠን ከፍ ብለን ያየነውን ትላልቅ የኅብረተሰባችን መፍትሔዎች በብሩህ ልቡና ያስተውሉታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ማስታወሻዎች

1. ኢ.ኤ.አ በሚያዝያ 10 ቀን 1944 በፊላዴልፊያ ከጸደቀው የዓለም የሥራ ድርጅት መሪ ሕገ ማኅበር መቅድም የተወሰደ፣ /ትርጉም የጸሐፊው/

2. Black's Law Dictionary, 5th ed., 1979, West Publishing Company /ትርጉም የጸሐፊው/

3. የሥራ ማቆም እርምጃ የሚለይበት ሌላው መንገድ እንደ እርምጃው አወሳሰድ ነው። ከነዚህም አጠቃላይ የሥራ ማቆም፣ ድጋፍ ሰጭ የሥራ ማቆም፣ ባሉበት በታ ሥራ ማቆም፣ አፈንጋጭ የሥራ ማቆም የተለመዱት ናቸው። አጠቃላይ የሥራ ማቆም እርምጃ ብዙውን ጊዜ የሚጠራው በሠራተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽኖችና ኮንፌዴሬሽኖች ሲሆን ተሳታፊ የሚሆኑት ሠራተኞች በአንድ በተወሰነ የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሰማሩ፣ በክልል፣ ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ማኅበራት በሚደግፏቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠሩበት ሁኔታም አለ። ዓላማዎቻቸው የአባላቱን ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጥቅም እናስጠብቃለን ከሚሉ አመለካከቶች የመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ባሉበት የሥራ ተቋም ሥራ የሚያቆሙ ሠራተኞች ሥራውን አይወጡም ከሥራ ገበታቸው ግን አይለዩም። አፈንጋጭ የሥራ ማቆም እርምጃዎች የሚባሉት ሠራተኞቹ ያለማኅበራቸው ድጋፍ አንዳንዴም ማኅበሩን በመቃወም የሚያደርጉት ነው። ድጋፍ ሰጭ የሥራ ማቆም እርምጃ በሚደረግበት ጊዜ ሁለት ዓይነት ሠራተኞች ይኖራሉ። የመጀመሪያዎቹ ለአሠሪያቸው ወይም ለሌላ አካል አንዳች ዓይነት ጥያቄ አቅርበው ካልተፈጸመ እንሠራም የሚሉት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ለእነዚህ ሠራተኞች የትግል ድጋፍ ለመስጠት ሥራ የሚያቆሙት ናቸው።

4. በዚህ ረገድ ዋና ዋናዎቹ የዓለም የሥራ ድርጅት ያወጣቸው ሰነዶች፡

ሀ) የማኅበር ነፃነትን ለማረጋገጥና የሠራተኞችን የመደራጀት መብት ለመጠበቅ በቁጥር 87 እ.ኤ.አ በ1948 የወጣው የቃል ኪዳን ስምምነት፡

ለ) የመደራጀትና የመደራደርን መብት በማወቅ በቁጥር 98 እ.ኤ.አ 1949 የወጣው የቃል ኪዳን ስምምነት፡

ሐ) የሠራተኞችን ተወካዮች በተመለከተ በቁጥር 135 እ.ኤ.አ በ1971 የወጣው የቃል ኪዳን ስምምነት፡

መ) የሠራተኞችን ተወካዮች በተመለከተ በቁጥር 143 እ.ኤ.አ በ1971 የወጣው የድጋፍ ሀሳብ፡

5 አዋጅ ቁጥር 210/1956፣ አንቀጽ 2(1)

6. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 12

7. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 19

8. አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የሠራተኞች ማኅበራትና ሌሎች የሲቪል ማኅበራት በተመሳሳይ ሁኔታ በ1952 ዓ.ም በተለይ በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ፣ 19ኛ ዓመት ቁጥር 2 በታወጀው በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጾች ሥር ይታዩ ነበር። የሕጉን አንደኛ መጽሐፍ፣ አንቀጽ 3፣ ምዕራፍ 2 በአጠቃላይና የሕጉን ቁጥር 406 በተለይ ይመለከቷል።

9. አዋጅ ቁጥር 210/1956፣ አንቀጽ 2 (ዘ)

10. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2 (ደ) ን ከአንቀጽ 28 ጋር ያገናዝቧል።

11. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 22

12. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 37 ያገናዝቧል። ሚኒስትሩ አዋጁን ለማስፈጸም በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎች ደንብ ቁጥር 302/1964 በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ አድርጓል።

13. እዚህ ላይ የመንግሥት ባለቤትነት ስንል በሚያበረክቱት አገልግሎት ጠቀሜታና ከአስፈላጊነታቸውም አንጻር እየታዩ በመንግሥት ብቻ የሚካሄዱ የሥራ ዘርፎችን ለማለት ነው።

14. አዋጅ ቁጥር 64/1968፣ አንቀጽ 49፣

15. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 50(4) (5) (7)።

16. የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 174/1972 ይመለከቷል።

17. አዋጅ ቁጥር 64/1968፣ አንቀጽ 52(1)(ለ)

18. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 114 (2)።

19. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 53 (3) (ለ)።

20. Report of the Committee of Experts on the Application of Conventions and Recommendations; International Labour Office Publication, Geneva, 1976, p. 120.

21. ዝኒ ከማሁ፣ /ትርጉም የጸሐፊው/

22. አዋጅ ቁጥር 64/1968፣ አንቀጽ 2(22)

23. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 106።

24. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2(5) እና አንቀጽ 2(12)፣ እነዚህ ሁለት ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው የወልና የግል የሥራ ክርክር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ። የወል የሥራ ክርክር ማለት የሕጎች፣ ደንቦች፣ የሕብረት ስምምነቶች፣ የሥራና የአስተዳደር ደንቦች ትርጉምና በእነዚሁ ውስጥ የተመለከቱ የሥራ ሁኔታዎች ወይም ጥቅሞች ወይም ሲሠሩባቸው የቆዩ ልምዶች ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ ወይም አዲስ ጥቅሞችን ለማግኘት በድርጅት ወይም በሠራተኞች የሚቀርብ አቤቱታን የሚመለከትና እንዲሁም በውደደት ጊዜ የሚነሳ ክርክር ነው። የግል የሥራ ክርክር ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከተው ሠራተኛ በሕግ በደንብ በሥራና የአስተዳደር ደንብ ወይም በሥራ ውል ውስጥ የተመለከተ ሁኔታን የሚሽር ወይም የሚቀንስ ርምጃ ድርጅቱ በመውሰዱ ወይም በድርጅቱ ሲሠራባቸው የቆዩ ልምዶች ሥራ ላይ ባለመዋላቸው በሠራተኛው ጥያቄ የሚቀርብ ማናቸውም ክርክር ነው።

25. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55፣

26. በዓርኒ ማስታወሻ ቁጥር 20 ላይ የተጠቀሰው ሪፖርት ገጽ 121፣

27. ኢሕአዴግ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ተራራማ ሸለቆዎች ተመሥርቶ ያደገና የነበረ፣ ከአሥራ አምስት ዓመታት በላይ ከወሰደ የሽምቅ ውጊያ በኋላ የደርግን መንግሥት የጣለ የፖለቲካ ድርጅት ነው። በአሁኑ ጊዜ አራት ድርጅቶችን ያካተተ ግንባር ሲሆን እነዚህም ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ፣ /ሕወሐት/ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ /ኢሕዴን/ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣ /ኦሕዴድ/ እንደዚሁም ብዙም የማይታወቀው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ /ኢዴመአን/ ናቸው። በሽግግር መንግሥቱ የተወካዮች ምክር ቤት ከተመደቡት 87 መቀመጫዎች ውስጥ 32ቱ፣ የኢሕአዴግ ናቸው። ሌሎቹን 55 መቀመጫዎች ብዛት ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖችና ነፃ አውጭ ንቅናቄዎች ይጋሩዋቸዋል።

28. አዋጅ ቁጥር 42/1985፣ አንቀጽ 113፣

29. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 114፣

30. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 115፣

31. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 157፣

32. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 3፣

33. የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደርያ ደንብ ቁጥር 269/1954፣ አንቀጽ 83፣

34. በመንግሥት የአስተዳደር ሥራ የተሠማሩ ሠራተኞችን የሥራ ሁኔታ በተመለከተ በቁጥር 151 እ.ኤ.አ በ1978 የወጣው የቃል ኪዳን ስምምነት፣ አንቀጽ 2፣

35. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 8፣ /ትርጉም የጸሐፊው/

36. አዋጅ ቁጥር 42/1985፣ አንቀጽ 136(2)፣

37. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 158፣

38. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 136(1)፣

39. ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 142፣

40. በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ተቋቁሞ የነበረው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 64/1968 እንዲፈርስ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል። ሥልጣንና ተግባሩም የወል የሥራ ክርክሮችን ማየት፣ ተከራካሪዎችን ማስማማት አስፈላጊ ሲሆንም ተገቢውን ትእዛዝና ውሳኔ መስጠት ነው።

41. አዋጅ ቁጥር 42/1985፣ አንቀጽ 154፣

42. ዝኒ ከማሁ፣

43. ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 136(3)፥

44. ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 116፥ ከፌዴሬሽኖችና ከኮንፌዴሬሽኖች ተግባር የአባል ማኅበራትን አንድነትና የመረዳዳት መንፈስ ማጠንከር፥ በሥራ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሥራ ሁኔታዎችን ለማሻሻልና ለመወሰን በሚደረጉት ጥረቶች መሳተፍ እንዲሁም አባሎቻቸው በአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ ተሳትፎአቸው እንዲጠናከር ማበረታታት ይገኙበታል። ጥያቄው ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ እነዚህ አካላት እንዴት አድርገው ነው ይህን ተግባር የሚፈጽሙት የሚለው ነው።

45. የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2512፥

46. ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1204፥

47. አዋጅ ቁጥር 42/1985፥ አንቀጽ 160፥

48. ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 185 ከአንቀጽ 183 ጋር ያናዝቧል። እንደዚሁም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 413 ይመለከቷል። ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ፥ 16ኛ ዓመት ቁጥር 1፥

Journal of Ethiopian Law Vol. 16, 1993

AN OVERVIEW OF THE RIGHT TO STRIKE IN ETHIOPIA

By Tilahun Teshome*

> *... Conditions of labour exist involving such injustice, hardship and privations to large numbers of people as to produce unrest so great that the peace and harmony of the world are imperilled .... the failure of any nation to adopt humane conditions of labour is an obstacle in the way of other nations which desire to improve the conditions in their own countries ...*[1]

1. General

In any system of industrial relations where employers and workers are bound by contractual relationships with separate and, at times, conflicting interests, it is natural for the employer to exert his superior economic power and managerial skill to take as much of the gain as possible from the production and service rendering process. It is likewise natural for the workers to wage their own struggle by effective utilization of their organizational strength to obtain a better share of the profit, good working conditions and employment security. Stoppage of work as a collective measure to secure one or a variety of economic or social ends, commonly referred to as strike, is but one aspect of this struggle of workers. It is an act "... by a body of workers for the purpose of coercing their employer to accede to some demand they have made upon him, and which he has refused".[2]

Strike grew out of the wage system in modern capitalism that paved the way for trade unionism and the institution of collective bargaining. It is not a stoppage of work resulting in the termination of the contract of employment, and the workers continue to be attached to their place of work.

The majority of such economic strikes result from controversies over wages. Disputes over improvement of work conditions, occupational safety, decrease in working hours are also expressions of economic strike. Points of controversy between employers and workers over union recognition and discriminatory employment policy

* Assistant Professor of Law, Addis Ababa University, former judge of the Supreme Court of Ethiopia.

resulting in strikes are also included in this category although they sometimes embrace other social and political dimensions.

Political strikes, on the other hand, are not motivated by the immediate economic interests of workers and thus do not spring from contractual relationships with their employers. They are usually called by federations or confederations of trade unions or other pressure groups for political objectives.[3]

As a right, strike is recognized in many countries the world over although it is not uncommon to come across pieces of legislation that require a series of specified efforts towards dispute settlement before conducting the strike. There are, of course, totalitarian regimes which are exceptions to this general trend that view all forms of strike as subversive. But the widely accepted view places recognition of this basic right as an issue of the day.

Modern developments in public international law are also in favour of this trend. That ... everyone has the right to work, to free choice of employment, to just and favourable conditions of work ... to just and favourable remuneration ensuring for himself and his family an existence worthy of human dignity ... is enshrined under Article 23 of the United Nations Universal Declaration of Human Rights. Furthermore the right to strike is explicity recognized under Article 8 of the International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights adopted by the General Assembly of the United Nations.

The International Labour Organization (ILO) too has adopted a number of conventions and recommendations dealing with freedom of association and the right of collective bargaining of workers which states-parties are required to give recognition and provide guarantees for their effective implementation in their respective jurisdictions.[4]

These conventions and recommendations recognize the right of workers to establish and join trade unions of their choice, the right of unions to draw up their constitutions, to elect their representatives and to freely organize their administration. Interferences impeding the exercise of the right to organize resulting in the dissolution or temporary suspension of trade unions, or anti-union discrimination in respect of employment or promotion and dismissal of workers for reasons of participation in union activities are strictly prohibited. Even the law of the land under the auspices of which the unions operate must not be applied to impair these guarantees.

As the main theme of this paper is to treat the controversial notion of the right to strike from the Ethiopian perspective, in the forthcoming discussion an attempt is made to make a brief survey of past and present legislations pertaining to the subject in light of these general considerations.

2. The Labour Relations Proclamation No. 210 of 1963

Ethiopian legislative history shows this Proclamation to be the first of its kind enacted in the area of industrial relations. As expressed in its preamble, its objective was the creation of conducive labour conditions and the settlement of labour disputes by means of collective bargaining. Labour dispute is defined as meaning any point of misunderstanding concerning the terms or tenure of labour conditions; or the eligibility or authority of a person claiming the right to represent either employers or workers in negotiating, arranging, fixing, maintaining or modifying the terms of labour conditions.[5]

A machinery for the settlement of trade disputes known as the Labour Relations Board was set up, with powers to consider, conciliate and arbitrate such disputes; to consider any complaint of unfair labour practice, to prohibit any such practice, to direct any persons, groups or organizations to abstain therefrom; to enforce its decisions and awards by appropriate means; and to recommend to the Minister of Community Development and Social Affairs the dissolution of organizations.[6] An appeal from a decision of the Board on questions of law, not on findings of fact, was allowed to be taken before the then Supreme Imperial Court. Its power was to examine such decision, and if there was any error of law to refer the case to the Board for final action, giving at the same time binding directives on questions of law.[7]

The Proclamation further recognized the rights of associations of employers and workers as well as the system of collective bargaining. As such workers were granted rights not only to form and join trade unions but also to have their unions affiliated to groups of unions confederated on a country-wide basis.[8] The term strike was given statutory definition as being:

> *... any temporary cessation of work by the concerted action of a group of employees taken in connection with and intended as a means of influencing an existing labour dispute.*[9]

Despite this definition, however, the Proclamation did not have any provision in which the right of workers to strike as a means of securing their demand was

recognized. It did not expressly deny it either. It prohibited unfair practices and it defined certain forms of strikes as elements of such unfair practices.[10] Difficult as the task of drawing any distinction between the forbidden practices and others may be, let us now examine the provision at some length.

The first proviso imposed on all forms of strikes was that they should not be initiated, organized and conducted by any other person or group except trade unions. Even workers of an undertaking with a serious trade dispute could not conceive of any idea of conducting a strike unless they had a union. Workers in undertakings with less than fifty workers were not allowed to form a union although it was possible for them to join general labour unions with workers of other undertakings. But this, at the time, was a rare occurrence.

It was also an unfair labour practice within the meaning of the Proclamation to incite or conduct a strike which was outside the scope of the lawful activities of trade unions. The scope of activities of trade unions was taken to be the regulation of labour conditions and activities permitted in the Proclamation, as well as the study, protection and development of the economic,social and moral interests of their members. It was in the scope of activities of trade unions to negotiate freely and voluntarily matters in the field of labour conditions and settle disputes arising therefrom by peaceful means whenever possible.[11]

Strikes initiated without willingness to negotiate in good faith or arbitrarily were likewise said to fall within the domain of unfair labour practices under the Proclamation. In this respect questions to be raised are: What is meant by initiation of arbitrary strikes? How is one to establish failure to show willingness to negotiate in good faith? What, after all, was meant by such terms as good faith and arbitrariness? Which body was empowered to determine the existence of these reasons? No explanation was given on these and related points of controversy and it seems the interpretation was left to the Minister of Community Development and Social Affairs, who had wide powers to implement the Proclamation and to issue subsidiary regulations for the better carrying out of its provisions.[12] Other bodies in whom the power to interpret the Proclamation was vested were the Labour Relations Board and the Supreme Imperial Court.

Similarly, conducting or initiating strikes prior to submission of the dispute to the Labour Relations Board and before the expiration of a period of sixty days following such submission as well as conducting strikes in violation of or against the final decision or award of the Board was also an element of unfair labour practice and therefore unlawful in the eyes of the Proclamation. First, the attention of the

employer must be drawn to the dispute that might lead to the intended strike. In the event of failure to reach an agreement acceptable to the parties, the law required it to be taken before the Board. The Board, after having exhausted all possible means of arriving at amicable settlement, had two options. It might reject the demands of the trade union and its petition for strike upon such terms as it may think appropriate, or it might grant the petition to strike so that the employer could be forced to submit to the demands of the union. It was also possible to initiate and conduct strikes sixty days after taking the dispute before the Board and if the latter failed to render any decision or award. Silence of the Board, for one reason or another, made the strike lawful once the prescribed time lapsed.

